# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 234 ሚያዝያ 24 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# የኢድ አልፈጥር በዓልን በሰላም እና በመረዳዳት ማሳለፍ እንደሚገባ ተገለጸ



**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ሕዝበ ሙስሊሙ የኢድ አልፈጥር በዓልን በሰላም፣ በመከባበር፣ በመተባበር፣ በመቀራረብ እና በመረዳዳት ማሳለፍ እንደሚገባ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጅ ዑመር እድሪስ ጥሪ አቀረቡ፡፡

በኢትዮጵያና በተለያዩ የውጭ አገራት ለሚገኙ ሙስሊሞች ለ1443ኛው ኢድ አልፈጥር በዓል የሰላም፣ የልማት፣ የመተባበር፣ የመከባበር እና የመረዳዳት እንዲሆን ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጅ ዑመር ተመኝተዋል።

ረመዳን የመተሳሰቢያ እና የመረዳጃ እንደመሆኑ በኢድ አልፈጥር በዓልም የሌላቸውን ሰዎች፣ ሸማግሌዎችንና ሕመምተኞች በደስታ ዕለት እንዳይከፋቸው ከጎናቸው መሆን ይገባል ብለዋል፡፡

ያላቸው ለሌላቸው፣ ጎረቤት ለጎረቤቱ፣ ጓደኛ ለጓደኛው እንዲረዳ እና እንዲያግዝ ጥሪ አቀርባለሁ፡፡ ‹‹እንተዛዘን፣ እንተባበር፣ እንከባበር›› ሲሉም ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጅ ዑመር ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ያላቸው ወገኖች የሌላቸውን በመመደገፍ ሁሉም በበዓሉ ተደስቶ እንዲያሳልፍ ሊያደርግ እንደሚገባውም ጥሪ አቅርበዋል።

ወላጆች፣ ወጣቶች፣ አስተማሪዎችና ተማሪዎች መሪዎች፣ ፖለቲከኞች ወደ ሰላም፣ ወደ ልማት መመለስ ይገባቸዋል ያሉት ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጅ ዑመር፤ በዓሉን በሰላም ማክበር፣ ከጫጫታ እና ከተቃውሞ በመራቅ ማሳለፍ ይገባልም ብለዋል፡፡

ረመዳናችንን በአዲስ አበባ ከተማ በሰላም፣

‹‹የኢድ አልፈጥር... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# «የኢድ በዓል ትሩፋቶች ከእምነቱ ተከታዮች ባለፈ ለሌሎችም መትረፍ የሚችሉ ናቸው»

*- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ*



አዲስ አበባ፡- የኢድ በዓል እሴቶችና ትሩፋቶች ከእምነቱ ተከታዮች ባለፈ ለሌሎችም መትረፍ የሚችሉ ናቸው ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ትናንት ባስተላለፉት እንኳን ለዒድ አል ፈጥር በዓል አደረሳችሁ መልዕክት ሕዝበ ሙስሊሙ ያሉትን መልካም ነገሮች ይዞ እርስ በእርሱ እየተጠያየቀ፣ አብሮነቱንና አንድነቱን የሚያሳይበት፣ ያለው ከሌለው የሚረዳዳበት፣ ያገኘው ካላገኘው ምግብና ፍቅርን ተጋርቶ የሚያሳልፍበት ዕለት ነው። እነዚህ እሴቶችና የበዓሉ ትሩፋቶች ከእምነቱ ተከታዮች ባለፈ ለሌሎችም መትረፍ የሚችሉ ናቸው ብለዋል።

ፈጣሪ ለሰው ልጆች ደስታ ሲል የሰጠውን የዒድ በዓል መላው ሕዝበ ሙስሊም በሐሴት ያከብረዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የደስታው ምንጭ መብላት መጠጣቱ፣ መልበስና ማጌጡ አይደለም፤ ከራስ ባለፈ ከሌሎች ጋር በአብሮነት ማሳለፉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

«የኢድ በዓል ትሩፋቶች... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ሊሳይ ኃይለማርያም

# የሕወሓት ዳግም የጦርነት ቅስቀሳ በትግራይ ሕዝብ ላይ ተጨማሪ ቀውስ ለመፍጠር ያለመ ነው

**ማእረግ ገብረእግዚአብሔር**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት ቡድን እራሱ የፈጠረውን ችግር አሁንም በኃይል እፈታዋለሁ በሚል የሚያደርገው ዳግም የጦርነት ቅስቀሳና ዝግጅት በትግራይ ሕዝብ ላይ ተጨማሪ ቀውስ ለመፍጠር መሆኑን ራእይ ፓርቲ መሥራችና ሊቀመንበር አቶ ሊላይ ኃይለማርያም ገለጹ፡፡ ቡድኑ በቂ ወታደራዊ ስልጠና ያልነበራቸውን ወጣቶች ወደ ጦርነቱ መማገዱን ማመኑንም አመልክተዋል፡፡

አቶ ሊላይ ኃይለማርያም ለወጋህታ ጋዜጣ እንደገለፁት፤ የሕወሓት ቡድን መሪዎች ችግሩን በኃይል እንፈታዋለን የሚሉት ለትግራይ ሕዝብ ችግር

የሕወሓት ዳግም... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







የጋራ ሃሳብ ለጋራ ታሪክ ገጽ 7

ወሰኑ እስከ መጻሕፍት ልገሳ የዘለቀው ኢትዮጵያዊ እሴት ገጽ 9

# ኢትዮጵያ የአበባ ምርቶችን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከ371 ሚሊዮን ዶላር በላይ ማግኘቷ ተገለጸ

## ●የአበቦች የወጪ ንግድ የ9 ነጥብ 8 በመቶ ዓመታዊ እድገት እያሳየ ነው

**በግርማቸው ጋሻው**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከአበባ ምርቶችን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከ371 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘቷን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሚኒስቴሩ የሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንትና ኤክስፖርት ድጋፍ ዳይሬክተር አቶ መኮንን ሰለሞን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ባለፉት 9 ወራት የአበባ ውጤቶችን ወደ ውጭ ገበያ በመላክ ከ371 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ አግኝታለች።

የኢትዮጵያ የአበባ ምርት በአሁኑ ወቅት ወደ 56 አገራት እየተሸጠ እንደሚገኝ አመልክተው፤ ኔዘርላንድስ 76 በመቶ የሚሆነውን ምርት ወደ አገሯ ማዕከላዊ ገበያ በማቅረብ ለተቀሩት የአውሮፓ አገራት ታከፋፍላለች። ባለፉት ዘጠኝ ወራት ብቻ እንኳን 251 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ የአበባ ምርት ለማዕከላዊ ገበያው ቀርቧል ሲሉ ተናግረዋል።

በሆርቲካልቸር ዘርፍ በአጠቃላይ 200ሺህ ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል መፈጠሩን የገለጹት አቶ መኮንን፤ የአበባው ንዑስ ዘርፍ በሥራ ዕድል ፈጠራ ረገድ 80 በመቶ አስተዋፅዖ ማድረጉን ጠቅሰዋል።

የአበባው ንዑስ ዘርፍ ከ18 ዓመታት የዘለለ ታሪክ እንዳልነበረው ገልጸው፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያ በዘርፉ ትልቅ እመርታ በማስመዝገብ ከዓለም አራተኛዋ አበባ ላኪ አገር ሆናለች። በአፍሪካም ከኬንያ ቀጥላ ሁለተኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኝም ገልጸዋል።

የአገሪቱ አግሮ ሥነ-ምህዳር ማንኛውንም ዓይነት ተክሎችን ለማምረት አመቺ መሆኑ፤ ያልተጋነነ የሎጀስቲክስ ትራንስፖርት ዋጋ መኖሩ፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦት መዘርጋቱ፣ መሰልጠን የሚችል በቂ የሰው ኃይል እና ከአምስት እስከ ሰባት ዓመት የሚደርስ የታክስ እፎይታ መኖሩ ዘርፉ እንዲያብብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካደረጉት መካከል ይጠቀሳሉ።

የአበባ ልማት ዘርፍ እየለማ የሚገኘው ከአንድ ሺህ 600 ሄክታር መሬት የማይበልጥ ቢሆንም የአበባ ልማት ዘርፍ አስተማማኝ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ እየሆነ መምጣቱን ጠቁመው፤ በክልሎች የሚስተዋለው የመሬት አቅርቦት ችግር ቢፈታ ዘርፉ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ እንደሚሆን ግልጽ ነው ብለዋል ዳይሬክተሩ።

መንግሥትም በዘርፉ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት የፖሊሲ ማሻሻያ ማድረጉን ጠቁመዋል።

# አባይ በረሃን አቋርጦ የሚልያፈው መንገድ በመበላሸቱ ለእንግልት መዳረጋቸውን አሽከርካሪዎች አማረሩ

## •አስተዳደሩ በበከሉ ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ችግሩን እያጠናሁ ነው ብሏል

**ወርቁ ማሩ**



ደጀን፡-ከአዲስ አበባ ወደ ባህር ዳር አባይ በረሃን አቋጦ የሚያልፈው መንገድ በመበላሸቱ አሽከርካሪዎች ለእንግልትና ለተጨማሪ ወጪ መዳረጋቸውን ገለጹ። የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በበኩሉ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ከጃፓን ኩባንያ ጋር በመሆን እያጠናን ነው ብሏል።

ላለፉት 11 አመታት ከአዲስ አበባ ወደ ተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶችን እንዳሽረከሩ የሚገልጹት አቶ ማዕረግ በየነ እንደገለጹት፣ መንገዱ በአሁኑ ወቅት ያለበት ደረጃ ሙሉ በሙሉ ከአስፋልት መንገድነት ወጥቶ ለማሽከርከር አደገኛ የሚባል ደረጃ ላይ መድረሱን ጠቁመው፣ በዚህ የተነሳ ለእንግልት እና ለተጨማሪ ወጪ መዳረጋቸውን ገልጸዋል።

መንገዱ በየጊዜው እየተንሸራተተ ለአደጋ የሚያጋልጥ ሆኗል የሚሉት አቶ ማዕረግ፤ የመንገዶች ባለስልጣን ሠራተኞች በየጊዜው ጥገና ቢያደርጉም የመንገዱ ሁኔታ ግን ከጊዜ ወደጊዜ እየተበላሸ ነው ብለዋል።

አንዳንድ ጊዜ መንገዱ ሲበላሽ እስከ ሰባት ሰዓት ድረስ የምንቆምበት ሁኔታ ያጋጥማል የሚሉት አቶ ማዕረግ ከዚህም በተጨማሪ ተሽከርካሪዎቻቸው በየጊዜው ስለሚበላሹና ጎማና ፍሬን ሸራ በየጊዜው ስለሚጨርሱ ለከፍተኛ ወጪ እየተዳረግን እንገኛለን ብለዋል።

ሌላው በአካባቢው ለብዙ ዓመታት የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ እንዳሽከረከረ የገለፀልን አቶ አበበ ማሞ በበኩሉ የአባይ በረሃ መንገድ አሁን ያለበት ሁኔታ ዘግናኝ ነው ይላል።

ከመንገዱ ብልሽት የተነሳ ተሽርካሪዎች በየጊዜው ለብልሽት እንደሚዳረጉ የሚገልፀው አቶ አበበ፣ አሁን ካለው የመኪና መለዋወጫ ዕቃ ውድነት አንጻር ለከፍተኛ ኪሳራ እየዳረገን ነው ብሏል።

ቀደም ሲል የመንገድ ዲስትሪክት ሠራተኞች አልፎ አልፎ ጥገና ሲያደርጉ ነበር የሚለው አቶ አበበ፤ አሁን ግን መንገዱ በከፍተኛ ሁኔታ በመበላሸቱ በጥገና ብቻ የሚስተካከል እንዳልሆነና ተሳፋሪዎች ጭምር እየተማረሩ ነው ብሏል።

እንደ አቶ አበበ ገለጻ፤ ከባድ ተሽርካሪዎች ጭነት ጭነው ሲሄዱ መንገድ ላይ ይበላሻሉ፤ ወደኋላ ይንሸራተታሉ፤ በዚህ የተነሳ ብዙ ጊዜ መንገድ ይዘጋል። በመሆኑም በዚህ መንገድ ላይ ማሽከርከርም ሆነ ተሳፋሪ ሆኖ መመላለስ፣ ለአደጋ የሚያጋልጥ ሆኗል ብሏል።

ከዚህ ቀደም ከአዲስ አበባ ደጀን በአንድ ቀን ደርሰው ይመለሱ እንደነበር የጠቆመው አቶ አበበ፣ አሁን ግን ከአንድ ጊዜ በላይ መሄድ እንዳልቻሉ ጠቁሟል።

ሌላው አሽከርካሪ አቶ ብስራት ተገኝ በበኩሉ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዚህ መንገድ ማሽከርከርም ሆነ መጓዝ ከፍተኛ አደጋ የተጋረጠበት ሆኗል።

ቀደም ሲል አንድ ቀን ይፈጅ የነበረው ጉዞ ሁለት ቀን ከመፍጀቱም በላይ የተሽከርካሪ መበላሸት፣ የተሳፋሪ መጉላላት እና ድካም እየጨመረ በመሆኑ መንገዱ አስቸኳይ መፍትሄ ሊሰጠው ይገባል ብሏል።

ከዚህ ባሻገር በየከተማው ስንገባ የባጃጅ ታክሲዎች ከፍተኛ ችግር እየፈጠሩባቸው በመሆኑ ከተሞችን ስናቋርጥ ከፍተኛ ችግር እየገጠመን ነው የሚሉት አቶ ብስራት በአጠቃላይ ዘርፉ ከፍተኛ ፈተና እየተጋረጠበት ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የዓለምገና መንገድ ኔትወርክ እና ደህንነት አስተዳደር ቅርንጫፍ ዳይሬክተር አቶ አመዴ ሙህዬ እንደገለፁት፣ መንገዱ አስቸጋሪ ከሚባሉ መንገዶች አንዱ ሲሆን ይህንን ታሳቢ በማድረግም በአካባቢው ላይ በቋሚነት ክትትልና ጥገና የሚያደርጉ ባለሙያዎችን መድቦ እየሠራ ነው።

ባለፈው ዓመት በዚህ አካባቢ ከፍተኛ ጥገና አድርገን ነበር የሚሉት አቶ አመዴ፣ በዚህ ዓመትም አንድ መቶ ሚሊዮን ብር በጀት ተይዞለት የጥገና ሥራ ለማከናወን ቢታቀድም መንገዱ እየተንሸራተተ ማስቸገሩን ጠቁመዋል። በዚህ የተነሳም ቦታዎችን በመምረጥ እና በግራ ጠርዝ ላይ ብቻ የማስተካከያ ሥራ በመሥራት ችግሩን በጊዜአዊነት ለመፍታት እየሠሩ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ከዚህ ጎን ለጎን የመንገዱን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት አይካ ከተባለ የጃፓን ኩባንያ ጋር በመመካከር ዘላቂ መፍትሄ የሚገኝበትን ሁኔታ ለማቻቸት እየተሠራ መሆኑንና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም በዚህ ላይ እየተሳተፈ መሆኑን ጠቁመዋል። እስከዚያ ድረስ ግን አሁን በተያዘው እቅድ መሠረት ጊዜአዊ ጥገና እያደረጉ ችግሩን በጊዜአዊነት ከማቃለል ውጪ ሌላ አማራጭ የለም ብለዋል።

ከዚህ ቀደም ያጋጠመንን የግብአት ችግር ለመፍታትም በአሁኑ ወቅት ግብአት ከውጭ አስገብተን እየሠራን ነው ያሉት አቶ አመዴ፣ በጣም የተበላሹት መንገዶች ለማስተካከል ለይተው እየሠሩ እንደሆነም ጠቁመዋል።

አሁን ባለው ሁኔታ በዚህ ጊዜ ችግሩን ሙሉ ለሙሉ ለማቃለል እንችላለን ለማለት ጥናቱ መጠናቅ አለበት ያሉት አቶ አመዴ፤ ይህ ደግሞ ረጅም ጊዜ ሊፈጅ ይችላል የሚል ግምት እንዳላቸው ተናግረዋል።

ባለፈው ዓመት ትልቅ ቋጥኝ መንገዱ ላይ በመውደቁ ለአንድ ሳምንት መንገዱ ተዘግቶ እንደነበር ያስታወሱት አቶ አመዴ፤ በዚህ አካባቢ ያለው መንገድ ተለዋጭ እየተሠራለት እንደሆነም ተናግረዋል። ሆኖም በአጠቃላይ ተለዋጭ መንገድ ለመሥራት ከባድ እንደሆነና ሆኖም ዘላቂውን መፍትሄ በተመለከተ ጥናቱ የሚመልሰው ይሆናል ብለዋል።

# ለአገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት የሕግ የበላይነት መከበር ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ተጠቆመ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**



አዲስ አበባ፡- ለአገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት የሕግ የበላይነት መከበር ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ተጠቆመ። በየአካባቢው የሚስተዋሉት የሰላምና የደህንነት ችግሮች ከአገራዊ ምክክሩ ቅድሚያ ትኩረት ተሰቷቸው ሊሠሩ የሚገባቸው ጉዳዮች መሆናቸውም ተመላክቷል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና የዓለምአቀፍ ግንኙነት መምህርና ተመራማሪ ዶክተር ደመቀ ሀጪሶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ዜጎች ወሳኝ አገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት በማድረግ ብሔራዊ አንድነትና መግባባት ለመፍጠር የሚደረገው አገራዊ ምክክር ተገቢና ወሳኝ ተግባር ነው።

ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ልሂቃን፣ ከሕዝብ ተወካዮች፣ የሲቪል ማኅበራት እንዲሁም የሃይማኖት ተቋማትና ሌሎች ከፌዴራል እስከ ቀበሌ ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር ለማድረግ የታለመው አገራዊ ምክክር ከወዲሁ በርካታ ፈተናዎች እየገጠሙት መሆኑን ጠቁመዋል።

ለዚህም እንደ ዋነኛ ፈተና የሚጠቀሰው በየአካባቢው የሚስተዋለው የሰላምና ደህንነት ስጋት መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር ደመቀ፣ ዜጎች በጉዳዮቻቸው ላይ በግልፅ እንዲወያዩና እንዲነጋገሩ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች የሕግ የበላይነት ሊረጋገጥ እንደሚገባ ገልፀዋል።

የተቋቋመው ኮሚሽን ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ መሥራት እንደሚጠበቅበት ተናግረዋል። ለዚህም በሚንቀሳቀስባቸው አካባቢዎች አስተማማኝ ሰላምና ደህንነቱ የተረጋገጠ አካባቢ መፍጠር የመንግሥት ቀዳሚና ቁልፍ ተግባር ነው ብለዋል።

እንደ ዶክተር ደመቀ ገለፃ፤ ከባለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህ በተካሄደው አገራዊ ለውጥ የአገሪቱን የፖለቲካ አቅጣጫ መተንበይ የሚከብድና በየጊዜው የመቀያየር ባህሪ የሚስተዋልበት ነው። በመሆኑም አሁን ባለው የአገሪቱ ሰላምና ደህንነት ነባራዊ ሁኔታ ወደ መረጋጋት ካልሄደና አስተማማኝ ሰላም ካልተመለሰ ለኮሚሽኑ ፈተና ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል።

አሁን ባለው የሰላም ሁኔታ በየአካባቢው ግጭቶች በተነሱ ቁጥር የሰዎች ሞት፣ መፈናቀል፣ እርስ በእርስ መጠራጠር በመበራከት በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በልሂቃን፣ በሲቪክ ማኅበረሰቡ መካከል ሌላ የልዩነት አጀንዳ እየተፈጠረ በመምጣት የአገራዊ ምክክሩ ውጤታማነት ላይ ፈተና ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል።

በአገራዊ ምክክሩ ማኅበረሰቡ ውስጥ የተፈጠረውን ተስፋ መሬት ላይ ካለው ተግዳሮት በማስታረቅ ኮሚሽኑ በተገቢው በማጤን መንቀሳቀስ እንዳለበት አሳስበዋል።

በአገሪቱ የሰላምና ደህንነት ጉዳዮች ላይ ከሰሞኑ የፀጥታው ምክር ቤት ያስተላለፋቸው ውሳኔዎችና ሌሎች ዋና ዋና ተግባራት ወደ መሬት ወርደው ተግባራዊ መሆን እንዳለባቸው ያብራሩት ዶክተር ደመቀ፣ አሁንም በአገር ሰላምና ደህንነት ጉዳዮች ላይ የተላለፉ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆን ካልቻሉ ማኅበረሰቡ የተለመደ ጉዳይ አድርጎ ሊወስደው እንደሚችል ያላቸውን ጥርጣሬ ተናግረዋል።

በሌላ በኩል በአገር ደረጃ የተከሰተው የኢኮኖሚ ጫና ከሰላም እጦቱ ጋር ተዳምሮ ማኅበረሰቡን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይ ወስድው መንግሥት ወሳኝ የሆኑ እርምጃዎች መውሰድ እንደሚገባውና ይህ ሁኔታም ሊደረግ በታሰበው አገራዊ ምክክር ላይ ሌላ ተግዳሮት እንዳይሆን ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አመልክተዋል።



# ዩኒቨርሲቲው ይፋ ያደረገውን የጥናት ውጤት በዓለም አቀፍ ጆርናሎች ላይ ለማሳተም ዝግጅት እያደረገ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት የፈጸመውን የዘር ጭፍጨፋ ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ እንዲደርስ የጥናት ውጤቱን በዓለም አቀፍ ጆርናሎች ላይ ለማሳተም ዝግጅት እያደረገ መሆኑን የጎንደር ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ።

በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የኅብረተሰብ ጤና መምህር፣ ተመራማሪና የጥናት ቡድኑ መሪ ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ አስራደ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ይፋ ያደረጋቸውን የጥናት ግኝቶች ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ጠቃሚ በመሆናቸው በተለያዩ ጆርናሎች ላይ የማሳተም ልምድ አለው። አሸባሪው ሕወሓት በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት የፈጸመውን የዘር ጭፍጨፋ በተለይ የእንግሊዝኛ አንባቢዎች በቀላሉ እንዲያገኟቸው ለማድረግ በዩኒቨርሲቲው በኩል በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ይህ የዩኒቨርሲቲው መደበኛ ሥራ በመሆኑ የሚወጡ ጥናቶች በእንግሊዝኛ ይታተማሉ ብለዋል።

ቡድኑ በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት የፈጸመውን የዘር ጭፍጨፋ የዓለም ሕዝብ እንዲያውቀው ሴሚናር ለማዘጋጀት ዩኒቨርሲቲው እቅድ አለው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ፤ አውደ ጥናቱ በእንግሊዝኛ የሚቀርብ ይሆናል። ኤምባሲዎችና ማንኛውም ማኅበረሰብ መሳተፍ ይችላል። ይፋ የሆነው የጥናት ውጤት በመሆኑ ምንም ዓይነት የፖለቲካ ይዘት የለውም። ማንም ሰው መጥቶ መታደም ይችላል። ምን ያክል ሰው ጅምላ መቃብር ውስጥ አለ፣ ሂደቱ ምን ይመስል ነበር የሚለውን ለመለየት ወደ ፊት የፎረንሲክ ምርመራ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል። በቀጣይ ምርምር ማድረግ የሚጠይቁ ሥራዎች ስላሉ የትኛውም የዓለም አቀፍ ተቋም ለመሥራት ፍላጎት ካለው የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ፈቃደኛ ነው ብለዋል።

በጥናቱ ዙሪያ ከዓለም አቀፍ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የተጀመሩ ሥራዎች አሉ ያሉት የቡድን መሪው፤ ከዓለም አቀፍ ምሁራን ጋር ጉዳዩን በጋራ መሥራት የሚችሉ ግለሰቦችና ተቋማት ጋር መነጋገር መጀመሩን ገልጸዋል።

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር ጌታ ገለጻ፤ ይህ ጉዳይ በአንድ ሳምንትና ወር የሚፈጸም ሳይሆን ጊዜ የሚወስድ ነው። ጥናቱ የጥናት መርሆችን ተከትሎ የተካሄደና ሙሉ መረጃዎች በእጃችን ያለ በመሆኑ ማየት ይቻላል፤ ነገር ግን የጥናቱን ውጤት ላለመቀበል ፍቃደኛ ያልሆነ ግለሰብ ካለ አላማው ሌላ ስለሆነ በየትኛውም ቋንቋ ቢቀርብለት ላይቀበል ይችላል።

እውነትን የሚቀበል ማኅበረሰብ በመረጃ የተደገፈ እውነታዎችን በማውጣት ለማሳየት እየተሠራ መሆኑን አብራርተዋል።

ጉዳዩ ከዩኒቨርሲቲው በላይ ስለሆነ የመንግሥት፣ የአገር ውስጥ የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ ተቋማት ጭምር መሥራት አለባቸው። የፖለቲካ አላማ ያለው ግለሰብና ተቋም ጥናቱን በማጣጣል ውዥንብር ሊፈጥር ይሞክራል፤ ነገር ግን የጎንደር ዩኒቨርሲቲ አላማ ለሰላም፣ ለልማትና ለዴሞክራሲ ሲል እውነታን የማውጣት ሥራ እየሠራ ነው።

ጥናቱ እንደሚያሳየው የሰብአዊ መብት፣ የዓለም አቀፍ ወንጀልና በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የተረሸኑበት ጉዳይ በመሆኑ መንግሥት፣ የዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ማወቅ ስለነበረበት የጥናቱ ግኝት በፍጥነት ይፋ ሆነ እንጂ ሥራው አለማለቁን ገልጸዋል።

# ሚዲያዎች በአገራዊ ምክክሩ ላይ ሊያበረክቱ ስለሚገባቸው አስተዋጽኦ ቀድመው እንዲዘጋጁ ተጠየቀ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ሚዲያዎች በአገራዊ ምክክሩ ላይ ሊያበረክቱ ስለሚገባቸው አስተዋፅዖ ከወዲሁ አበክረው እንዲያስቡ ተጠየቀ።

ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት ፕሮፌሰር አድማሱ ገበየሁ እንደገለፁት፤ ኃላፊነት የማይሰማቸው አካላት ማህበራዊ የትስስር ገፆችን ተጠቅመው ኅብረተሰቡን ሊያወናብዱ የሚችሉበትና አፍራሽ መልዕክት ሊያስተላልፉ የሚችሉበት ዕድል ሰፊ በመሆኑ ሚዲያዎች በአገራዊ ምክክሩ ላይ ሊያበረክቱ ስለሚገባቸው አስተዋፅዖ ከወዲሁ አበክረው ሊያስቡ ይገባል።

በአገራዊ ምክክሩ ላይ ማህበራዊ የትስስር ገፆች አወንታዊም ሆነ አሉታዊም ሚና ሊኖራቸው ይችላል። ይህን ታሳቢ በማድረግ መደበኛ መገናኛ ብዙኃን ኃላፊነት በጎደላቸው አካላት ሊነዙ የሚችሉ አሉባልታዎችንና መልዕክቶችን መመከት መቻል አለባቸው። ለዚህም ተዓማኒነታቸውን ገንብተው በፍጥነት ወደ ሕዝብ መረጃ የሚደርሱበትን መንገድ ሊያስቡ ይገባል ሲሉ መክረዋል።

በአዳራሽ ውስጥ ተሰባስበው ከሚመካከሩ ዜጎች ባሻገር አብዛኛው የአገራዊ ምክክሩ መድረክ ሚዲያ ነው። ሚዲያዎች ተዓማኒነትን ገንብተውና ፈጥነው መረጃ የሚያቀብሉ በማድረግ ቀውስን እየፈጠረ ሰውን የሚያሸብረውን የማህበራዊ ትስስር ገጽ ማዳከም ይቻላል። ይህም ለአገራዊ ምክክሩ በእጅጉ ይጠቅማል ብለዋል።



**ፕሮፌሰር አድማሱ ገበየሁ**

ምንም እንኳን አገራዊ ምክክሩ አካታች ቢሆንም በየአዳራሹ ተሰብስቦ መምክር የሚችለው ዜጋ ውስን ስለሚሆን ይህንን ክፍተት ለመሙላት ሚዲያ ትልቅ ኃላፊነት ይኖርበታል።

ታማኝ መረጃዎችን ለማውጣት ጊዜ ይፈልጋል፤ ጊዜው ሲሄድ ደግሞ ታማኝ መረጃዎች ዋጋቸውን አጥተው ሕዝብ ጋር ይደርሳሉ ያሉት ፕሮፌሰሩ አድማሱ፤ ፍጥነቱም ጥንቃቄውም እንዲኖር ደግሞ ሚዲያው በሰው ኃይልና በቴክኖሎጂ የተሟላ ሊሆን ይገባል።

ፕሮፌሰር አድማሱ እንደሚሉት፤ በአሁኑ ወቅት መገናኛ ብዙኃን በዚህ መጣ የማይባል የመዋጊያና የማጥቂያ ስልት ሆነዋል። የአንድ አገር ውጊያ በጦር መሣሪያና በጦር ሠራዊት ሲሆን አካላዊ ስለሚሆን ለመከላከልም ለማጥቃትም ምቹ ነው። ሚዲያን የተመለከትን እንደሆነ ግን በትንሽ ሰከንዶች ውስጥ የእያንዳንዱ ቤት ውስጥ መድረስ ስለሚችል ከባዱ የውጊያ ሜዳ ሆኖ ይገኛል። ይህንን የውጊያ ስልት ለመቋቋም ሚዲያዎች ከመቼውም ጊዜ በላይ ተነቃቅተው መሥራት እንደሚጠበቅባቸው ጠቁመዋል።

አገራዊ ምክክሩ ልክ እንደ ፍርድ ቤት ሥርዓት ሁሉ ሊዘገብበት የሚገባ አካሄድና ሥርዓት ስለሚኖረው በዚህ ዙሪያም ከሚመለከታቸው ጋር ተባብሮና ተቀናጅቶ መሥራት እንደሚገባ ፕሮፌሰር አድማሱ አሳስበዋል።

ፕሮፌሰር አድማሱ እንደገለጹት፤ አገርን በጥሩ ሁኔታ ከሚገነቡ ነገሮች አገራዊ ምክክር አንዱ ቢሆንም ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ግን ሁሉም አካል የበኩሉን ድርሻ ሲወጣ ነው። መገናኛ ብዙኃን በአገር ሰላምና ዕድገት ላይ የሚጫወቱትን ሚና በአገራዊ ምክክሩ ወቅትም ተግተው በመሥራት ሊፈጠሩ የሚችሉ ክፍተቶችን መዝጋት እንደሚኖርባቸው አስገንዝበዋል።



## ታላቁን የኢድ ሰላት በኢትዮጵያ ለማካሄድ የቅድመ ዝግጅት ሥራ ተጠናቀቀ

አዲስ አበባ፡- ታላቁን የኢድ ሰላት በኢትዮጵያ ለማካሄድ የቅድመ ዝግጅት ሥራ መጠናቀቁን የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት አስታወቀ።

ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ የጎረቤት አገራት የሃይማኖት መሪዎች እንዲሁም በአዲስ አበባና አካባቢዋ የሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚሳተፉበት የታላቁ ኢድ ሰላት ቅድመ ዝግጅት መጠናቀቁን ከኢድ እስከ ኢድ ብሔራዊ ኮሚቴ ሴክሬታሪያትና የአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት በጋራ ባደረጉት ስብሰባ አስታውቀዋል።

በወቅቱም የዘንድሮው የዒድ ሰላት ከዚህ በፊት ከነበሩት በተሻለ ቅንጅት ተሰርቶ ለአገር ገፅታ ግንባታ ከፍተኛ ሚና እንዲጫወት የሁሉንም አካላት ርብርብ እንደሚያስፈልግ ተመላክቷል።

ጥሪ የተደረገላቸው የጎረቤት አገራት አቻ ተቋማት ተወካዮችም በክብር እንግድነት ለመገኘት ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ መሆኑ ነው የተገለጸው።

ኢትዮጵያውያንናትውልደኢትዮጵያውያንም በበዓሉ ላይ ለመታደም አስቀድመው መግባት መጀመራቸውም ተጠቁሟል።

የዚህ ዓመት የኢድ ሰላት ስግደት ከከተማው ሁሉም አካባቢዎች በመሰባሰብ በጋራ ለመስገድ በሚያስችል መልኩ ዛሬ በአዲስ አበባ ስታዲየም የሚካሄድ መሆኑን ከአገልግሎቱ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

ኮሚቴው ጥሪውን አክብረው በዓሉ ላይ ለመታደም ለመጡ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች መልካም የኢድ አልፈጥር በዓል እንዲሆን ተመኝቷል።

## ጉባኤው ድብቅ ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች ሃይማኖቶችን ሽፋን በማድረግ ያልተገባ ድርጊት እንዲፈጸም እያደረጉ መሆኑን ገለጸ

አዲስ አበባ፡- ድብቅ ያላቸው ግለሰቦች ሽፋን በማድረግ ድርጊት እንዲፈጸም እያደረጉ መሆኑን የኢትዮጵያ የሃይ ማኖት ተቋማት ጉባኤ አስታወቀ። ጉባኤው ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለ፤ ሺህ 443ኛው ዓመተ ሂጅራ የኢድ አል ፈጥር በዓል በሰላም በጤና አደረሳችሁ ሲል መልዕክቱን አስተላልፏል።

ጉባኤው ትናንት ባወጣው መግለጫ፤ ሕዝበ ሙስሊሙ በዓሉን ሲያከብር በአገሪቱ እየሆነ ስላለው ክፋትና በደል በመጸጸት እውነተኛ ንስሀ በማድረግ ወደ ፈጣሪው በመጠጋት ሊሆን እንደሚገባ ገልጿል።

ግጭት እና ግድያ አሁንም እንደቀጠለ መሆኑን ያስታወቀው መግለጫው፤ ድብቅ አላማና ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች ሃይማኖቶችን ሽፋን በማድረግ ያልተገባ ድርጊት እንዲፈጸም እያደረጉ ሲሆን ለዘመናት ተከባብሮ የኖረውን ሕዝብ አንዱ በሌላው እንዲነሳና አለመተማመን እንዲፈጠር እያደረጉ መሆኑን አመላክቷል።

የዘንድሮውን በዓል ስናከብር ከውጭ አገር ወደ አገራቸው በመግባት ላይ ለሚገኙ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ደማቅ አቀባበል ማድረግ እንደሚገባ መግለጫው አስታውሷል።

መግለጫው ሕዝበ ሙስሊሙ በዓሉን ሲያከብር እስልምና በሚያስተምረው መሠረት የተቸገሩ ወገኖችን በመርዳትና ያለውን በማካፈል እንዲሆን አሳስቧል።

በወቅታዊ ሁኔታው ተፈናቅለው ከመኖሪያቸው ርቀው በችግር የሚገኙ ወገኖችን በማሰብ እንዲሆን ጉባኤው በመግለጫው አሳስቧል።

## የሕወሓት ዳግም የጦርነት

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ስለማይጨነቁና ደንታ ስሌላቸው ነው። የትግራይ ሕዝብ በሕወሓት ምክንያት እየተጎዳ ቢሆንም አሁንም ቡድኑ በትግራይ ሕዝብ ችግር ላይ ተጨማሪ ቀውስ ለመፍጠር የጦርነት ነጋሪት እየጎሰመ ነው።

የፌዴራል መንግሥት ለሰላም እጁን ቢዘረጋም፣ ሕወሓት ሰላም የሚፈልግ ኃይል አይደለም ያሉት አቶ ሊላይ፤ ሕወሓት ሲፈጠር ጀምሮ ችግሮችን በሰላም ፈትቶ አያውቅም፤ ባህሪውም የሚፈቅድለት አይደለም። ከዚህ በፊትም ብዙ ፖለቲካዊ ድርጅቶችን በኃይል እያጠፋ የመጣ ኃይል ነው ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ አቶ ሊላይ ገለፃ፣ ሕወሓት ችግሮችን በሰላም የመፍታት ፍላጎት የለውም፤ ሲፈጠር ጀምሮ በድርድር አያምንም። በሕወሓት ቤት የተለየ ሀሳብ ካነሳህ የሚጠብቅህ ሞት፣ ስቅላትና እስራት ነው፤ ከድሮ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ይህን ባህሪው እንደተጠናወተው ይገኛል።

ከአፈጣጠሩ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስም በኃይል እንጂ በድርድር የፈታው ችግር እንደሌለ ተናግረዋል።

አሁንም ከመንግሥት ያለው ችግር በሰላም ከመፍታት ይልቅ በኃይል እፈታዋለሁ ማለቱ ከባህሪው የሚመነጭ መሆኑን አውስተው፤ ምክንያቱም ችግሮች በሰላም ለመፍታት ባህሪው አይፈቅድለትም። ከባህሪው አንፃር ከሕወሓት ጋር በሰላም የሚፈታ ችግር እንደሌለና ሁሉም ነገር በጦርነት መፍታት የሚፈልግ ቡድን መሆኑን አመልክተዋል።

ሕወሓት በፈጠረው ችግር ብዙ የትግራይ ወጣት ሞቷል። ሕዝቡም ለከፋ ችግር ተዳርጓል፤ ወደ አጓራባች ክልሎችም እየተፈናቀለ ይገኛል ያሉት አቶ ሊላይ፤ አሁን ሕወሓት በአዲስ መልክ ጦርነት እጀምራለሁ የሚል ከሆነ በትግራይ ሕዝብ ላይ ተጨማሪ ቀውስ ከመፍጠሩ በተጨማሪ ለራሱ የመጨረሻ መጥፊያው መሆኑን አስረድተዋል።

ከዚህ በፊት በሕዝብ የተገኘው ድል ሕወሓት ለራሱ ጥቅም እንዳዋለው አውስተው፤ አሁንም ለራሱ ጥቅም ሲል የትግራይን ሕዝብ ወደ ችግር እየከተተው መሆኑን ተናግረዋል።

እስካሁንም ቡድኑ በፈጠረው ችግር ምክንያት ሕዝቡ አላስፈላጊ ዋጋ እየከፈለ ነው ብለዋል።

ሕዝቡ ከሕወሓት ጭቆና ነፃ ለመውጣት እየታገለ ቢሆንም ቡድኑ ሕዝብን በመከፋፈልና ነፃነት በመንፈግ የችግሩ ሰለባ እያደረገው እንደሚገኝ ገልጸው፤ ከቡድኑ ጨቋኝ ሀሳብ ያፈነገጡ ሰዎችን እየደበደበና እያሰረ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የትግራይ ሕዝብ የኢትዮጵያ አካል በመሆኑ የፌዴራል መንግሥት ከሌሎች ፖለቲካዊ ፓርቲዎች ጋር በመሆን ነፃ ሊያወጡት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የትግራይ ሕዝብ ለኢትዮጵያ ዋጋ የከፈለ ሕዝብ ነው ያሉት አቶ ሊላይ፤ ሕወሓት የትግራይ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ጭምር መሆኑ ተናግረዋል።

የሕወሓት አመራር ቡድን በቅርብ ጊዜ ከምሁራን ጋር ውይይት አድርገዋል ተብሎ በማህበራዊ ሚዲያ የተላለፈ የድምጽ መልዕክትም በጦርነት ወቅት በቂ ስልጠና ያልወሰዱ ወጣቶች በጦርነቱ ማሳለፋቸውንና አሁንም ለጦርነት እየተዘጋጁ መሆኑን መናገራቸውን ታውቋል።

በአማራና አፋር ክልሎች ደግሞ ዝርፊያ እንደፈፀሙ ማመናቸውንና የቡድኑ አመራሮችም አሁንም ለጦርነት መዘጋጀታቸውም ለሁለተኛ ጊዜ የትግራይ ወጣት እንዲያልቅ ፍላጎት እንዳላቸው የሚያመላክት መሆኑን አቶ ሊላይ ጠቅሰዋል።

## የኢድ አልፈጥር...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በመመካከር፣ በመተባበር ጨርሰናል። በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የመንግሥት አካላት በተለይም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ የጸጥታ ኃይሎች፣ መሪዎች ሊመሰገኑ ይገባል። በሰላም ማጠናቀቃችን ታላቅ ተግባር ነውም ብለዋል።

የዘንድሮ በዓል ከወትሮው ለየት ያለ መልክ አለው ያሉት ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጅ ዑመር፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ያቀረቡትን ጥሪ ተከትለው የኢድ በዓልን ለማክበር ከገቡ እንግዶች ጋር በደስታ እያከበርን እንገኛለን ነው ያሉት።

ምክር ቤቱ የመስጊድ መሥሪያ ቦታ አፍሪካ ሕብረት አዳራሽ አጠገብ ቦታ መረከቡን ያነሱት ተቀዳሚ ሙፍቲ ሃጅ ዑመር፤ ግንባታ ለመጀመር ዝግጅት መደረጉንም ተናግረዋል። በግንባታው መሳተፍ የሚፈልጉ ሀብታሞች፣ ባለሙያዎች እንዲሳተፉም ጥሪ አቅርበዋል።

ምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤቱ በሚገኝበት ስፍራ ለማስፋፊያ 10 ሺህ ካሬ ሜትር መረከቡን ጠቁመው፤ ቦታውን ጥቅም ላይ ለማዋል ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ተቀራርቦ በመነጋገር ለማልማት መነሳሳት እንዳለበት መክረዋል። ቦታውን በማልማት ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ ጥቅም እንዲሰጥ ለማድረግ ሁሉም ድርሻውን እንዲወጣም ጥሪ አቅርበዋል።

## «የኢድ በዓል ትሩፋቶች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ረመዳን በስግደት፣ በጸሎት፣ በደግ ሥራና በእዝነት ወደ ፈጣሪ ቀርቦ በጥሞና የሚያስብበት፣ ሁሉም ራሱን የሚመዝንበት የተባረከ ወቅት ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስተሩ፤ የረመዳን ወር በሕዝበ ሙስሊሙ ዘንድ እጅግ ታላቅ ቦታ ከሚሰጣቸው ወሮች መካከል ቀዳሚው ነው። የረመዳን ጾም ደምቆ እንደተጀመረ ሁሉ በድምቀት አልቆ እነሆ ለዒድ አል ፈጥር በዓል ደርሰናል። ሁላችንንም እንኳን አደረሰን ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

የዘንድሮው ረመዳን በኢትዮጵያ ፍቅርና አገራዊ አንድነት የታየበት ሆኖ በማለፉ ከመቼም ጊዜ የተለየ ተደርጎ በታሪክ ሲታወስ ይኖራል። «ከዒድ እስከ ዒድ» የተሰኘው አገራዊ ንቅናቄ ብዙዎችን ከመላው ዓለም አሰባስቦ በእናታቸው ቤት፣ በወገናቸው መሐል እንዲያሳልፉ ዕድል ፈጥሯል። ከመዲና ከተማችን ጀምሮ በክልል ከተሞችና በየቀየው በተዘጋጁ የጎዳና ላይ የኢፍጣር ፕሮግራሞች ወንዱ - ሴቱ፣ ሙስሊሙ - ክርስቲያኑ፣ ትንሹ - ትልቁ ኅብረትና አንድነቱን አሳይቷል። ኢትዮጵያም በልጆቿ ወንድማማችነት ደስ ተሰኝታለች ሲሉ ተናግረዋል።

በትንሽ በትልቁ እልህና ጠበኝነትን የሚቆሰቁሱ የሸይጣን እጆች በበዙበት በዚህ ወቅት ከሁላችንም የሚጠበቀው ትዕግሥትና ሰከን ብሎ ነገሮችን በጥሞና መመርመር መሆኑን አመልክተው፤ እኛም እንደ ሕዝብ ለውዲቷ አገራችን በጥሞና እንድንጸልይ፣ በሚዛናዊ ምልከታ እንድንራመድ፣ ለመልካምነትና ደግነት ራሳችንን እንድናስገዛ፣ የሸይጣን እጆችን በትዕግስትና በማስተዋል በትር እንድንረታ አበክሬ እጠይቃለሁ ብለዋል።

አገርን መገንባት እጅግ ብርቱ ድካም የሚጠይቅ መሆኑን ሁላችን እንረዳዋለን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በዐረብኛ ‹ከፍ ያለ ቦታ መድረስ የሚፈልግ ቢኖር ብዙ ሺህ ሌሊቶችን ሳይተኛ ማሳለፍ አለበት› የሚል ወርቃማ አባባል አለ። እኛም ከሌሎች አልባሌ ነገሮች ራሳችንን ቆጥበን፣ ዕውቀትና ጉልበታችንን ከፍ ያለ ቦታ ለመድረስ ማዋል እንደሚገባ አመልክተዋል።

ኢትዮጵያ፣ ገና አሁን ከጦርነት የወጣች አገር ናት። ከዚያ በፊት አንበጣና ኮሮና ጫና አሳርፎብን ነበር። እሱም ሳይበቃ ድርቅ ቁጥሩ ቀላል ያልሆነ ወገናችንን ክፉኛ ጎድቶታል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ፤ ብዙ ያጣነው ነገር አለና ስለጎደለብን መታገሥና በርትተን መሥራት እንጂ ተስፋ መቁረጥ የለብንም። መንግሥት የሚችለውን ሁሉ ያደረጋል። እናንተም ለአገር ህልውና ሲሉ የተሠዉ ጀግኖችን ወደ ሕይወት መመለስ ባትችሉ በሕይወት ያሉትን መርዳት፣ ቤተሰባቸውን መደገፍ ይገባችኋል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ስለ መረዳዳት ለሕዝበ ሙስሊሙ ማስረዳት ለቀባሪው እንደ ማርዳት ተደርጎ እንደሚቆጠር ዐውቃለሁ የሚሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ እናም ሰውን ከሰው ሳትለዩ፣ እከሌ ሙስሊም ነው ክርስቲያን ነው ሳትሉ፣ ከዚህና ከዚያ ወገን ብላችሁ አንዱን ከሌላው ሳትለዩ ዐቅማችሁ የፈቀደውን በማድረግ ለተጎዱ ወገኖቻችን እንድትደርሱላቸው በትኅትና እጠይቃችኋለሁ ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

ከዒድ እስከ ዒድ፣ ሁላችንንም የሚመለከት የሕዝብ በዓል መሆኑን ጠቁመው፤ የዚህ በዓል በደመቀ ሁኔታ መከበር፣ የሁላችንም ድምቀት፣ የሁላችንም ክብር እንደሆነ ማወቅ ይገባናል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ዒድ ሙባረክ!

ፈጣሪን የማሰብ፣ ለፈጣሪ የመገዛት፣ መልካም የማድረግ፣ የመረዳዳትና የመፋቀር ወቅት የሆነው ታላቁ የረመዳን ጾም በስኬት ተጠናቆ እነሆ ዛሬ ታላቁ 1443ኛው የዒድ አልፈጥር በዓል የሚከበርበት ቀን ሆኗልና ለመላ የእስልምና ምዕመናን እንኳን አደረሳችሁ ማለቱ ተገቢ ይሆናል። እንኳንስ አንድ ወር ቀርቶ አንዲት ደቂቃን እንኳን ሰው ሰላም ሆኖ የሚያሳልፈው በፈጣሪ ምህረትና ቸርነት ነውና ወሩን ሙሉ በሰላም፣ በፍቅርና በደስታ ያሳለፈን ፈጣሪ በትልቁ ማመስገን ግድ ይላል።

ታላቁ የረመዳን ወቅት የእስልምና እምነት ተከታዮች ከምግብና ከውሃ ራሳቸውን አቅበው በታላቅ ጾም፣ ጸሎትና ስግደት ፈጣሪያቸውን ሲማጸኑ ከርመዋል። ከዚህም ጎን ለጎን የእምነቱ አስተምህሮ የሆነውን የመረዳዳትና የመደጋገፍ መርህ መሠረት በማድረግም አቅም ላጠራቸው ወገኖች ድጋፍና እገዛ አድርገዋል። ወላጅና ጧሪ ደጋፊ የሌላቸውን ወገኖችን በመጎብኘትና በመርዳትም አምላካዊ ትዕዛዝን በተግባር አውለው አሳይተዋል።

ፍቅር እንዲጸና፣ ችግር እንዲወገድ፣ የአገራችን ሰላምና አንድነት እንዲጠበቅ በጸሎት ወደ ፈጣሪ ምልጃ ተደርጓል፤ እርቅና ይቅርታ ተሰብኳል፤ ቂምና ተንኮል ተወግዟል። በአጠቃላይ ወሩ ቅዱስ ተግባራትን በመፈጸምና ለፈጣሪ ራስን በማስገዛት በጽኑ ጾም ጸሎት አልፏል። ክርስቲያን ኢትዮጵያውያንም የኢፍጣር ፕሮግራሞች በማዘጋጀት ለሙስሊም ወንድምና እህቶቻቸው ያላቸውን ክብርና ፍቅር ገልጸዋል።

በተለይም ባለፈው ዓርብ በመዲናችን አዲስ አበባ ታላቅ የኢፍጣር ፕሮግራም በማካሄድ አንድነትን የማጠናከርና አብሮነትን የማጎልበት ተምሳሌታዊ ተግባር ተከናውኗል። ምዕመናኑ በዕለቱ የነበረው አስቸጋሪ የአየር ጸባይ ሳይበግራቸውና ከተለያየ አቅጣጫ የሚሰነዘሩ አፍራሽ መልዕክቶች ሳይበግራቸው ፕሮግራሙ ስኬታማ እንዲሆን ማድረግ ችለዋል። በዚህም በልዩነት ውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ ውበት ፍንትው ብሎ እንዲበራና የኢትዮጵያውያን አንድነትና ኅብረት ከብረት የጠነከረ መሆኑን ለማሳየት ተችሏል።

በዚሁ ፕሮግራም ላይ የተገኙ የሃይማኖት አባቶችና መሪዎችም በታላቁ ረመዳን ወቅት የታየው ፍቅር፣ መተሳሰብና መደጋገፍ ጸንቶ እንዲቀጥልና ጥላቻ እንዲወገድ አበክረው አሳስበዋል። አንዳንድ የጥፋት ኃይሎች በጎንደር የፈጸሙትን አሳፋሪ ተግባር በመኮነንም አጥፊዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ ጠይቀዋል። ከዚህም ጋር አያይዘውም ይህንን ሁኔታ እንደምቹ ሁኔታ በመጠቀም አገር ለማፍረስ የሚሠሩ የጥፋት ኃይሎች ተግባርም ስህተት መሆኑን አመላክተዋል። ስህተትን በስህተት፤ ነውርን በነውር ማረም እንደማይገባና እንደማይቻልም አጽንኦት ሰጥተው አሳስበዋል። በአስቸጋሪና ፈታኝ ወቅት ሰከን ማለት፣ ወንጀለኞችን ማጋለጥና አውቀውም ይሁን ሳያውቁ ለጥፋት ተልዕኮ ተባባሪ አለመሆን ምዕመኑ በጽናት ሊተገብሩት እንደሚገባ መክረዋል።

ዛሬ ታላቁ 1443ኛው የኢድ አልፈጥር በዓል ነው። በዚህ ዕለት የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ከንጋት አንስቶ በታላቅ ሃይማኖታዊ ሥነሥርዓት በዓሉ ወደሚከበርበት ቦታ ይጓዛሉ። በዚያም ለዚህ ታላቅ ቀን ያደረሳቸውን ፈጣሪ አመስግነውና ጸሎት አድርገው ወደየቤታቸው በመመለስ በዓሉን ከቤተሰብ፣ ከወዳጅና ከጎረቤት ጋር በደስታና በፍቅር ያከብራሉ። ከዚህም ጎን ለጎን ዘመድ ይጠየቃል፤ አቅምና ደጋፊ የሌላቸው ወገኖች ይጠየቃሉ፤ ይታገዛሉ። እዚህ ላይ ግን ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ቢኖር በተለይም አሁን ላይ አገራችን ካለችበት ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር ድጋፍ የሚሹ ወገኖች ብዙ መሆናቸውን ነው። በተለይም አሸባሪው ሕወሓት በዳግም ወረራ በአማራና በአፋር ክልሎች ባሉ ዜጎቻችን ላይ በፈጸመው የግፍ ተግባር በርካታ ዜጎች ከሞቀ ጎጇቸው ተፈናቅለዋል፤ ጥረው ግረው ያፈሩት ሀብትም ተዘርፎና ወድሞ ለከፍተኛ ችግርና እንግልት ተዳርገዋል። ከዚህም ሌላ በድርቅና በጸጥታ መደፍረስ ምክንያትም ድጋፍ የሚሹ ወገኖቻችን ቁጥርም ቀላል አይደለም። ስለሆነም መደጋገፉና መተሳሰቡ ከምንጊዜውም ይልቅ ዛሬ ላይ እጅግ አንገብጋቢና አስፈላጊ ሆኗል።

አሁን አሁን በአገራችን እየተስፋፋና እየተለመደ የመጣው በበዓል ወቅትም ሆነ በሌላ ጊዜያት የመረዳዳትና የመደጋገፍ ባህል በኢድ አልፈጥርም በዓል ተጠናክሮ እንደቀጠለ ከሰሞኑ የታዩ በጎ ተግባራት ምስክሮች ናቸው። ይህን ቅዱስ ተግባር መተግበርም በምድር ከሚሰጠው የሞራል ርካታ ባሻገር ከፈጣሪ የሚያስገኘው ዋጋ እጅጉኑ የላቀ ስለሆነ ዋጋው እጥፍ ድርብ ነው። ዒድ ሙባረክ!

# እንኳን ለዒድ አል ፈጥር በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

ፈጣሪ ለሰው ልጆች ደስታ ሲል የሰጠውን የዒድ በዓል መላው ሕዝበ ሙስሊም በሐሴት ያከብረዋል። የደስታው ምንጭ መብላት መጠጣቱ፣ መልበስና ማጌጡ አይደለም፤ ከራስ ባለፈ ከሌሎች ጋር በአብሮነት ማሳለፉ እንጂ። ሕዝበ ሙስሊሙ ያሉትን መልካም ነገሮች ይዞ እርስ በእርሱ እየተጠያየቀ፣ አብሮነቱንና አንድነቱን የሚያሳይበት፣ ያለው ከሌለው የሚረዳዳበት፣ ያገኘው ካላገኘው ምግብና ፍቅርን ተጋርቶ የሚያሳልፍበት ዕለት ነው። እነዚህ እሴቶችና የበዓሉ ትሩፋቶች ከእምነቱ ተከታዮች ባለፈ ለሌሎችም መትረፍ የሚችሉ ናቸው።

ከዒዱ አስቀድሞ ሙስሊሙ ወር ሙሉ ከክፋት ርቆ ደግነትን ይለምዳል፤ ከዓለማዊ ተግባር ርቆ መልአይካዎችን ይመስላል። መላእክት አይበሉም፤ አይጠጡም፤ በፍጹም ልባቸው የፈጣሪን ትዕዛዝ ይፈጽማሉ። ሕዝበ ሙስሊሙም በረመዳን ወር ከዚህ የተለየ አያደርግም። ወሩ አላህ (ሱወ) እጅግ ውድ ስጦታዎቹን የሰጠበት፣ ቁርአን ወደ ምድር የወረደበት፣ የጀሃነም በሮች ተዘግተው የጀነት በሮች የተከፈቱበት፣ አማኙ እንደ እምነቱ ጽናትና እንደ አላህ (ሱወ) እዝነት ምናዳዎችን የሚያገኝበት የተቀደሰ ወር ነው።

በቁርአን አማኙ ከፈጣሪው ጋር ተነጋግሯል፤ የሚበጀውን የሕይወት መንገድ መርጦ እንደ ፈጣሪው ትእዛዝ ለመኖር ዕድል አግኝቷል። በስግደት፣ በጸሎት፣ በደግ ሥራና በእዝነት ወደ ፈጣሪ ቀርቦ በጥሞና የሚያስብበት፣ ሁሉም ራሱን የሚመዝንበት የተባረከ ወቅት ነው - ረመዳን። በዚህ ምክንያት የረመዳን ወር ሲጠናቀቅ ሕዝበ ሙስሊሙ ወሩ አለቀልን ከማለት ይልቅ አለቀብን ማለትን ያስቀድማል። ይኽ ቅዱስ ወር በሕይወቱ ውስጥ ዳግም የሚመጣበትን አጋጣሚ እየናፈቀም ይቆያል። ለዚያም ነው የረመዳን ወር በሕዝበ ሙስሊሙ ዘንድ እጅግ ታላቅ ቦታ ከሚሰጣቸው ወሮች መካከል ቀዳሚው የሆነው። የረመዳን ጾም ደምቆ እንደተጀመረ ሁሉ በድምቀት አልቆ እነሆ ለዒድ አል ፈጥር በዓል ደርሰናል። ሁላችንንም እንኳን አደረሰን!

የዘንድሮው ረመዳን በኢትዮጵያ ፍቅርና አገራዊ አንድነት የታየበት ሆኖ በማለፉ ከመቼም ጊዜ የተለየ ተደርጎ በታሪክ ሲታወስ ይኖራል። «ከዒድ እስከ ዒድ» የተሰኘው አገራዊ ንቅናቄ ብዙዎችን ከመላው ዓለም አሰባስቦ በእናታቸው ቤት፣ በወገናቸው መሐል እንዲያሳልፉ ዕድል ፈጥሯል። ከመዲና ከተማችን ጀምሮ በክልል ከተሞችና በየቀየው በተዘጋጁ የጎዳና ላይ የኢፍጣር ፕሮግራሞች ወንዱ - ሴቱ፣ ሙስሊሙ - ክርስቲያኑ፣ ትንሹ - ትልቁ ኅብረትና አንድነቱን አሳይቷል። ኢትዮጵያም በልጆቿ ወንድማማችነት ደስ ተሰኝታለች።

ፈጣሪም የሚፈልገው ይኼንን ነው። በቅዱስ ቁርአኑ ላይ በግልጽ እንደሰፈረው «ልቦቻችሁን የሰበሩ ጠላቶቻችሁ ቢሆኑም እንኳ በአላህ ፈቃድ ወንድም ሊሆኑዋችሁ ይችላሉ» በማለት ሁሉም የአደም ልጆች በአንድነት ሳይከፋፈሉ እንዲያምኑ፣ ፈጣሪ ያደረገላቸውንም እንዲያስታውሱ፣ በሰው ልጆች መሐል ፍቅርና መረዳዳት እንደሚያስፈልግ አበክሮ ይገልጻል። የቱንም ያህል የሐሳብ ልዩነት ቢኖረን፣ በባህልና በወግ - በቋንቋና በልማድ ብንለያይ፣ ያለን አንድ አገር እስከሆነ ድረስ፣ እነዚህ ልዩነቶችን ተሻግረን ወንድማማችና እኅትማማች እንድንሆን፣ እርስ በእርስ እንድንተሳሰብ የፈጣሪ ትእዛዝ ያሳስባል። ‹የአላህ እጅ ሱብሱብ ብለው በአንድነት በቆሙ ሰዎች መካከል ይገኛል› የሚለው የእምነቱ አስተምህሮም ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው።

### ውድ ወገኖቼ፣

በትንሽ በትልቁ እልህና ጠበኝነትን የሚቆሰቁሱ የሸይጣን እጆች በበዙበት በዚህ ወቅት ከሁላችንም የሚጠበቀው ትዕግሥትና ሰከን ብሎ ነገሮችን በጥሞና መመርመር ነው። የነብዩ መሐመድ (ሰዐወ) ሕይወት አበክሮ እንደሚያስገነዝበን የተመኙትን ለመጨበጥ፣ ከምንም ነገር በላይ ረጋ ብሎ ማሰብን ይጠይቃል። ማሰላሰል እና ትዕግሥት ይጠይቃል። በሐዲሳቸው ላይ እንደተጠቀሰው፣ ጥድፊያ እና ችኮላ ከሸይጣን ሲሆኑ፣ ማሰላሰል እና ትዕግሥት የአላህ ናቸው ብለዋል። በቁርአንም ላይ «አላህ (ሱወ) ታጋሾችን ይወዳል» ተብሎ ተጽፏል። ነቢዩም በሌላ ሐዲሳቸው «ማንም ቢሆን፣ ከትዕግሥት የበለጠና የተሻለ በረከት ሊያገኝ አይችልም» ማለታቸው ተጠቅሷል። የታገሠ ሰው፣ ሥነ ሥርዓት ይኖረዋል። ራሱን ለመመዘንና ሌሎችን ለማየት ጥሞና ይኖረዋል። ነቢዩ መሐመድ (ሰዐወ) ለአንድ ሰዓት ያክል፣ ራስን በጥሞና ማየትና መመዘን 70 ዓመት ከመጸለይ የበለጠ ዋጋ እንዳለው ለተከታዮቻቸው አስተምረዋል። እኛም እንደ ሕዝብ ለውዲቷ አገራችን በጥሞና እንድንጸልይ፣ በሚዛናዊ ምልከታ እንድንራመድ፣ ለመልካምነትና ደግነት ራሳችንን እንድናስገዛ፣ የሸይጣን እጆችን በትዕግስትና በማስተዋል በትር እንድንረታ አበክሬ እጠይቃለሁ።

አገርን መገንባት እጅግ ብርቱ ድካም የሚጠይቅ መሆኑን ሁላችን እንረዳዋለን። በዐረብኛ ‹ከፍ ያለ ቦታ መድረስ የሚፈልግ ቢኖር ብዙ ሺህ ሌሊቶችን ሳይተኛ ማሳለፍ አለበት› የሚል ወርቃማ አባባል አለ። እኛም ከሌሎች አልባሌ ነገሮች ራሳችንን ቆጥበን፣ ዕውቀትና ጉልበታችንን ከፍ ያለ ቦታ ለመድረስ እናውለው። ኢትዮጵያ፣ ገና አሁን ከጦርነት የወጣች አገር ናት። ከዚያ በፊት አንበጣና ኮሮና ጫና አሳርፎብን ነበር። እሱም ሳይበቃ ድርቅ ቁጥሩ ቀላል ያልሆነ ወገናችንን ክፉኛ ጎድቶታል። ብዙ ያጣነው ነገር አለና ስለጎደለብን መታገሥና በርትተን መሥራት እንጂ ተስፋ መቁረጥ የለብንም። መንግሥት የሚችለውን ሁሉ ያደረጋል። እናንተም ለአገር ህልውና ሲሉ የተሠዉ ጀግኖችን ወደ ሕይወት መመለስ ባትችሉ በሕይወት ያሉትን መርዳት፣ ቤተሰባቸውን መደገፍ ይገባችኋል። ስለ መረዳዳት ለሕዝበ ሙስሊሙ ማስረዳት ለቀባሪው እንደ ማርዳት ተደርጎ እንደሚቆጠር ዐውቃለሁ። እናም ሰውን ከሰው ሳትለዩ፣ እከሌ ሙስሊም ነው ክርስቲያን ነው ሳትሉ፣ ከዚህና ከዚያ ወገን ብላችሁ አንዱን ከሌላው ሳትለዩ ዐቅማችሁ የፈቀደውን በማድረግ ለተጎዱ ወገኖቻችን እንድትደርሱላቸው በትኅትና እጠይቃችኋለሁ።

በድርቁም ሆነ በግጭቶች የተሰደዱትን ወገኖቻችንን ወደ ቀዬአቸው እንዲመለሱ እናግዛቸው። ከሥራቸው ለተፈናቀሉ ሥራ እንፍጠርላቸው። ቤት ለወደመባቸው ቤት እንሥራላቸው። ከብቶቻቸው የሞቱባቸውን አርብቶና አርሶ አደሮች እንደ ዐቅማችን እናግዛቸው። እምነት ሳይለያየን ሁላችንም ተባብረን የወደቀ ወገናችንን በማንሣት ለአገርና ለሕዝብ ያለንን ፍቅር ለዓለም እናሳይ። ጠብን በፍቅር ስናሸንፍ፣ ከወደቅንበት ተጋግዘን ለመነሳት ስንጣጣር፣ እንደ አገር አስበን ስናደርግ ሰውም ፈጣሪም ደስ ይሰኛል። ከዒድ እስከ ዒድ፣ ሁላችንንም የሚመለከት የሕዝብ በዓል፣ የአገር በዓል ይሆንልናል። የዚህ በዓል በደመቀ ሁኔታ መከበር፣ የሁላችንም ድምቀት፣ የሁላችንም ክብር እንደሆነ ማወቅ ይገባናል።

**በድጋሚ፣ እንኳን ለታላቁ የዒድ አል ፈጥር በዓል አደረሳችሁ፣ አደረሰን!!**

**ዒድ ሙባረክ!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

**ሚያዝያ 23 ቀን 2014 ዓ.ም.**


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ቢሊየኖች የሚፈሱበት ዓለምአቀፍ የሽቶ ገበያ

**(አቤል ገ/ኪዳን)**

ጠረን ጉልበተኛ ነው። በተለይም የሰውነት ጠረን በስሜትም በአመለካከትም ላይ ያለው ተጽእኖ ቀላል የሚባል አይደለም። ሁሉም ሰው የሚታይ ብቻ ሳይሆን የሚያውድ ውበት እንዲኖረው ይፈልጋል። አይነ ግቡ መሆን ብቻ ሳይሆን ከሩቅ የሚጠራ ጠረን መያዝ የሁሉም ሰው ፍላጎት ነው። ለዚህም ሲባል ሁሉም ሰው መልካም መአዛ ያለውን ነገር በሙሉ ይጠቀማል። ከነዚህ መልካም ጠረን ከሚፈጥሩ ግብአቶች ዋነኛው ሽቶ ነው።

ሽቶ ረዥም ታሪክ ያለው የውበት ግብአት ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ሽቶ መጠቀም የጀመሩት ጥንታውያን ግብጻውያን ናቸው። ሽቶን የሰሩበት ዋነኛ ምክንያት ደግሞ ለአማልክት ለሚያቀርቡት መስዋእት እንዲሆን ነበር። ስለዚህም ሽቶ በቀላሉ የሚገኝ እና ተራው ህዝብ ሁሉ የሚጠቀመው ነገር አልነበረም። ቅድሚያ ለአማልክቱ ፤ ከዚያ ለመኳንንቱ ፤ ከዚያ ለባለጸጎቹ ነው የተፈቀደው።

ቀደምቶቹ ስልጣኔዎች ከሚገበያዩቸው ነገሮች መካከል ዋነኛውም ሽቶ ነው። በተለይ ምስራቃውያኑ የህንድ ፤ የቻይና ፤ የአረብ ስልጣኔዎች በሽቶ ምርት ቀዳሚ ናቸው። ተራውም ህዝብ ቢሆን ግን የራሱን ጠረን የሚያሳምርበት ሽቶ ለማምረት አልሰነፈም።

በየሀገሩ የተለያየ አይነት ህዝባዊ የጠረን ማሳመሪያ ተፈጥሯል። በእኛም ሀገር ሰዎች የሰውነታቸውን ጠረን ለማሳመር የተለያዩ አይነት ግብአቶችን ይጠቀማሉ። ነገር ግን ባህላዊ መዋቢዎች እየቀሩ በፋብሪካ የተመረተ ሽቶ በብዛት ጥቅም ላይ መዋል ከጀመረ ቆይቷል። የሽቶ ገበያውም እየሰፋ እና ተጠቃሚውም እየበረከተ ይገኛል።

በአለም አቀፍ ደረጃ የሽቶ ገበያ ሽቅብ እየተመዘገዘገ ነው። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በአለም አቀፍ ደረጃ ባለፈው የፈረንጆች አመት (2021) በአለም ላይ ለሽቶ ወጪ የተደረገው ገንዘብ መጠን 33 ነጥብ 5 ቢሊየን ዶላር ነው። ይህ አሀዝ ከ2022 እስከ 2027 እ.ኤ.አ በአመት የ6 ነጥብ 7 በመቶ እድገት እስመዘገበ ሄዶ በፈረንጆቹ 2027 በአለም ላይ በአመት ለሽቶ ግዢ ይውላል ተብሎ የሚጠበቀው ገንዘብ 47 ቢሊየን ዶላር ያደርሰዋል ተብሎ ይገመታል።

> **ሽቶ አምራች ድርጅቶች በ2018 ብቻ ያስገቡት ገቢ ከ115 ቢሊየን ዶላር በላይ ሲሆን፣ የሌሎች የፋሽን ምርቶቻቸው ሽያጭ ተቀንሶ በሽቶ ንግድ ብቻ ያስገቡት ገቢ ከ25 ቢሊየን ዶላር በላይ ነው**

ለዚህ እድገት ዋነኛ መነሻው የወጣቶች መበራከት እና የሰዎች የአኗኗር ስልት ወደ ቅንጦት ያዘነበለ መሆን ተጠቃሽ ነው። የሰዎች ኑሮ መሻሻል ፤ የከተሜነት መስፋፋት እና ለጤና እና ውበት የሚሰጡት ትኩረት መጨመር የሽቶ ገበያውን ተፈላጊ እያደረገው እንደሚቀጥልም ነው መረጃዎች የሚያመለክቱት።

ከተለያዩ ተፈጥሯዊ ነገሮች የሚሰራው ሽቶ በስሙ አንድ አይነት ይሁን እንጂ በአይነቱ ግን ብዙ ነው። አንዳኛው ከሌላኛው የሚለዩት በሰውነት ላይ ጠረናቸው በሚቆይበት ሰአት መጠን ሲሆን በአይነትም ዋነኞቹ 5 ናቸው።

እነሱም የመጀመሪያው ፐርፊዩም ወይም ንጹህ ሽቶ የሚባለው ነው። ይህ የሽቶ አይነት የአልኮል መጠኑ ዝቅተኛ የመልካም ጠረን ፈጣሪ ቅመሞቹ ክምችትም ከ20 እስከ 30 በመቶ የሚደርስ ሲሆን ከተቀቡት በኋላም በሰውነት ላይ ጠረኑ እስከ 10 ሰአት የሚቆይ ነው። በተለይም ቆዳቸው ስስ ለሆኑ ሰዎች ይህ ሽቶ የአልኮል መጠኑ አነስተኛ በመሆኑ ይስማማቸዋል።

ሁለተኛው የሽቶ አይነት ዩ ደ ፐርፊዩም የሚባል ሲሆን፣ ይህ አይነቱ ሽቶ የመልካም ጠረን ፈጣሪ ጠረን ፈጣሪ ቅመሞቹ ክምችት ከ15 እስከ 20 በመቶ ብቻ ነው። በተለይ ለልብስ የሚሆን ነው። ለአዘቦት ቀን በተለይ የሚሆነው ይህ ሽቶ ጠረኑ ሳይጠፋ እስከ 8 ሰአት የመቆየት አቅም አለው።

ሶስተኛ ዩ ደ ቶይለት የሚባል ሲሆን ክምችቱ ከ5 እስከ 15 በመቶ ብቻ ነው። ለእለት ተእለት እንቅስቃሴ ጥቅም ላይ የሚውል ነው።

አራተኛው የሽቶ አይነት ኮሎኝ ይባላል። መለያውም ከሌሎቹ ተለቅ ባለ እቃ መመረቱ ነው። ጥሩ ጠረን ለመፍጠር በርከት አድርጎ መቀባትን ይፈልጋል። ጠረን ፈጣሪ ቅመሞቹ ክምችት ከ2 እስከ 5 በመቶ ብቻ ነው። በሰውነት ላይ ቢበዛ ሊቆይ የሚችለው ለ2 ሰአታት ብቻ ነው። የአልኮል መጠኑ ከፍተኛ መሆን ስስ ቆዳ ባላቸው ሰዎች ዘንድ ተመራጭ እንዳይሆን ያደርገዋል። አምስተኛው የሽቶ አይነት ዩ ፍራይች ይባላል። ጠንካራ ጠረን ለማይወዱ ሰዎች ተስማሚ ነው።

ሽቶዎቹ በገበያ ላይ ያላቸው ድርሻ በጠራታቸው ቅደም ተከተል ሲሆን ፣ፐርፊዩም 40 በመቶውን ሽያጭ ይይዛል። በጾታ አንጻር ሲታይ ሴቶች ዋነኛ የሽቶ ሸመቾች ሲሆኑ፣ እስከ 60 በመቶ የሚሆነውን ግዢ የሚፈጽሙት እነሱው ናቸው።

አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፤ በተለይ በምእራቡ አለም ሴቶች በየወሩ በሚባል ደረጃ አዲስ ሽቶ ይገዛሉ፤ ወንዶች በአንጻሩ በአመት አንዴ ወይም ሁለቴ ሽቶ ሊገዙ ቢችሉ ነው። በዚህም የተነሳ የሽቶ አምራቾች ለሴት ደንበኞቻቸው አዳዲስ ምርቶችን በማስተዋወቅ ተጠምደዋል።

አይማርክ ግሩፕ ድረገጽ በኖቬምበር 2019 ባወጣው መረጃ መሰረት ዋነኞቹ የሽቶ አምራቾች በቢሊየን የሚቆጠሩ ዶላሮች የሚያንቀሳቅሱ ሲሆን፣ ዋነኞቹ አምስት ድርጅቶች የሚከተሉት ናቸው። ኤቮን ፕሮዳክትስ ይባላል። መቀመጫውን ለንደን ያደረገው ይህ ድርጅት በ1886 እ.ኤ.አ የተቋቋመ ሲሆን፣ ምርቶቹ እስከ 70 በሚደርሱ አለም ሀገራት ተደራሽ ናቸው።

ከሽቶ ንግድ በተጨማሪ በሌሎች የፋሽን ዘርፎች ላይም የተሰማራው ይህ ድርጅት 23 ሺ ሰራተኞች አሉት፤ በ2018 እ.ኤ.አ ያገኘው አመታዊ ገቢም 5 ነጥብ 5 ቢሊየን ዶላር ገደማ ነው።

መቀመጫውን ፈረንሳይ ያደረገው እና በ1910 እ.ኤ.አ የተቋቋመው ቻኔል ሌላኛው ግዙፍ ሽቶ አምራች ነው። ሽቶን ጨምሮ በርካታ ምርቶችን የሚነግደው ይህ ድርጅት በ2018 ብቻ አመታዊ 11 ቢሊየን ዶላር ገቢ ያገኘ ሲሆን፣ በመላው አለም 25ሺ ሰራተኞች አሉት።

በ1904 ኒውዮርክ ውስጥ የተቋቋመው ኮቲ በ46 ሀገራት ይሰራል፤ 20ሺ ሰራተኞች ቀጣሪው ኮቲ አመታዊ ገቢው በ2018 እ.ኤ.አ ብቻ 9 ነጥብ 4 ቢሊየን ዶላር በላይ ነበር።

ሎሬአል ሌላኛው ግዙፍ የሽቶ አምራች ድርጅት ነው። መቀመጫውን ፈረንሳይ ያደረገው ይህ ድርጅት በ2018 ብቻ አመታዊ ገቢው 30 ቢሊየን ዶላር ገደማ ነበር። በ150 ሀገራት ስፍር ቁጥር የሌላቸው ምርቶቹን የሚያከፋፍለው ሎሬአል 36ሺ ሰራተኞች አሉት።

በእድሜም አንጋፋ በገቢም ከፍተኛ ባለ ብዙ ሰራተኛው የሽቶ አምራች ኤል ቪ ኤም ኤች ይባላል። በ2018 ብቻ 156 ሺ ሰራተኞች እና 4590 ሱቆች የነበሩት ይህ ድርጅት ያስገባው ገቢ 51 ቢሊየን ዶላር ነበር።

እንግዲህ እነዚህ ድርጅቶች በ2018 ብቻ ያስገቡት ገቢ ከ115 ቢሊየን ዶላር በላይ ሲሆን፣ የሌሎች የፋሽን ምርቶቻቸው ሽያጭ ተቀንሶ በሽቶ ንግድ ብቻ ያስገቡት ገቢ ከ25 ቢሊየን ዶላር በላይ ነው።

# ማረፊያ/ትዝብት

## የቀበሌ ቤቶች የቀበሌ ወይስ የተከራይ?

**ይቤ.ከደጃች ውቤ**

በሸገር ያለውን የመኖሪያ ቤት ችግር ሳስብ ሁሌም የሚታሰቡኝ የቀበሌ ቤቶች ናቸው። የስንቱን ቤት አልባ ነዋሪ ገበና የሸፈኑ መሆናቸው፤ የግል ቤት ተከራዮች በቤት ኪራይ የዋጋ ጭማሪና በአከራዮች ባህሪ ሲጠበሱ የቀበሌ ቤት ተከራዮች ተመስገን ብለው ነው የሚኖሩት። ይህን ተመስጌን ማን አየው? ቤቶቹን ሲያስተዳደሩ የነበሩ ያለፉት መንግስታትና እያስተዳደረ ያለው የአሁኑ መንግስትም በእዚህ በኩል ትልቅ ምስጋና ይገባቸዋል።

በቤቶቹ ያለውን ነጻነትና የክፍያ ዝቅተኛነት እያሰቡ የቀበሌ ቤትን የራስ ቤት ብለው የሚጠሩ ተከራዮች ብዙ ናቸው። አንዳንዶች ቤቶቹን የሚያድሱበት እና የሚያጠናክሩበት ሁኔታም ሲታሰብ በእርግጥም የቤታቸው ያህል መመልከታቸውን ነው። ይህ ጥሩ ነው። እነዚህ ቤቶች የከተማ አስተዳደሩ ቢሆኑም የከተማ አስተዳደሩ አደስኳቸው ሲል ተሰምቶም አይታወቅም። ማደስ አይደለም የከተማ አስተዳደሩ ሃላፊዎች ከተማዋ ምን ያህል የቀበሌ ቤቶች ያሏት ስለመሆኑ ወቅታዊ መረጃ ያላቸውም አይመስለኝም።

እርግጥ ነው አሁን አሁን ክረምት ላይ ህዝብንና ድርጅቶችን በማስተባበር የአቅመ ደካማ የቀበሌ ቤቶች እድሳት እየተካሄደ ነው። ከዚህ በመለስ ግን የቀበሌ ቤቶችን ነዋሪዎቹ ናቸው ቤት ያረጓቸው እንጂ ፈርሰው ያልቁም ነበር።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ150 ሺ የቀበሌ ቤቶች ላይ ኦዲት ሊያደርግ መሆኑን በቅርቡ በመገናኛ ብዙሃን ስሰማ ቤቶቹ ቀን ሊወጣላቸው ይሆን እንዴ ስል አሰብኩ። ይህ እርምጃ ከተማ አስተዳደሩ በከተማዋ ምን ያህል የቀበሌ ቤቶች እንዳሉት ሳይሆን እንደቀሩት ለማወቅ ያስችለዋል ብዬም አሰብኩ። እርምጃው ብዙ ቤቶች በመልሶ ልማት፣ በህገወጦች ደብዛቸው ከጠፋ በሁዋላ ይህ መታሰቡ ጅብ ካለፈ ውሻ ጮኸ የሚያሰኝ አይነት ቢሆንም፣ የተረፉትን ቤቶች መታደግ ያስችላልና ጥሩ ጅማር ነው ማለት ይቻላል።

በከተማዋ በአሁኑ ወቅት ይህን ያህል የቀበሌ ቤት መኖሩም ያስገርማል። ብዙ ቤቶች በመልሶ ልማት ፈርሰዋል፤ አንዳንድ ቤቶችም ከሰፋፊ ይዞታቸው ጋር በመንግስት ባለስልጣናት እና ካድሬዎች ደብዛቸው እንዲጠፉ ተደርጓልም ይባላል፤ በይዞታቸው ላይ ህንጻ ተሰርቶ ይዞታቸው የግል ንብረት መደረጉ ሲታሰብ ይህ አህዝ ትልቅ ነው።

የመንግስት እርምጃ ቤቶቹን ኦዲት በማድረግ ብቻ የሚያቆም አይመስለኝም፤ እነዚህ ብዙ ጉድ ታቅፈው የተቀመጡ ቤቶች በእርግጥም የመንግስትና የህዝብ ሀብት መሆናቸውን የሚያሳይ ስራ ሊሰራባቸውም ይችላልና አጀማመሩን ማድነቅ ጥሩ ነው። መቼም ኦዲት ተደርገው ነገሮች አያቆሙም።

ቤቶቹ ያሉበትን ሁኔታ ለተመለከተ የመንግስት ኦዲት ብዙ ጉድ ያወጣል የሚል ግምት መሰንዘር ያስችላል። ቤቶቹ ያሉበት ሁኔታ ሲታሰብ የመንግስት ሳይሆን የግል ይዞታ በሚመስል መልኩ ነው እየተዳደሩ ያሉት። በርካታ የቀበሌ ቤት ተከራዮች ቤቶቹን ሸንሽነው ለንግድና ለመኖሪያ ቤት ካከራዩዋቸው አስተዳዳሪው ቀበሌ ወይም ወረዳ ሳይሆን እነሱ ናቸው ማለት ነው። የቀበሌ ቤት ተከራዮች ቤቶቹ የተጠቀሙትን ያህል በንጉሱ ዘመን ቤቶቹን የገነቡትም ሆኑ የወረሳቸው ደርግና ከዚያም ወዲህ ሲጠቀምባቸው የኖረው መንግስት አልተጠቀሙም።

የሚገርመው ደግሞ ዘመናዊ ቤቶችን ገንብተው የቀበሌ ቤትን ሙጥኝ ብለው የተቀመጡ ፣ ኮንደሚኒየም ደርሷቸው አሳምረው ጨርሰው የሚያከራዩትም ጥቂት የሚባሉ አለመሆናቸው ነው። ቤት ሰርተው ወይም ገዝተው ለቀቁ የሚባሉትን ቁልፉን በሚገርም ዋጋ ሸጠው ነው የሚሄዱት ይባል ነበር። ሌሎች ደግሞ ቤቶቹን በተለይ የንግድ ቤቶችን የተከራዩ ቤቶቹን ሸንሽነው በማከራየት የሚዝቁት ገቢ ሲታሰብ እንዴ ቤቶቹ የማናቸው ያሰኛል። የግል ቤት እያላቸው የኮንደሚኒየም ቤት ተረክበው የሸጡም አሉ ይባላል። ይህ ሁሉ ሲታሰብ የቀበሌ ቤቶች ባለቤት አልነበራቸውም፤ የላቸውምም ያሰኛል።

እነዚህን የቀበሌ ቤቶች ከመንግስት ተከራይተው የሚኖሩ ለኪራይ የሚከፍሉት ዋጋና ዘመኑና ያሉበት አካባቢ የቤት ኪራይ ዋጋ ሲታሰብ ተከራዩቹ ሎተሪ የወጣላቸው ቢባል አይገርምም። ይህ ጥቅም አልበቃ ብሏቸው ነው እንግዲህ የራሳቸውን ቤት ሰርተውም ከእዚያ ቤት የማይለቁት፤ ሸንሽነው በማከራየት የሚጠቀሙት፤ ይሄ ደግሞ እንደ ግል ቤት አከራዮች ዋጋ በየጊዜው የሚጨምሩም ሊሆኑ ይችላሉ። በመንግስት ሀብት ዜጎችን መበደል ምን ይሉታል?

እንደ እኔ እንደ እኔ ቤት መስራት ሳይችሉ ቀርተው በቤቶቹ ብዙ ወግ ማእረግ ያዩ፣ ቤቶቹ ሲለቀቁ በጣም ለተቸገሩ የከተማዋ ነዋሪዎች እየተሰጡ ያሉበት ሁኔታ ሲታሰብ ብቻ ነው ቤቶቹ ትክክለኛ አገልግሎት ላይ መዋላቸውን የሚያመለክተው። ተከራዮች እንደራሳቸው ቤት አርገው አሳምረው የያዙበት ሁኔታም እዚህ ላይ በጥሩ ጎኑ የሚጠቀስ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ ቤቶቹ በንጉሱ ዘመን የተሰሩና አብዛኞቹም የጭቃ ቤቶች ከመሆናቸው አኳያ አብዛኞቹን ማግኘት ባልተቻለም ነበር። ከዚያ በመለስ ያለው የቀበሌ ቤቶች ጉዳይ ብዙ ብዙ የሚያነጋግር ነው።

መቼም የመዲናዋ ጉድና ገመና ተዘርዝሮም ተነግሮም አያልቅም። በመረጃ መረብ የተጠናከረ ሥርዓት የያዘ የነዋሪ መረጃ መኖሩን እጠራጠራለሁ። ለነገሩ ካለው የመልካም አስተዳደር ችግር አንጻር መረጃው ቢኖረም የቀበሌ ሹሞችና ተከራዮች ተመሳጥረው በቀበሌ ቤት ላይ ቁማር ሊጫወቱ አይችሉም ተብሎ አይታሰብም።

ስለቀበሌ ቤቶች ከአንድ አባት ጋር ስናወራ የቀበሌ ቤት ተከራይተው ለግለሰቦች ሸንሽነው ስለሚያከራዩ ሰዎች ህገወጥ ተግባር ሳነሳላቸው እሳቸው ችግሩ ያለው ቀበሌ ወይም ወረዳ ጋ ነው አሉኝ። አሁን ከቀበሌ ወይም ከወረዳ የሚሰወር ምስጢር በዚህች ከተማ አለወይ ሲሉም ጠየቁኝ።

የመኖሪያ ቤት እጥረት የከተማዋ ስር የሰደደ ችግር ሆኖ እያለ በቀበሌ ቤት ውስጥ በነጻ ሊያሰኝ በሚችል መልኩ በርካሽ ኪራይ የኖሩበትን ቤት የራሳቸውን መኖሪያ ቤት ሲሰሩ ለመንግስት እንዲያረክቡ ማድረግ ሲቻል ከቀበሌ ጋር ባለ የጥቅም ትስስር የቀበሌ ቤቱን ሙጥኝ ብለው የሚኖሩ ብዙ መሆናቸው ሲታሰብ የእኚህ አባት በእርግጥም ትክክል ነው።

አዎን የቀበሌ ቤቶቹን ተከራዮች እያከራዩም ቁልፍ እየሸጡም ሲጠቀሙ ቀበሌ ወይም ወረዳ አያውቅም ማለት አይቻልም። ሹሞቹ ወይም ከቤቶች አስተዳደር ጋር ግንኙነት ያላቸው አካላት የሚሰጣቸው እየተሰጣቸው ነው እንዳለየ የሚያልፉት።

አሁን ቤት ሲለቀቅ እንደፊቱ የተመቸ ሁኔታ ያለ አይመስለኝም። የተለቀቀ ቤት መኖር አለመኖሩን ከፍለ ከተማም ጭምር እንዲያውቅ ይደረጋል መሰለኝ፤ በመልሶ ልማት እና በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሳቢያ የቀበሌ ቤቶች ለነዋሪዎች የሚሰጡበት ሁኔታ ስላለ በቤቶቹ ላይ ክትትል ያለ ይመስለኛል።

አሁን ችግር ያለው የራሳቸውን ቤት ሰርተው የቀበሌ ቤቱን መለቀቅ ባለባቸውና ባልቀቁት ላይ እንዲሁም የንግድ ቤቶችን ሸንሽነው የሚያከራዩ ላይ ነው። የመኖሪያ ቤትና የንግድ ቤት እጥረት የከተማዋ ቁልፍ ችግር ሆኖ እያለ በአንዲህ አይነቶቹ ተከራዮች ላይ እርምጃ አለመውሰድ አልፎም ተርፎ አብሮ መስራት የሌላ የማንም ችግር አይደለም ቤቶቹን የማስተዳደር ሃላፊነት የተሰጠው የከተማ አስተዳደሩ ችግር ነው። የራሳቸው ቤት እያላቸው የቀበሌ ቤት ሙጥኝ ብለው የተቀመጡና የቀበሌ የንግድ ቤቶችን ሸንሽነው የሚያከራዩ ላይ አንዳች ዘመቻ መደረግ ያለበት ይመስለኛል። እኔ ከቀበሌ ቤቶች ኦዲቱ በኋላ ብዙ እጠብቃለሁ።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

## የጋራ ሃሳብ ለጋራ ታሪክ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

አለም በአሁኑ ሰአት የተለያየ ርዕዮተ አለምን በሚያራምዱ ሀገራት፣ መንግስታት፣ ግለሰቦች የተሞላች ነች:: የነዚህ ሁሉ የሀሳብ ማረፊያ ደግሞ ሀገርና ህዝብ ናቸው:: ሀገር የምርጥ ሀሳብ ማረፊያ ናት፣ ህዝብ የድንቅ እውነት ስፍራ ነው:: ሀገርና ህዝብ ከነዚህ ጥንድ ሀቆች ሲርቅ ሌላ መልክ ነው የሚይዘው:: ምርጥ ሀሳብ፣ ድንቅ እውነት ሀገር የሚያቆሙ ዋልታና ማገር ናቸው:: የእኛም ሆኑ የአብዛኞቹ ሀገራት አሁናዊ ስቃዮች ከነዚህ የሀሳብ ጅረቶች የሚፈሱ ናቸው:: ሀገርና ትውልድን ማረፊያ ያደረጉ ከግለሰብና ከመንግስት እየፈለቁ ወደ ነገ የሚፈሱ አያሌ ሀሳቦች፣ አያሌ ድርጊቶች አሉ:: እኚህ የሀሳብ መልኮች የእኔና የእናተ አሁናዊ ታሪኮች ናቸው:: መጪውን ከመቃኘት ረገድም የጎላ ድርሻ አላቸው:: ከትናንት ተንከባለው ወደ ዛሬ የመጡ፣ ከዛሬ ተሸቀንጥረው ወደ ነገ ለመሄድ የሚያኮበኩቡ የሀሳብ እንቶፈንቶዎች፤...

ሰው ያለሀገር፣ ሀገር ያለሰው ምንድናቸው ቢባል መልስ አይኖረውም:: ሀገር ያለ ሰው፣ ሰው ያለ ሀገር ባዶ ናቸው:: ለአንዱ ህልውና የአንዱ መኖር ግድ ይለዋል:: ሀገር ያለ ሰው ምድረ በዳ ነው፣ ጋራ ሸንተረሩ፣ ሜዳና ዱሩ ትርጉም አልባ ነው:: አፈሩ፣ ምድሩ፣ ቀዬ፣ አእዋፋቱ ምንም ናቸው:: ሰውም ያለ ሀገር እንዲሁ ነው... ፍቅር ተስፋና እምነት በሀገር የሚበቅሉ የሰውነት ጌጦች ናቸው:: ሰውነት በሀገር፣ ሀገር በሰውነት የተሸመኑ አንድ አይነት መልኮች ናቸው:: በዚህ አንድ አይነት ውስጥ የሚለመልሙ፣ የሚያብቡ፣ የሚያፈሩ የጋራ ታሪኮች አሉ:: በዚህ አንድ አይነት ውስጥ የሚፈጠሩ፣ የሚጎለብቱ የጋራ ባህልና ሥርዓቶች አሉ:: እንደዚሁም ደግሞ ይሄንን የሀገርና የሰውነት መስተጋብር ባለመረዳት የምናበላሻቸው በርካታ ሀገራዊ ታሪኮች ይኖራሉ:: አሁን ላይ እንደ ሀገር የተፈጠሩብን ችግሮች ሰውነትን ከሀገር፣ ሀገርን ከሰውነት የመለያየት ጣጣ የፈጠረው ነው:: የቱ ጋ ነን?

ሀገር ዋጋ የምታወጣው በግለሰቦች የጋራ ህልም ነው:: ግለሰቦች ለየብቻቸው እያለሙ የሚፈጥሯት የጋራ ሀገር የለችም:: አብዛኞቻችን ግራ የተጋባን ነን:: የጋራ ሀገር ከመፍጠር ይልቅ የግል ሀገር ለመፍጠር የምንለፋ ነን:: በጋራ ሀሳብ ከመስማማት ይልቅ የብቻ አጀንዳ ይዘን ለመለያየት የቆምን ነን:: በየትኛውም የሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ለብቻ በመቆም፣ ለብቻ በማሰብ የተፈጠሩ ሀገርና ህዝቦች የሉም:: የጋራ በሆነች አንድ ሀገር ላይ የሚፈጠር የብቻ ህልምና ራዕይ የለም:: እንደ ግለሰብ ከሌላው የተለየ ሀሳብና ህልም ሊኖረን ይችላል በሀገር ጉዳይ ላይ ግን በጋራ ማሰብ፣ በጋራ ማረይ፣ በጋራ መቆም የዜጎች ግዴታ ነው:: ስልጡኖቹ አውሮፓውያን እንዴት ከዘመናዊነት ማማ ላይ እንደተሰቀሉ ብታጤኑ አንድ መልስ ነው የምታገኙት እርሱም...ለጋራ ሀገር በጋራ ማሰብ የሚል እውነት ላይ ትደርሳላችሁ:: ቢገባን ኖሮ ይሄ እውነት አስተማሪያችን ይሆን ነበር:: ለምን ለየብቻ እንደቆምን፣ ለምን ለየብቻ እንደምናስብ፣ ለምን ጎራ እንደለየን መልስ ይሰጠን ነበር::

በእኛ ሀገር የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ መንግስትና ህዝብ አንድ ሆነው አያውቁም:: ባለፉት በርካታ አመታት ውስጥ መንግስት ህዝቡን ሲያስተዳድር የነበረው በሀይል ነበር:: መንግስትና ህዝብ ያልተስማሙባት ሀገር ምን አይነት ትውልድ፣ ምን አይነት ማህበራዊ መስተጋብር እንደሚኖራት መገመት አይከብድም:: አብዛኞቹ ችግሮቻችን በፖለቲካው በኩል የመጡ ናቸው:: አሁን ድረስ ፍዳ እየበላንባቸው ያሉ መከራዎቻችን እነዛ በራስ ወዳድነት የተቃኙ የወየቡ የፖለቲካ ሥርዓቶቻችን የፈጠሩት ናቸው:: አንድ ሀገርና አንድ ህዝብ ያስፈልገናል:: መንግስትን የሚያምን ህዝብ፣ በህዝብ የሚተማመን መንግስት ያስፈልገናል:: እንዲህ ሲሆን የብቻ ህልም አይኖረንም፣ እንዲህ ሲሆን የብቻ ሀገር ለመፍጠር አንለፋም:: እንዲህ ሲሆን ተነጋግሮ መግባባት አይከብደንም:: ለችግሮቻችን እጅ አንሰጥም:: እዚም እዛም የምንሰማቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ችግሮቻችን ያለፈው የፖለቲካ ስርዐት የፈጠራቸው እንደሆኑ እሙን ነው::

> **ሀገር የጋራ ህልም ከሌሳት ምንም ቢሞሳት ዋጋ የለውም፡፡ አሁን ሳይ የወጣት ሀይሳችንን፣ የተፈጥሮ ሀብታችንን፣ እውቀታችንንና ብዙሀነታችንን እንዳንጠቀም ያደረገን የጋራ ህልም አለመኖራችን ነው፡፡ የጋራ ህልም የጋራ ብልጽግና፣ የጋራ ታሪክ ነው፡፡ የጋራ ህልም የጋራ ትውፊት፣ የጋራ ጥቅም ነው፡፡ የክብርና የሞገስ ዘውድ ነው፡፡ የመፈራትና የአንበሳነት ምልክት ነው፡፡ በጋራ ሀገር ሳይ በጋራ አለማሰባችን ይሄን ሁሉ አሳጥቶናል፡፡ ክብርን፣ ሙሳትን አስፈሪነትን ወስዶብናል፡፡ እድገትን፣ ብልጽግናን አሳጥቶናል፡፡ አብዛኞቹ የዓለም ሀገራት ከኋሳችን ተፈጥረው፣ የእኛን ያክል ምንም ሳይኖራቸው አልፈውን የሄዱት ለምን ይመስላችኋል? እውነት ይሄን አስባችሁት ታውቃሳችሁ? የጋራ ህልም ስሳሳቸው ነው**

አሁን ያለው መንግስት እኚህን ትላንትናዊ ችግሮች በመለየትና መፍትሄ በመስጠት በመንግስት ላይ እምነት ያጣውን ህዝብ እንደ አዲስ መፍጠር ይጠበቅበታል:: ያለፉት የፖለቲካ ስርዐቶች የዛሬውን ትውልድ ያሸመደመዱ፣ በሀገር ላይ በርካታ አሉታዊ ችግሮችን የፈጠሩ ናቸው:: እኚህ ችግሮች ከዛሬ ወደ ነገ እንዳይሻገሩ ሁሉን ባቀፈ ሀገራዊ ምክክር እልባት ሊሰጥባቸው ይገባል:: ህዝብና መንግስት የሚግባቡባትን፣ አንድ የሚሆኑባትን ኢትዮጵያ መፍጠር የሁላችንም ግዴታ ነው:: እንዳለፈው ጊዜ በተለያየና በተንሸዋረረ የፖለቲካ ምህዳር የምንፈጥረው ሀገርና ህዝብ የለም:: ያለፈው ጊዜ ምን ይዞልን እንደመጣ ሁላችንም የምናውቀው ነው:: ለፖለቲካ ጥቅም ሲባል፣ ለስልጣን ጥም ሲባል በህዝቦች መካከል መለያየትን የሚፈጥሩ የሀሰት ትርክቶች ሆን ተብለው ሲፈጠሩ ነበር:: ታስቦና ታልሞ በትውልዱ መካከል የጥላቻ ቁርሾ ሲነገር ነበር እኚህ ሁሉ የማስመሰል ድራማዎች ከትላንት ተሻግረው ዛሬም አሉ::

ይሄ ትውልድ እኚህን የጥላቻና የመለያየትን ግድግዳ ማፍረስ አለበት:: ይሄ ትውልድ ከዛሬ ወደ ነገ የሚሻገር የፍቅርና የእርቅ መሰላል መዘርጋት አለበት:: በመንግስት ላይ እምነት ያለው ህዝብ በመፍጠር ረገድ ሀይሉንና ጉልበቱን እውቀቱንም መስዋዕት ማድረግ ይጠበቅበታል:: ኢትዮጵያ ያጣችው ምንድነው? ይሄን ጥያቄ ራሳችሁን ጠይቃችሁት ታውቃላችሁ? ካላወቃችሁ አሁኑኑ ራሳችሁን ጠይቁት...:: ኢትዮጵያ ሀገራችን ያጣችው ምንም የለም:: የወጣት ሀይል አላት፣ በተፈጥሮ የታደለች ናት:: ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ሀብቶቿ ብዙ ናቸው:: አለም የሌለው ብዙ ነገር አላት:: የተማሩ፣ ፊደል የቆጠሩ ሙህራን አላት:: ታሪክ ብትሉ፣ ባህል ስርዐት ብትሉ በሁሉም ሙሉ ናት...አንድ ነገር ግን ጎሎናል:: እርሱም የጋራ ህልም ነው::

ሀገር የጋራ ህልም ከሌላት ምንም ቢሞላት ዋጋ የለውም:: አሁን ላይ የወጣት ሀይላችንን፣ የተፈጥሮ ሀብታችንን፣ እውቀታችንንና ብዙሀነታችንን እንዳንጠቀም ያደረገን የጋራ ህልም አለመኖራችን ነው:: የጋራ ህልም የጋራ ብልጽግና፣ የጋራ ታሪክ ነው:: የጋራ ህልም የጋራ ትውፊት፣ የጋራ ጥቅም ነው:: የክብርና የሞገስ ዘውድ ነው:: የመፈራትና የአንበሳነት ምልክት ነው:: በጋራ ሀገር ላይ በጋራ አለማሰባችን ይሄን ሁሉ አሳጥቶናል:: ክብርን፣ ሙላትን አስፈሪነትን ወስዶብናል:: እድገትን፣ ብልጽግናን አሳጥቶናል:: አብዛኞቹ የዓለም ሀገራት ከኋላችን ተፈጥረው፣ የእኛን ያክል ምንም ሳይኖራቸው አልፈውን የሄዱት ለምን ይመስላችኋል? እውነት ይሄን አስባችሁት ታውቃላችሁ? የጋራ ህልም ስላላቸው ነው:: የጋራ ህልም አንድነትን ይፈጥራል:: ምንምነትን ወደ ሙላት የሚቀይር ሀይል ነው:: አሁንም ቢሆን ወደተውነውና ወደሚጠቅመን የአንድነት ህልም መመለስ አለብን እላለው:: ይሄን ካላደረግን ከዚህም በኋላ የምናባክናቸው በርካታ ሀገራዊ እድሎች ይፈጠራሉ:: ይሄ እንዳይሆን አርነት ወደሚያወጣን፣ ከፍ ወደሚያደርገን የአንድነት ህልም እንመለስ::

ሁሉ ሞልቶን ምንም እንደሌለን መሆናችን ሊያበቃ ይገባል:: በግለኝነት የተጓዝንባቸውን የብቻ ጎዳናዎች መለስ ብለን ብናያቸው ለማንም ያልጠቀሙ ሆነው ነው የምናገኛቸው:: እንደ ሀገር የጋራ ህልም ያስፈልገናል:: የጋራ መንገድ፣ የጋራ እውነት ግድ ይለናል:: የእኔና የእናተ የሀገር ፍቅር የሚለካው ለሀገራችን በምናስበው በጎ ሀሳብ ልክ ነው:: የእኔና የእናተ እውቀትና ማስተዋል ፍሬ የሚያፈራው ከግለኝነት ወጥተን ሁሉን አቃፊ በሆነ ማህበራዊ እውነት ላይ ስንቆም ነው:: ለዘመናት ሳይገባን ባክነናል:: መግባባት እየቻልን ሳንግባባ፣ መለወጥ እየቻልን ሳንለወጥ ወንዝ በማያሻግር የእኔነት አባዜ ተጠፍንገን ባለንበት እየረገጥን ቀመናል:: ይሄ ምንም ካልጠቀመን ወደ ሚጠቅመን መራመድ አለብን:: ወደሚጠቅመን ማማተር አለብን:: የሚጠቅመን ደግሞ እስከዛሬ ያልሄድንበት የአንድነት መንገድ ነው:: የጋራ ሀሳብ ነው:: የጋራ ህልም ነው:: በዚህ እውነት ውስጥ ራሳችንን እንድንፈልገው እንደ አንድ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁላችንንም አደራ እላለው::

ከየትኛውም ጥበብ በላይ ትውልዱ ይቅር ባይነትን መማር አለበት:: ከየትኛውም እውቀት በላይ ዜጎች የአንድነትን መንፈስ ሊረዱት ይገባል:: ከየትኛውም ማስተዋል በላይ መንግስትና ፖለቲከኞች በዛሬ የፖለቲካ ክሽፈት የሚፈጠረውን ነገ አርቀው ማየት አለባቸው እላለው:: ዛሬ ላይ ዋጋ እያስከፈሉን ያሉ ነገሮች እነዛ ትላንትና አርቀን ያላየናቸው ነገሮች ናቸው:: አርቀን ብናይም ሀላፊነት በማይሰማቸውና እኔነት በተጠናወታቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ነው:: ትውልዱ የአባቶቹን ስርዐት ተቀብሎ ለእውነት ማጎብደድ አለበት:: ሀገርና ህዝብን ከሚጎዱ ሀሳቦች፣ ድርጊቶች በመራቅ ለሀገራችን ውለታ መዋል ይጠበቅብናል:: የሀገራችን ኋላ መቅረት ሊሰማን ይገባል:: የህዝባችን ከስልጣኔ መራቅ ሊያመን ይገባል:: ያለ እኛ..ያለ እኔና እናተ ሀገራችን ምንም ናት:: በበለጠ ሀሳብ በልጠን መገኘት ለድሀ ሀገራችን ልንሰጣት የሚገባ የመጨረሻ ስጦታ ነው እላለው:: በጋራ ህልም ወደ ፊት መራመድ ለድሀ ህዝባችን ልንውለው የሚገባ የመጨረሻ ውለታ ነው እላለው::

በጋራ ሀሳብ ላይ ህዝብ ከመንግስት ጋር አንድ አይነት ሀሳብ ማሰብ አለበት:: በጋራ ጉዳይ ላይ ዜጎች አንድ አይነት ህልም ማለም አለበት:: አላማውን ትልቅ ያደረገ ትውልድ ሁሌም ትልቅ ነገር ነው የሚያስበው:: ትልቅ ነገር እንድናገኝ ትልቅ ነገር ማሰብ አለብን:: እስከዛሬ በትንሽ ሀሳብ ትንሽ ሆነን ቆይተናል:: ለመለየየት ሰበብ እየፈለግን፣ ለመገፋፋት መንገድ እየጠረግን ብዙ ጊዜአችንን በከንቱ አባክነናል:: አሁን ጊዜው የእርቅ መሆን አለበት:: በራስ ወዳድነት የቆሸሹ፣ በፖለቲካ ጭቅቅት ያደፉ ታሪኮቻችንን የምናድስበት የምክክር እንዲሆን ሁላችንም የበኩላችንን እንወጣ:: ሀገራዊ ምክክሩ ፍሬ አፍርቶ የሰላምን ፍሬ እስክንበላ ድረስ፣ የአንድነትን ካባ እስክንጎናጸፍ ድረስ የሀገራችን ጉዳይ ያሳስበናል::

ተነጋግሮ እንደመግባባት ጥበብ አለ አልልም:: ተስማምቶ አብሮ እንደመቆም ማስተዋል አለ አልልም:: እኛ ግን ይሄን ማድረግ ከብዶናል:: በዘመናት ታሪክ ውስጥ ተነጋግረን ከተግባባንባቸው ይልቅ ተነጋግረን ጎራ የፈጠርንባቸው ታሪኮቻችን ይበዛሉ:: በጋራ ካሰብነው ይልቅ ለብቻ ቆመን ያሰብነው ይልቃል:: ለምን? ይሄ ጥያቄ አንድ መልስ ነው ያለው..ሁላችንም ራሳችንን ጀግና ማድረግ እንፈልጋለን፣ ባለመስማማት ጦርነት ከፍተን ሀሳባችንን በሀይል ለማሳከት እንጥራለን:: ሳንዋጋና ሳንገዳደል ታሪክ ያለ አይመስለንም፣ ለውጥ የሚመጣ አይመስለንም:: የክፍለ ዘመኑ አስቂኝ ሞኝነት እኔና እናተ በጦርነት ያሳለፍነው ጊዜ ነው:: የክፍለ ዘመኑ የማይደገም አላዋቂነት ተነጋግረን መግባባት እየቻልን በአልሸነፍም ባይነት ጦር የተማዘዝንበት ጊዜ ነው:: በታሪካችን ላይ እንደዚህ ጊዜ ያለ አስነዋሪ ጊዜ አልጻፍንም:: ቢገባን ኖሮ ጀግንነት ያለው ተነጋግሮ በመግናባት ውስጥ ነበር:: ብናውቅ ኖሮ ከብቻ ሀሳብ ይልቅ በጋራ ሀሳብ ውስጥ ነበር ልዕልና ነበር:: በእኛ መስማማት የሚለመልሙ፣ በእኛ አንድ መሆን የሚያፈሩ ታሪኮች ከፊታችን እየጠበቁን ነው:: ለነሱ ስንል የጋራ ህልም እናዳብር::

እስኪ ሁላችንም በአንድ ሀሳብ፣ በአንድ ልብ የጋራ ታሪክ እንጻፍ:: እስኪ ሁላችንም ዘመን የሚሻገር፣ ለትውልድ የሚቆይ የጋራ ሀገር እንፍጠር:: በአንድ ቀለም፣ በአንድ ብዕር ኢትዮጵያ ትቅደም የሚል መፈክር እንከትብ:: ዛሬ..አሁን ለኢትዮጵያ ሰላም፣ ለህዝባችን አንድነት እንትጋ:: ስለሀገራችን ምርጡን የምናስብበት ጊዜ ይሁን::

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የመኸር የግብርና ሥራ ዝግጅትና ያስፈው ተሞክሮ

**ስምስም መንግሥቱ**

የ2013/2014 የመኸር የምርት ዘመን ፣ ቀጥሎ የተከናወነው የመስኖና የበልግ የልማት ሥራ ተጠናቅቆ ለ2014/2015ዓ.ም የመኸር ግብርና ሥራ ከወዲሁ ዝግጅት በሚደረገበት ጊዜ ላይ እንገኛለን:: በተከታታይ የተከናወኑት የግብርና ሥራዎች ከፊታችን ለሚጠብቀን የመኸር የግብርና ሥራ ተሞክሮና ግንዛቤ የሚገኝባቸው እንደሆነ ይታመናል:: በዚህ ወቅት የሰብሉን፣የአትክልትና ፍራፍሬውን፣የእንስሳት ልማቱን ሁሉ አካቶ የሚከናወነው የግብርና ሥራ ይጠበቃል:: እንደሀገርም በግብርና ላይ የተመሰረተውን ኢኮኖሚ ወደላቀ ደረጃ ማሸጋገር የሚቻለው ሁሉም በየአካባቢው በግብርና ሥራው የሚጠበቅበትን መወጣት ሲችል ነው:: ከዚህ አንጻር የኦሮሚያ ክልል ቡኖበደሌ ዞንን የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ከዞኑ ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳዊት ጅፋር ጋር ቃለምልልስ አድርገናል::

**አዲስዘመን፡- የግብርና ሥራ ከፍ ያለ ሀገራዊ የኢኮኖሚ አስተዋጽኦ እንዲኖረው በማድረግ የቡኖበደሌ ዞን በዘርፉ እያከናወነ ስላለው ተግባር ቢገልጹልን ?**

**አቶ ዳዊት፡-** በዞኑ ሁለገብ የግብርና ሥራ ነው የሚከናወነው:: በቡና፣ በአዝርዕት ልማትና በሌሎችም ሰፊ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው:: በቅርቡ በተከናወነው የበጋ ወይንም የቆላ መስኖ ስንዴ ልማት በዞኑ ሰፊ ሥራ ተሰርቷል:: በመስኖ ወደ ስምንት ሺህ ሰባ(8070)ሄክታር መሬት በስንዴ ዘር ለመሸፍን ዕቅድ ተይዞ ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን፣የተከናወነው ግን ከእቅድ በላይ ነው:: 16ሺ ሄክታር መሬት ታርሶ በዘር ተሸፍኗል:: በዘር ከሚሸፈነው መሬትም ከ520ሺ ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ በቅድመ ትንበያ ተይዟል:: እስካሁን በተከናወነው የምርት መሰብሰብ ሥራ ከአምስት መቶሺ ኩንታል በላይ ምርት መሰብሰብ ተችሏል:: ያለፉ የሥራ ተሞክሮዎች መልካም ውጤት ያስገኙ መሆናቸውም በግምገማ ተለይቷል:: አሁን በክረምት ለመኸር የግብርና ሥራ ዝግጅት እያደረግን ነው:: የዝግጅት ሥራው በስልጠና የታገዘ ሲሆን፣ አርሶ አደሩ ቀድሞ ዝግጅት እንዲያደርግ የዞኑ ግብርና ቢሮ በባለሙያዎቹ የክህሎት ሥልጠና እየተሰጠ ይገኛል:: ጎን ለጎንም የንቅናቄ ሥራ እየተከናወነ ነው:: ስልጠናው ባለሙያዎችንም ያካትታል:: የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት ባለሙያውንም የማብቃት ሥራ ይከናወናል:: በዚህ መልኩ የተያዘው ዕቅድ ከተከናወነ በኋላ ሙሉ ለሙሉ ወደ ግብርና ሥራው ይገባል:: የሚታረሰው መሬትም ከወዲሁ እንዲለይ ተደርጓል:: ወደ174ሺ ሄክታር መሬት በተለያየ ሰብል ለመሸፈን ነው በእቅድ የተያዘው:: አሁን ያለው ወቅታዊ የአየርፀባይ በተለይም ዝናቡ ለእርሻ ዝግጅት ተስማሚ ነው:: ቀድመው የማሳ ዝግጅት የጀመሩ አርሶአደሮችም ይገኛሉ::

**አዲስዘመን፡- ከቆላ የበጋ ስንዴ ልማት ጎን ለጎን በመስኖ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትም ሲከናወን እንደቆየ ይታወቃል:: በዚህ ረገድ በቡኖበደሌ ዞን የተከናወነውን ልማት እንዴት ይገለፃል?**

**አቶ ዳዊት፡-** ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት በዞኑ ሁለገብ የግብርና ሥራ ነው የሚከናወነው:: በመሆኑም በማህበር የተደራጁ የአካባቢው ወጣቶች በአትክልትና ፍራፍሬ በተለይም በአቮካዶ ልማት ሰፊ ሥራ ተሰርቷል:: በአሁኑ ወቅትም ዘር የማዳቀል ሥራ እየተከናወነ ሲሆን፣በተለይም በዞኑ ሶስት ወረዳዎች ውስጥ የችግኝ ጣቢያዎች በማፍላት ጭምር ነው ሥራዎች የተከናወኑት:: በነዚህ ችግኝ ጣቢያዎች የሚፈላውን ወይንም የሚዘጋጀውን ችግኝ በ185ሺ ሄክታር መሬት ላይ የአቮካዶ ልማት ለማከናወን መሬቱ በክላስተር ተዘጋጅቷል:: የሙዝ ልማትም በተመሳሳይ ለማከናወን እንቅስቃሴ ተጀምሯል:: በክላስተር የአሰራር ዘዴ ወደ 85ሺ የሙዝ ችግኝ ለመትከል በእቅድ ተይዞ ወደ 60 ሺ ችግኞች ተተክለዋል:: በዘንድሮ አመት በልዩ የትኩረት አቅጣጫ ይዘን እየተንቀሳቀስን ያለው የከተማ ግብርናን ማስፋፋት ነው:: የከተማውን ነዋሪ የአትክልትና ፍራፍሬ ፍላጎት በማሟላት ደረጃ ብዙ ሥራዎች እንደሚጠበቁ ቀድመን በመገምገም የለየነው ሥራ በመሆኑ ትኩረት



አቶ ዳዊት ጂፋር፤

ፎቶ:- ስምስም መንግሥቱ

ሰጥተን እየሰራን እንገኛለን:: የልማት ሥራው ከመከናወኑ በፊትም መሰራት ስላለባቸው የልማት ሥራዎችና ልማቱም በእውቀት እንዲከናወን በስልጠና በማብቃት ነው ወደ ሥራ የተገባው:: በተሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና የከተማው ነዋሪ ባለው ክፍት ቦታ የተለያዩ አትክልቶችን በመትከል ቢያንስ እራሱን ለመመገብ የሚያስችለውን የከተማ ግብርና ሥራ እንዲያከናውን የሚረዳውን ክህሎት እንዲያገኝ ነው የተደረገው::

**አዲስዘመን፡- በዞኑ ሁለገብ የግብርና ሥራ እንደመከናወኑ በእንስሳት ልማት በኩል ያለው እንቅስቃሴ በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል? በተለይም በአሁኑ ጊዜ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች በድርቅ እንስሳት እየተጎዱ በመሆኑ መልሶ የመተካትም ሆነ በዘርፉ ሰፊ ሥራ ይጠበቃል:: ከዚህ አንጻር ምን እየሰራችሁ ነው?**

**አቶ ዳዊት፡-** በእንስሳት ልማት በተለይ ከከተማ ግብርና ልማት ጋር ማያያዝ ይቻላል:: በመሆኑም አመርቂ በሚባል ደረጃ እየተሰራ ነው:: በአርቲፊሻል በማዳቀል ዘዴ እንስሳትን የማራባት ሥራ ተሰርቷል:: እንስሳት የማራባቱ ሥራ መስፋቱ ለወተት ምርት መጨመር ወይንም ከፍ ማለት አስተዋጽኦ ያበረክታል:: በአሁኑ ጊዜ የከተማው ነዋሪ በከተማ ግብርና በተከናወነ የወተት ልማት ነው በመጠቀም ላይ የሚገኘው:: እዚህ ላይ አልሰራንም ወይንም ይቀረናል ብለን በግምገማ የለየነው በዞኑ በደሌ ከተማ ላይ የወተት ማዕከል በማቋቋም ሰፊ ሥራ መሥራት ይቻል እንደነበር ነው:: ምክንያቱም የእንስሳት ሀብቱና የምርት አቅርቦቱ አለ:: አቅርቦቱ በተበታተነ መልኩ ከሚከናወን የወተት ማዕከል ቢቋቋም ለአቅራቢውም ለተጠቀሚውም ምቹ ይሆናል:: ማእከሉ ቢቋቋም ወጣቶችን በማደራጀት እንዲሰሩ ማድረግ ይቻላል:: ልማቱ ለአካባቢው ወጣቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር አስተዋጽኦ ይኖረዋል:: በቢሮ ደረጃም እየተወያየንበት ነው:: ቀጣዩ ስራ በውይይት እንዳይቀር ማድረግ ነው::

ከድርቅ ጋር በተያያዘ ለተነሳው ጥያቄ ሀገራችን ከውስጥም ከውጪም በገጠማት የተለያየ ፈተና በብዙ ችግር ውስጥ እንደሆነች ይታወቃል:: ይህ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ እያጋጠመ ካለው ፈተና ለመውጣት ሥራዎች መሰራት እንዳለባቸው በዞናችን ግንዛቤ ተይዟል።በመሆኑም በዘመናዊ የአረባብ ዘዴ የእንስሳት ሀብትን ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ ነው:: ዞኑ ለእንስሳት፣ለአሳ እርባታና ለንብ ማነብ ምቹ በመሆኑ ከሰብል ልማት ጎን ለጎን ከግብርና ሥራ ጋር ተያያዥ በሆኑት ላይ ሥራዎች ይሰራሉ:: ሥራው ደግሞ ተጀመረ እንጂ ኢትዮጵያ ሀገራችን ከዘርፉ ከምትጠብቀው ውጤት አኳያና ዞኑም በግብርናው ዘርፍ በስፋት ሊከናወን የሚችል ካለው እምቅ ሀብት አኳያ የቤት ሥራ እንደሚጠብቀን እኛም በአመራር ደረጃ ተነጋግረንበት መግባባት ላይ ደርሰን የተሻለ ሥራ ሰርተን ለውጥ ለማምጣት እየተንቀሳቀስን ነው:: እንቅስቃሴው የተለያዩ የግብርና ውጤቶችን ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በማሳደግ አስተዋጽኦ ለማበርከት ነው:: በተለይም የእንስሳት ውጤቶችና የማር ምርትን ለውጭ ገበያ ማቅረብ የሚቻልበት ዕድል አለ:: ከኛ የሚጠበቀው ልማቱን ማዘመን ነው::

**አዲስዘመን፡- ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር አንዱ መንገድ ቴክኖሎጂን መጠቀም ነው:: ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ደግሞ በተለያየ መንገድ ይገለጻል:: ከዚህ አንጻር ያለው ጥረት ምን ይመስላል?**

**አቶ ዳዊት፡-** የግብርና ሥራ በቴክኖሎጂ ሲታገዝ ምርትና ምርታማነት እንደሚያድግ ወይንም እንደሚጨምር ጥያቄ ውስጥ አይገባም:: ከቴክኖሎጂ ግብአቶች አንዱ የክላስተር ወይንም ኩታገጠም የግብርና ዘዴ ነው:: ይህ ዘዴ ምርጥዘር፣ ማዳበሪያ እንዲሁም በመስመር መዝራትና ሌሎች የግብርና ግብአቶችን አጠቃቀም አካቶ የያዘ በመሆኑ ይህን ለመተግበር በትኩረት ይሰራል:: ባለፈው አመት በዚህ የክላስተር ዘዴ ወደ 58ሺ ሄክታር ነበር በክላስተር የተለያየ የሰብል ልማት የተከናወነው።በ2014/2015 የመኸር የምርት ዘመን ሄክታሩን በእጥፍ በማሳደግ በስምንት ሰብሎች ላይ በክላስተር ለማምረት አቅደን እየሰራን ነው:: ምርታማነትን ከመጨመር አንጻር አስተዋጽኦው ከፍ ያለ በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶታል:: ለአርሶአደሩም ግንዛቤ እየተሰጠ ያለው በዚህ ደረጃ ነው::

**አዲስዘመን፡- በዚህ ወቅት እንደተግዳሮት እየተነሳ ያለው የማዳበሪያ አቅርቦት ነው:: ዞኑ ይሄን በምን መልኩ ሲፈታው አስባል?**

**አቶ ዳዊት፡-** እንደሀገር ባጋጠመው የውጭ ምንዛሪ እጥረትና የዓለም የማዳበሪያ ዋጋ መናር የተነሳ አቅርቦቱ ቀደም ሲል እንደበረው ሊሆን እንደማይችል ይጠበቃል:: በመሆኑም በጉዳዩ ላይ በክልል ደረጃ እንደ አቅጣጫ ተይዞ የተፈጥሮ ማዳበሪያ የማዘጋጀት ሥራ እንዲጠናከር ተደርጓል:: የተፈጥሮ ማዳበሪያ የአፈር ለምነትን በማስተካከልና በመጠበቅ ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው:: የማዳበሪያ አቅርቦትን ሙሉ ለሙሉ ይተካል የሚል እምነት ባይኖርም አማራጭ ዘዴ በመጠቀም ችግሩን መፍታት የግድ ነው:: የተፈጥሮ ማዳበሪያን ከማዘጋጀት ጎን ለጎን የማዳበሪያ አቅርቦትንም ለማመቻቸት ጥረት እየተደረገ ነው። ዞኑ 135ሺ ኩንታል ማዳበሪየ እንዲቀርብ ለክልል ጥያቄ አቅርበናል:: ከቀረበው ጥያቄ ውስጥ ወደ 33ሺ ኩንታል ማዳበሪያ ገብቷል:: ቀሪው መቅረብ ካልቻለ በተፈጥሮ ማዳበሪያ በማካካስ የግብርና ሥራው ይከናወናል:: ሌላው ተግዳሮት የበቆሎ ዘር እጥረት ነው:: በተለይም ፓይነር የሚባል የዘር አይነት ከጠየቅነው ዘር አንድ ሶስተኛ የሚሆነው እንኳን አልደረሰንም:: ሌሎች ምርጥ ዘሮች ላይ ችግር አልገጠመንም::

**አዲስዘመን፡- በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በተከፈተው ጦርነት ምክንያት በግብርና ሥራው ላይ የባከነ ጊዜ መኖሩ ይታወቃልና ይህንን በሚያካክስ ሥራ መሰራት አለበት:: ከዚህ አንጻር ያላችሁ ዝግጁነትስ ምን ይመስላል?**

**አቶ ዳዊት፡-** እውነት ነው ብዙ የባከኑ ጊዜዎች አሉ:: ስለዚህ የተለያየ አቅጣጫዎችን ይዞ ነው በግብርና ሥራው ላይ እየሰራን የምንገኘው:: ዞናችን የሰላም ዞን ነው:: እንደ አመራርም፣እንደ ባለሙያና አርሶአደር በተለያዩ አካባቢዎች በግብርና የባከኑትን የመሸፈን ተግባር ለማከናወን ነው ያቀድነው:: ድርብርብ ተልዕኮዎችንና ኃላፊነቶችን ይዘን እየተንቀሳቀስን መሆናችንን አርሶአደሩም ያውቃል:: በመሆኑም አመራሩና አርሶአደሩ እጅ ለእጅ ተያይዞ ለልማት ዕድገት ተነሳስቷል ማለት ይቻላል::

**አዲስዘመን፡- ዞኑ በሚያከናውነው የግብርና ሥራ ዋና ዋና ብሎ የሚለያቸው ምርቶች እሉ?**

**አቶ ዳዊት፡-** ከዋና ዋና ምርቶቹ የቡና ምርት ይጠቀሳል:: በቆሎም ከሌላው ሰብል በስፋት ይመረታል:: በክላስተር የአመራረት ዘዴ የበቆሎ ምርት ከአንድ ሄክታር በአማካይ እስከ 50 ኩንታል፣ከፍ ሲል ደግሞ እስከ አንድ መቶ ኩንታል ምርት ይገኛል:: ከምርታማነት አንጻር በአንድ ሄክታር እስከ አምስት ኩንታል ነው የጨመረው:: ማሽላ፣ጤፍ፣ጥራጥሬና የቅባት እህሎች በቅደም ተከተል ይገለጻሉ:: በተጨማሪም አትክልትና ፍራፍሬ ናቸው::

**አዲስዘመን፡-** ምርትና ምርታማነትን ካደገ በኋላ ገበያ ላይ ወጥቶ አርሶአደሩን፣አካባቢውንና ሀገርን ተጠቃሚ ማድረግ ይኖርበታል:: የገበያ ትስስሩስ ምን ይመስላል?

**አቶ ዳዊት፡-** አምራቹና ተጠቃሚው እንዳይገናኝ ትልቁን ችግር እየፈጠረ ያለው በመካከል ላይ ሆኖ የሚደልለው ነው:: በመሆኑም ችግሩ ሰው ሰራሽ ነው:: ይህን ለመቅረፍ የሰንበት ገበያ ተጀምሯል:: ይህ በመጠኑም ቢሆን ያቃልላል ተብሎ ይታመናል:: አርሶአደሩን ንግዱን ከሚመራ የመንግሥት ተቋማት ጋር በማስተሳሰር ከሸማቹ ጋር በቀጥታ እንዲገበያይ ጥረት እየተደረገ ነው:: በዞኑም ኤግዚቢሽንና ባዛር በሚል ሸማቹን ከአርሶአደሩ ጋር የሚያገናኝ ሥራ ተጀምሯል:: ጅምሩም ያበረታታል:: አጠናክረን በመቀጠል ለውጥ እንዲመጣ ጥረት እናደርጋለን::

**አዲስዘመን፡- ስነበረንቆይታ እናመሰግናለን::**

**አቶ ዳዊት፡-** እኔም አመሰግናለሁ::

ማህበራዊ
# አስኳላ

# ወሰኑ እስከ መጻሕፍት ልገሳ የዘለቀው ኢትዮጵያዊ እሴት

ግርማ መንግሥቴ

እጅ ልገሳ ለኢትዮጵያዊያን እሴት ነው። ይህን ማለት የተቻለው መረዳዳት፣ መደጋገፍ፣ ያለው ለሌለው ... ወዘተ ቢባልም፤ ሄዶ ሄዶ ሊሆን የሚችለው "እጅ ልገሳ" በመሆኑ ነው።

"እጅ ልገሳ" ያው ልክ እንደ "ደም ልገሳ" ሁሉ፤ እጅን ለተሻለና አጋዥ ለሆነ ተግባር "ማዋስ" ማለት ነው። ይህ በዘይቤያዊ አገላለፅ የተከሸነው "እጅ ልገሳ"፣ ልክ "እጅህን አውሰኝ" (አግዘኝ ለማለት) ሁሉ፣ ግለሰቦች በግልም ይሁን በጋራ የሚያደርጉትን መልካም ነገር (በተለይም ስጦታ) የሚመለከት እና የሚያመለክት ሲሆን፤ ከደራሲያን አኳያም የሚዘወተርና "ሀንድቡክ" የሚል ርእስን ይዘው ለንባብ በሚበቁ መጻሕፍት የሚስተዋል ነው።

ይህ፣ "እጅ ልገሳ ለኢትዮጵያዊያን እሴት ነው" የሚለው፣ ጥናት ያረጋገጠው፤ መረጃና ማስረጃ ያለው ድምዳሜ ቢመስልም/ባይመስልም ኢትዮጵያዊነታችን በራሱ የሚነግረን እውነት ነውና ክርክሩም ሆነ እሰጥ አገባው ውሀ አይቋጥርም ማለት ነው።

ሰሞኑን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በቅጥር ግቢው ውስጥ "በአምስት ቀን አምስት ሺህ መጻሕፍት" በሚል መሪ ቃል ከሚያዝያ 10 ጀምሮ አምስት ቀናትን የዘለቀ መጻሕፍት የማሰባሰብ ስራን ሲያከናውን ቆይቶ ከእቅዱ በላይ በሄደ ስኬት የ"የመጻሕፍት ልገሳ" መርሀ ግብሩን አጠናቅቋል። ሚያዝያ 18 2014 ኢ.ም ለሚመለከተው፣ ለተሰበሰበለት አካል በደማቅ ስነስርአት አከናውኗል። ዛሬ በዚሁና ከዚሁ ጋር በተረያያዘ ሀሳብ እንለዋወጥ ዘንድ፤ ልምዱ ለብዙዎች ይዳረስ ዘንድ ተፈልጓልና መልካም ንባብ እንላለን።

በአገራችን በ"እጥረት" ከተያዙት፤ በ"ክፍተት" ከሚታዩት ... መሰረታዊ ሰብአዊ ጉዳዮች መካከል መጻሕፍት ከቀዳሚዎቹ ተርታ ይገኛሉ። በተለይ "ቤተ መጻሕፍት የሌላቸው የትምህርት ተቋማት በብዛት አሉ" መባልን ለሰማ ጉዳዩ ያስደነግጣል።

በመሆኑም፣ ይህን የመጻሕፍት እጥረት ለማስወገድ፣ ይህን ክፍተት ለመሙላት፤ ይህንን የመጻሕፍት (እና የአንባቢ እጥረት) ድርቅ ለመቋቋም ... የተለያዩ ተቋማት የየራሳቸውን የእጥረት አወጋገድ፣ ክፍተት አሞላል .... ዘዴን ተጠቅመው ለችግሩ መፍትሄን በማፈላለግ ላይ ይገኛሉ። ከዘዴዎቹም አንዱ እየተነጋገርንበት ያለው የ"እጅ ልገሳ"ው ዘዴ ነው። "የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአንጋፋ ደራስያኑ ስም ያሰባሰባቸውን 5 ሺህ መጻሕፍት ለአብርሆት ቤተመጻሕፍት አስረከበ" የሚለው የሰሞኑ ዜናም ከዚሁ አኳያ ብቻ ሳይሆን በዚህ ተግባር ከፊር ቀዳጅነቱም አንፃር ሊታይ የሚገባው ነው።

ሚዲያዎች በተደጋጋሚና በስፋት እንደሄዱበት፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአንጋፋ ደራስያኑ ስም ያሰባሰባቸውን ከአምስት ሺህ በላይ መጽሐፍት ለአብርሆት ቤተመጻሕፍት አስረክቧል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጌትነት ታደሰ በርክክቡ ላይ እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በተቋሙ ስር በተለያየ ጊዜ ሲጽፉ በነበሩ ደራስያን ስም አምስት ሺህ መጻሕፍትን በአምስት ቀን ለማሰባሰብ የተለያዩ ጥረቶች ሲያደርግ የነበረ ሲሆን (10ሺህ መጻሕፍት ለማሰባሰብ የሚያስችለውን መርሀ ግብር አዘጋጅቶ ሁለተኛውን ዙር ጀምሯል)፤ ዓላማውን የተረዱ ጋዜጠኞች፣ የጥበብ ወዳጆች ከአዲስ አበባና ከተለያዩ ከተሞች መጻሕፍቶቻቸውን ለግሰዋል።

በድርጅቱ ስራ ሀላፊዎች ሲገለፅ እንደተሰማውና ህዝብም እንደሚያውቀው ለ81 ዓመታት ሕዝብን ሲያስተምር የቆየው አንጋፋው የሚዲያ ተቋም የጀመረውን መጻሕፍት የማሰባሰብ ጥረት ይቀጥላል። "ዕድሜ ልክ" በሚል ስያሜ፤ "የ81 ዓመታት የየዓመቱ 100 ምርጥ መጻሕፍት" በተሰኘ መርሐግብርም ተመሳሳይ የመጻሕፍ ማሰባሰብ ሥራ ይከናወናል። የእጅ ልገሳው ተግባር ይቀጥላል ማለት ነው።

አብርሆት ቤተ መጻሕፍ ምቹ የማንበቢያና ዕውቀት መገብያ ስፍራ መሆኑን ለተመለከተ፤ ዕውቀት እንዲስፋፋ በተለያዩ ሥፍራዎች ላይ መጻሕፍትንና መጻሕፍት ቤቶችን ማስፋፋት እንደሚያስፈልግ በቀላሉ ይረዳል። "እኛም ለአንባብያን የሚሆኑ መጻሕፍትን በማሰባሰብ ለማበርከት ስንነሳ አገር ለመገንባት ወሳኝ የሆነው ዕውቀት እንዲስፋፋ በማሰብ ነው። ይህ ጥረታችንም ተጠናክሮ ይቀጥላል።" ከሚለው በተጨማሪ ከሃገር አቀፉ የአንድ ሚሊዮን መጻሕፍት የማሰባሰብ ጥረት ጋር በተያያዘም ተቋሙ የሚያከናውናቸው ሰፋፊ ሥራዎች እንደሚኖሩ መነገሩም የዚሁ የእጅ ልገሳው አካልና አምሳል ነውና ዘመኑ የንባብና እውቀት ዘመን ነው ቢባል ያስኬዳል።

በሃገር አቀፍ ደረጃ ከሚያዚያ 28 ቀን እስከ ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ አንድ ሚሊዮን መጻሕፍትን ለአብርሖት ቤተመጻሕፍት ለማሰባሰብ ዝግጅቱ በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን በርክክቡ ወቅት ሙዓዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ማስታወቃቸውም እየተነጋገርንበት ያለውን ሀሳብ የሚያጠናክርልን ነውና የኢትዮጵያዊያን የእጅ ልገሳ እሴት ይቀጥላል ማለት ነው።

መጻሕፍት ዕውቀትና ስልጣኔን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ወሳኝ ናቸው። የሃገራችንን ችግሮች መቅረፍ ከምንችልባቸው መንገዶች አንዱ ዕውቀት ነው። በዚህ ረገድ የአብርሖት ቤተመጻሕፍት ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፤ የቤተመጻሕፍቱ ዓላማም የዕውቀት ማዕከል ሆኖ ማገልገል መሆኑ የተነገረውም ከዚሁ አኳያ የሚታይ ነው።

እንደ ዲያቆን ዳንኤል ክብረት አስተያየት ከምግብ እጥረት እኩል በዚህች ሃገር ችግር እየፈጠረ ያለው የዕውቀት እጥረት ነው። በዚህ ደግሞ ከዚህ ጸሐፊ ጀምሮ በርካቶች ይስማማሉ። ይህ ደግሞ የመጻሕፍትና የቤተመጻሕፍት አቅርቦት በየአካባቢው እንደሚያስፈልግ በግልፅ የሚያሳይ ጉዳይ ነው። ዲያቆኑ "የዕውቀት እጥረት ልክ እንደምግብ እጥረት ሁሉ መፍትሔ ያሻዋል። የምግብ እጥረቱን በቫይታሚንና በፕሮቲንም መቅረፍ እንደሚቻው ሁሉ በሃገር ላይ ችግር እየፈጠረ ያለውን የዕውቀት ችግር ለመቅረፍ ደግሞ መጻሕፍት ወሳኝ ናቸው" ማለታቸውንም ስለትክክለኛነቱ ሲባል እዚህ መጥቀስ ያስፈልጋል።

ከዚህና ሌሎች ጉዳዮች አኳያ እንግዲህ በዚህ ጉዳይ ፊር ቀዳጁን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በተቋሙ በሰሩ አንጋፋ ደራስያን ስም መጻሕፍትን አሰባስቦ ለአብርሖት ማስረከቡ የሚያስመሰግነው። ከየአቅጣጫው "የሃገራችን ሚዲያዎች ሰዎች መጻሕፍትን እንዲያሰባስቡና እንዴት መሰብሰብ እንደሚቻል እያስተማሩ ያሉበት መንገድ የሚደነቅ ነው። በተመሳሳይ በየመሥሪያ ቤቱና በየቤቱ የተቀመጡ መጻሕፍትን ወደ ቤተመጻሕፍት ማምጣት ያስፈልጋል" የሚል አስተያየት ለድርጅቱ መሰጠቱም ከእውቀት መስፋፋትና ትውልድ ግንባታ ጋር በተያያዘ ሊታይ የሚገባው እንጂ ለድርጅቱ ብቻ የተሰጠ አስተያየት ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው አይደለም።

ከላይ በገለፅነው የርክክብ ስነስርአት ላይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሃና ተገኝተው ነበር። እሳቸው እንዳሉት ገና ካሁኑ አብርሆት ቤተመጻሕፍትን በየቀኑ ከሶስት እስከ አምስት ሺህ ሰዎች ለንባብ እየጎበኙት ነው። ይህም በአገራችን ያለው የቤተመጻሕፍትና የመጻሕፍት እጥረት ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል። ሕዝብም የማንበብ ፍላጎቱ ምን ያክል እንደጨመረ ያመላክታል። በመሆኑም ከሕዝቡ ቁጥር ጋር የሚመጣጠን የንባብ ባህልን ለማዳበር እንደ አብርሆት ያሉ ቤተመጻሕፍትን በየክፍለ ከተማው መገንባት ይጠበቃል።

በአገር አቀፍ ደረጃ በአንድ ወር ውስጥ አንድ ሚሊዮን መጻሕፍትን ለማሰባሰብ የተያዘው ዕቅድም የቤተመጻሕፍቱን አቅም በማሳደግ ረገድ ትልቅ ሚና እንደሚኖረው፤ አብርሆት ቤተመጻሕፍት አራት ሚሊዮን መጻሕፍት የመያዝ አቅም እንዳለው፤ ቤተመጻሕፍቱ ውስጥ ቢያንስ ሁለት ኮፒ ያላቸው ሁለት ሚሊዮን መጻሕፍት እንደሚያስፈልጉ፤ በዚህ ረገድ የተለያዩ ግለሰቦችና ተቋማት መጻሕፍት በማሰባሰብ ረገድ እያደረጉ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም አምስት ሺህ መጻሕፍትን መለገሱ በሂደቱ አርዓያ እንደሆነ፤ በአንድ ወር ውስጥ አንድ ሚሊዮን መጽሐፍትን ለማሰባሰብ በሚደረገው ጥረት ዜጎች የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሊያደርጉ እንደሚገባ ነው ፕሮፌሰሩ በርክክብ ስነስርአቱ ላይ የተናገሩት። ይህም የኢትዮጵያዊያን የእጅ ልገሳ እሴት ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት መሆኑን በሚገባ የሚያሳስብ ሆኖ ነው የምናገኘው።

ለዚሁ ቤተመጻሕፍት "ሚሊዮን መጻሕፍት ለሚሊኒየሙ ትውልድ" በሚል መሪ ሃሳብ ለአንድ ወር የሚቆይ አንድ ሚሊዮን መጻሕፍትን የማሰባሰብ ዘመቻው ከዚሁ አገራዊና ትውልዳዊ ፋይዳው አኳያ ሲታይ መሆን ያለበት ብቻ ሳይሆንየዘገየ ሁሉ የሚያስብል ነውና ለእጅ ልገሳው አንድ እራሱን የቻለ ገፊ ምክንያ ነው ማለት ነው።

የመጻሕፍት አሰባሳቢ ኮሚቴው ሚያዝያ 21 2014 ኢ.ም በቤተ መጻሕፍቱ አዳራሽ በሰጠው መግለጫ፤ የመጻሕፍት መሰባሰብ ዓላማው፤ ለአብርሖት ቤተ መጻሕፍት የሚሆኑ መጻሕፍትን በአይነትና በብዛት ማሰባሰብ፤ ለሌሎች ክልሎችና ከተማዎች ለሚገኙ አብያተ መጻሕፍት ለመለገስ፤ እንዲሁም የንባብ ባህልን በማዳበር አንባቢና አሰላሳይ ትውልድ እንዲፈጠር ለማበረታታት እንደሆነ አስታውቋል።

ይህ ለአንድ አገር ህዝብ ከ"የእናት አገር ጥሪ" የሚተናነስ አይደለምና እጅ ልገሳው ሊቀጥል ይገባል።

በዚሁ ስነስርአት ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሳው፤ ዕውቀት መር ማህበረሰብ ለመገንባት እውቀት የሚሸጋገርባቸው መንገዶችን ማሳለጥ ያስፈልጋል፤ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ መጻሕፍት ዋነኞች መሆናቸውን፤ ኢትዮጵያዊያን ፊደል ቀርጸው፣ ብራና ፍቀውና ቀለም በጥብጠው፣ ከድንጋይ ዘመን እስከ ወረቀት ዘመን እውቀትን ለማስተላለፍ የተጉ እንደ ነበሩ፤ ይህም መቀጠል ያለበት ስለ መሆኑ፤ በዚህ የፊደል ቀረጻና የእውቀት ምርት ያላቸውን ቦታ ያህል ከታሪካቸው፣ ከቋንቋና ባህል ብዝኃነታቸው ከህዝብ ቁጥራቸው ጋር የሚመጣጠኑ አብያት መጻሕፍት እንደሌሉ መናገራቸው፤ ይህም እውቀት መር የሆነ ማህበረሰብ ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት ማጓተቱትን፤ ይሄንን ችግር ለመፍታት ከዛሬ 75 ዓመታት ጀምሮ ዘመናዊ አብያተ መጻህፍትን ለመገንባት ጥረት ሲደረግ መቆየቱን፤ ነገር ግን የህዝቡን ቁጥር፣ ብዝኃነትና የሥነ ጽሁፍ ሀብት የሚመጥን አለመሆኑን መግለፃቸው ብዙ የሚለው ነገር አለና በእጅ ልገሳው ተግባር ወደ ኋላ ማለት ይከብዳል።

የአብርኖት ቤተ መጻሕፍት፤ እውቀት መርና አመክንዮአዊ የሆነ ትውልድ ለመገንባት፣ ከግንባታው ጀምሮ በያዛቸው አካላዊና ዲጂታል መጻህፍት ድረስ ወደ ፊት ለሚገነቡ አብያተ መጻሕፍት አርአያ እንዲሆንና ለሌሎች አብያተ መጻሕፍት ማሠራጫ ማዕከል እንዲሆን ለማስቻል እንደተገነባ ከዚህ በፊሪት በዚሁና ሌሎች የጋዜጣው አምዶች ላይ መግለፃችን የሚታወስ ነው። በመሆኑም፣ ይህን ቤተ መጻሕፍት ለኢትዮጵያውያን በሚጠቅሙ አካላዊና ዲጂታል መጻሕፍት ለማሟላት እየተሰራ ያለውም ሆነ ሊሰረታ የታሰበው ስራ በእጅጉ የሚበረታታ ነውና ሁሉም በእጅ ልገሳው ተግባር እዚህ ልማት ውስጥ እጁን ሊያስገባ ይገባል ስንል ዝም ብለን አይደለም።

ከሚያዚያ 28 እስከ ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም አንድ ሚሊዮን መጻሕፍት እንደሚሰበሰቡ፤ ይህም የሚከናወነው በአብርኖት ቤተ መጻሕፍት ውስጥ እንደሆነ መነገሩ፤ ለሥራው መሳካት የፌዴሬሽንና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ ተጠሪ ተቋማት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ የንግዱ ማህበረሰብ፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የትምህርት ተቋማት፣ የህክምና ተቋማት፣ የኮንስትራክሽን ተቋማት፣ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን፣ ተቀማጭነታቸው ኢትዮጵያ የሆኑ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ አባላት፣ የሚዲያ ተቋማት፣ የመከላከያና የፖሊስ ሠራዊት፣ ተማሪዎች፣ ነጋዴዎች፣ አርሶና አርብቶ አደሮች፣ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች፣ ደራሲያን፣ አሳታሚዎችና ማተሚያ ቤቶች፣ የታክሲና የረጅም ርቀት ሹፌሮችና ረዳቶች፣ ሊስትሮዎች፣ የቀን ሠራተኞችና ሌሎችም በልዩ ልዩ የኢትዮጵያና የውጭ ቋንቋዎች የተጻፉ እንዲሁም ልዩ ልዩ የእውቀት ዘርፎችን የሚያስረዱ መጻሕፍትን በመለገሥ አሻራቸውን ለትውልድ እንዲያቆዩ በአስተባባሪዎቹ በኩል ጥሪ መቅረቡ ሌላ ሳይሆን ጉዳዩ የጋራ መሆኑን ከማመላከት ባሻገር የ"ኑ፣ እጅ ለግሱ"፤ ወይም፣ ከላይ እንዳልነው ትውልድን የመታደግና የነቃ ማህበረሰብ (Civil society)ን የመፍጠር "የእናት አገር ጥሪ" ስለ መሆኑ ምንም አይነት የሚያሻማ ነገር የለውም።

በእለቱ አስተባባሪዎቹ ዜጎች ራሳቸውን በእውቀት እንዲያጎለብቱ አብርኖት ቤተ መጻሕፍት ትልቅ ሚና እንደሚኖረው መግለፃቸው፤ በአሁን ወቅት በመጻህፍት ቤቱ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የኤሌክትሮኒክስ መጻህፍት ከምችት እንዳለ መነገሩ ተስፋ ሰጪ ነው።

በአንድ ወር አንድ ሚሊዮን መጻሕፍት ለመሰብሰብ በተጀመረው ተግባር ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት፣ ከአዲስ አበባ ባህል፣ ቱሪዝምና ኪነ ጥበብ ቢሮ፣ ከኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ከአዲስ አበባ ኮሙኒኬሽን ቢሮ የተወጣጡ አካላት በኮሚቴ ተዋቅረው እየሰሩ እንደሚገኙ የተገለፀ ሲሆን፤ ሁሉም፣ አቅሙ የፈቀደለት በሙሉ፣ የኢትዮጵያዊያንን የእጅ ልገሳ እሴት በማስቀጠል አብርኖት ቤተ መጻሕፍትን ምሉእ በኩለሄ ማድረጉ ላይ ሊረባረብ ይገባል።



# “ሲቃወምም ሆነ ሲደግፍ ምክንያታዊ የሆነ የከተማ ነዋሪ ለማፍራት እየተሰራ ነው”

**– አቶ አበራ መኮንን የደብረብርሃን ከተማ የሰላምና ህዝብ ደህንነት መምሪያ ኃላፊ**

**ዕፀገነት አክሊሉ**

የደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን የምትገኝና በመካከለኛ ከተማ አስተዳደር ደረጃ ያለች ስትሆን፣ ከክልሉ ርዕሰ ከተማ ባሕር ዳር 695 ኪሎ ሜትር፤ ከፌዴራሉ ከተማ አዲስ አበባ ደግሞ 130 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። ከተማዋ ከባሕር ጠለል በላይ 2ሺ 700 ሜትር ከፍታ ላይ ትገኛለች።

የከተማዋ ስፋት 18ሺ ሄክታር መሬት የሚሸፍን ሲሆን፣ በከተማው ፕላን የተካተተው ከማስፋፊያው ውጭ 5ሺ 711 ሄክታር ይሸፍናል። የቦታውም አቀማመጥ 86 በመቶ ሜዳማ፤ 10 በመቶ ዳገታማ፣ አራት በመቶ ተራራማ የሆነ እና ከዚህም ውስጥ 95 በመቶ ለግንባታ ምቹ የሆነ ቦታ ነው።

የከተማዋን አየር ንብረት ስንመለከትም በቀዝቃዛማ አየር ንብረት ብትታወቅም አሁን ላይ ቀዝቃዛነቱ እየቀነሰ የመጣ፤ በአማካይ 14 ነጥብ 5 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሙቀትና 964 ሚሊ ሜትር አመታዊ የዝናብ መጠን ያላት ከተማ ነች።

ከአስተዳደራዊ አደረጃጀት አንጻር ሲታይም ከተማዋ በዘጠኝ የከተማና በአምስት የገጠር ቀበሌ አስተዳደርና በ19 ሴክተር መስሪያ ቤቶች ተዋቅራለች።

የከተማው ህዝብ የተሰማራበት የሥራ መስክ በአብዛኛው በንግድና በግብርና ሲሆን ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ኢንዱስትሪዎች እየተመሙባት የምትገኝ ከተማ እንደሆነች መረጃዎች ያመለክታሉ።

የደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽህፈት ቤት እንደሚገልጸው ከተማዋ ለአዲስ አበባ ካላት ቅርበት፤ ምቹ አየር ንብረት፤ ሠላማዊና ሥራ ወዳድ ሕዝብ የሚኖርባት ከተማ በመሆኗ ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ በከፍተኛ ደረጃ በኢንቨስተሮች ተፈላጊ ከተማ ለመሆን ችላለች ።

እስከ 2012 ዓ.ም በጀት ዓመት መጨረሻ ብቻ በ504 ባለሀብቶች 31 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር ያህል ኢንቨስት እንዳደረጉም መረጃው ያመለክታል ።

ኢንቨስትመንቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ሌሎች ባለሀብቶች ወደ ከተማዋ በብዛት መምጣት እንዲችሉ መስተዳድሩ ከምንጊዜውም በላይ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት በቅንነት በመስጠት ረገድ ከፍተኛ ሥራ እየሠራ ከመሆኑም በላይ የከተማዋን ሰላምና ጸጥታ ለማስጠበቅ ሰፋፊ ስራዎች እየተከናወኑ ነው።

ኢንቨስትመንቱ ቀጣይነት እንዲኖረው ለበርካታ ዓመታት ሲጓተት የነበረው የመሠረተ ልማት አገልግሎት ባለፉት ጥቂት ዓመታት ብቻ አዳዲስ የምስረታ ሠፈሮችን ከነባሩ ሠፈር ጋር ለማገናኘት የመሠረተ ልማት አውታሮችን በዋናነት መንገድ ዝርጋታ፤ ውሃና መብራት መስመር አቅርቦት እየሠራ ይገኛል ።

መሠረተ ልማት ለአንድ ሀገር ህዝብ ዕድገት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ እንደ ደም ሥር የሚታይ ቢሆንም ይህ መሰረተ ልማት የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድ ደግሞ ጸጥታና ሰላም ወሳኝነት አላቸው ።

በአጠቃላይ በደብረብርሃን ከተማና በዙሪያዋ እየተገነቡ በሚገኙ ኢንዱስትሪዎች የከተማዋ ህብረተሰብ ታላቅ ተስፋን የሰነቀ በመሆኑ መስተዳድሩም አስፈላጊውን ሁሉ እያደረገም ይገኛል ።

ደብረ ብርሃን ከተማ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በከተማ ካለው ሰላምና ጸጥታ አንጻር ተመራጭ እየሆነች ስለመምጣቷ ደግሞ በደብረብርሃን ከተማ የሰላምና ህዝብ ደህንነት መምሪያ ሃላፊ አቶ አበራ መኮንን ይናገራሉ። እኛም በከተማዋ ስላለው የሰላም ሁኔታና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ቃለ ምልልስ አድርገናል።

**አዲስ ዘመን ፦ ደብረ ብርሃን ከተማ በተለይም እንደ አገር ካለብን ፈተና አንጻር ያለው የሰላምና ደህንነት ሁኔታ ምን መልክ አለው?**

**አቶ አበራ ፦** ደብረ ብርሃን ከተማ በቅርቡ አዲስ መዋቅር ተሰርቶ ወደ ሪጂዎ ፖሊታንት ከተማ አስተዳደር ተሸግራለች። አሁን ላይ በሙሉ አቅማቸው የሚንቀሳቀሱ አራት ክፍለ ከተሞችንም እንዲያቅፍ ሆኗል። ይህ ደግሞ የከተማዋን እድገት በማፋጠን ሌሎች እህት ከተሞች የሚያደርጉትን ድጋፍ ተንተርሶ በርካታ የኢንቨስትመንት አማራጭ እንዲኖራት በርካታ ባለሀብቶች እንዲሳቡና ያላትን የገጸምድርና ከርሰ ምድር ሃብት በቅጡ አውቀው ወደልማት በመቀየር በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ ሚናዋን እንድትወጣ የሚያደርጋት ነው። ይህ እንዲሆን ግን ከተማዋ ከዚህ ቀደም የምትታወቅበትን የሰላምና መረጋጋት ሁኔታ ማስጠበቅ የግድ ይላል።

ይህንን የሰላም ማስጠበቅ ስራ አጠናክሮ ለመቀጠልም ከዚህ ቀደምም ቢሆን ሰላም ወዳድ የሆነውን የከተማዋን ነዋሪ ይበልጥ በሰላም አስፈላጊነት ዙሪያ ግንዛቤው እንዲያድግ በማድረግ የከተማዬ ሰላም የእኔም፣ የቤተሰቤም ነው ብሎ እንዲያስብ በማድረግ በኩል ሰፊ ስራዎች ተሰርተው የተለያዩ ውጤቶችም እየተመዘገቡ ነው።

ህዝቡ የከተማዬ ሰላም የእኔና የቤተሰቤም በሰላም ወጥቶ መግባት ምክንያት ነው ብሎ በማመኑም በአሁኑ ወቅት የትኛውም ሃይል የሚሰጠው አጀንዳ በከተማችን ነዋሪዎች ዘንድ ምንም አይነት ተቀባይነት የሌለው ሆኗል። በአሁኑ ወቅት ሲቃወምም ሆነ ሲደግፍ ምክንያታዊ የሆነ የከተማ ነዋሪም ለማፍራት ተችሏል።

አሁን ባለው ሁኔታ እንደ አገር በበርካታ ውጥረት ውስጥ ያለን ብንሆንም እንደ ደብረ ብርሃን ከተማ ግን አንጻራዊ ሰላም ያለበት ከተማ ነው። ይህ ደግሞ የመጣው የጸጥታ መዋቅሩና ህዝቡ እጅና ጓንት ሆኖ አካባቢውን በንቃት በመጠበቁ የተፈጠረ ነው ማለት እችላለሁ።

ለምሳሌ ብነግርሽ እዚህ ከተማ ውስጥ የሚኖር ነዋሪ በሙሉ በከተማዋ በየእለቱ ምን እየተከናወነ እንደሆነ፣ እነማን ምን እየሰሩ እንደሆነ ያውቃል ከዚያ በላይም ደግሞ ለየት ያለ እንቅስቃሴ ሲያይ ወይንም ደግሞ ጸጉረ ልውጦች በከተማዋ መንቀሳቀስ ላይ ከሆኑ ጊዜ ሳያጠፋ ለፀጥታ ሀይሉ ያሳውቃል። በዚህ ደግሞ የፀጥታ ሀይሉ በፍጥነት ወደ አካባቢው በመድረስ ብዙ ነገሮችን ማዳን የከተማዋንም ሰላም በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲቆም ለማድረግ ችሏል።

አሁን ባሳለፍነው የትንሳኤ በዓል ወቅት እንኳን ህዝበ ክርስቲያኑ በዓሉን በሰላምና በደስታ እንዲያከብር በሰራቸው ስራ በበዓሉ ዋዜማም ሆነ በእለቱ እንዲሁም በቀጣይ ባሉ ቀናት እንኳን ህዝቡን ስጋት ላይ የሚጥል ችግር ቀርቶ የእርስ በእርስ ድብድብ እንኳን ያልታየበት ሆኖ አልፏል። ይህ ውጤት ሊገኝ የቻለው ደግሞ ህዝቡና የጸጥታ ሀይሉ በመናበብ በሰሩት ስራ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

**አዲስ ዘመን ፦ አሁን ያለንበት ወቅት አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ በተለይም እንደ አማራ ክልል ችግሮች እዚህም እዚያም ብቅ ብቅ ይላሉና ደብረ ብርሃን ከተማ ሰላሟን በዚሁ መልክ አጠናክራ እንድትቀጥል በተለይም በእናንተ የጸጥታ መዋቅር ውስጥ ምን አይነት ስራዎች ይከናወናሉ?**

**አቶ አበራ ፦** የሰላም ጉዳይ ዋናና መሰረታዊ ነው። ሰላም ከሌለ ከተማዋን ማልማት ህዝቡን ተጠቃሚ ማድረግ ብሎም እንደ አንድ ዜጋ ወጥቶ መግባት በራሱ ትልቅ ፈተና ስለሚሆን ይህ እንዳይመጣና

**የከተማዬ ሰላም የእኔም፣ የቤተሰቤም ነው ብሎ እንዲያስብ በማድረግ በኩል ሰፊ ስራዎች ተሰርተው የተለያዩ ውጤቶችም እየተመዘገቡ ነው**



# ወቅታዊ

የሰላሙ ሁኔታ በዚሁ መልኩ አስተማማኝ እንዲሁም ሌት ቀን ይሰራል:: ነገር ግን ሰላምን ማስጠበቅ ከላይ እንዳልኩት የፀጥታ መዋቅሩ ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዱ ነዋሪ ሃላፊነት በመሆኑና ሁሉም ነቅቶ አካባቢውን መጠበቅ ስላለበት እንደ ቢሮ የምንሰራው የህዝቡን አስተሳሰብ መቀየር ላይ ነው:: በየደረጃው ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችም ማለትም ሰላምን በማስጠበቅ በኩል ወጣቱም፣ ሴቶችም፣ የሃይማኖት አባቶችም በጠቅላላው ሁሉም የየራሱ ድርሻ ስላለው ከእነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ሰፋፊ ወይይቶችን እናደርጋለን::

በቀጣይም ህዝብና መንግስት የተጠናከረ ስራን እንዲሰሩ እንዲሁም የተለያዩ የፖሊስ አደረጃጀቶችም ወደነበሩበት እንዲመለሱ በሌላም በኩል ፖሊስ በሌለበት ሁሉም የከተማው ፖሊስ ሆኖ እንዲሰራ በተለያዩ ጊዜያት ከእምነት ከአመለካከትና ከብሔር እንዲሁም ከሌሎች ጉዳዮች ጋር በተገናኘ የሚፈጠሩ ችግሮች እንዳይኖሩ፤ ሲኖሩም በምክንያት እንዲፈቱ በማድረግ በኩል የፀጥታ መዋቅሩ ሰፊ ስራ እየሰራ ነው ለማለት እችላለሁ ::

ነገር ግን እዚህ ላይ የጸጥታ መዋቅሩ የፈለገ ቢጠናከር ህዝብ ያልተሳተፈበት ስራ ውጤታማ ስለማይሆን እንደ ትልቅ የትኩረት አቅጣጫ የያዝነው የሰላም ማስከበሩን ጸጥታ የማስፈኑን ስራ ህዝቡ በበላይነት እንዲመራውና የነቃ ተሳትፎን እንዲያደርግ በክልሉ ልማት ስራ ለመስራት የመጡ ባለሀብቶችም ድጋፍ እንዲያደርጉ የማድረግ ስራም እየተሰራ ይገኛል::

**አዲስ ዘመን ፡- በደብረ ብርሃን አቅራቢያ ያሉ የአማራ ክልል ከተሞች እንግዲህ በህወሃት ሀይሎችም እንዲሁም በኦነግ ሸኔ የተለያዩ ችግሮችን እያስተናገዱ ነውና እንደው ይህ የሰላም መደፍረስ ወደክልሉ እንዳይመጣ እየተሰራ ያለው የመከላከል ስራ ምን መልክ አለው?**

**አቶ አበራ ፡-** ትክክል ነው ፤ በቅርብ ርቀት ያሉ ከተሞች በተለያዩ አሸባሪ ቡድኖች ችግር ውስጥ እየገቡ ነው:: ይህ ወደከተማችን እንዳይመጣ ትልቅ ሀላፊነት ወስደን ህዝቡን በደጀንነት አሰልፈን ብዙ ስራዎችን እየሰራን ነው:: በቅርቡ በነበረው የህልውና ዘመቻ ላይ እንኳን የከተማዋ በርካታ ወጣቶች “ሆ” ብለው በመነሳት ክቡር የሆነውን ህይወታቸውን እስከመስጠት የደረሰ መስዋዕትነት ከፍለዋል::

በነገራችን ላይ ደብረ ብርሃን ከተማ በተግባር ጦርነት አይካሄድበት እንጂ የሁሉም ነዋሪ አእምሮ በጦርነት ውስጥ የከረመ ነው:: ከዚህ አንጻር አሸባሪው ቡድን እስከ ደብረ ሲና ሲመጣ እንኳን በከፍተኛ ወኔና ሞራል የክልልን እንዲሁም የከተማውን ሰላም ለማስጠበቅ ብዙ መስዋዕትነት ከፍሏል:: ከዚህ ጎን ለጎንም አሁን ላይ ደግሞ ወደጦርነት ልጆቻቸውን ባሎቻቸውን የሸኙ ቤተሰቦች የፋሲካ በዓልን ተደስተው እንዲውሉ በማሰብ በርካታ ድጋፎችንም አሰባስበው ለግሰዋል:: በመሆኑም አሁን ባለው ሁኔታ ከተማዋ በራሷ ዙሪያውን በተለያዩ ሀይሎች የተወጠረች ከመሆኑ እንዲሁም ሰላም መሆኗ የሚያናድዳቸው በርካታ የጥፋት መልዕክተኞች ያሉ በመሆኑ አሁን ከዚህ በፊቱ በተሻለ ሁኔታ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል::

እነዚህ የከተማዋ ሰላም መሆን የሚያናድዳቸው ሀይሎች በተለያየ ጊዜ አጀንዳዎችን ለመስጠት ሲሞክሩ ተገኝተዋል፤ በመሆኑም ህዝቡም የጸጥታ ሀይሉም በቅንጅት እነዚህን መጥፎ በድኖች ሲዋጋ ቀሪው የመንግስት ስራ አስፈጻሚ ደግሞ በተለይም በከተማዋ ህዝቡን ለአመጽ ወይንም ደግሞ ለሌላ ሃሳብ የሚዳርጉ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ከስር ከስር መፍታት ይኖርበታል ብለን በዚህም ላይ ተስማምተን ሁሉም የድርሻውን እንስቶ ስራዎች በመሰራት ላይ ናቸው::

ይህንን ካደረግን በኋላ ዙሪያውን በሸኔም ይሁን የጁንታው ተላላኪዎች ሰርገው ሊገቡ ስለሚችሉ አከራይ ተከራይ የጸጉረ ልውጥ እንቅስቃሴ የሆቴሎች ፍተሻ በጣም በተጠናከረ መልኩ ይቀጥላል ፤ አሁን ላይ ደግሞ በከተማዋ ያሉ ኢንዱስትሪዎችም ስራ በመጀመር ላይ ስለሆኑ የተለያየ ሰው ከመላው የአገሪቱ ጫፍ ወደከተማዋ ስለሚመጣ ይህንን በአግባቡ መምራትና ክትትል ማድረግ ላይ ከፍተኛ ስራን እንሰራለን:: ችግሮችም ሲገኙ ከስር ከስር የሚታረሙበትን ሁኔታ እንፈጥራለን::

አሁን ባለው ሁኔታ ግን ደብረ ብርሃን ከተማ ጥሩ የሚባል ሰላም ያለባት ነች፤ ነገር ግን ይህንን ሁኔታ አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል::



**አዲስ ዘመን ፡-በከተማዋ ከሚስተዋለው ነገር አንዱ ከተለያዩ የአማራ እንዲሁም የወለጋ አካባቢዎች ተፈናቅለው የመጡ ዜጎች ጉዳይ ነውና እንደው ከተማዋ በዚህን ያህል ስደተኞች ሲገቡባት ከሰላም ከጸጥታ አንጻር ስጋት የመሆኑ ሁኔታ ምን ያህል ነው፤ ይህንን በመቆጣጠሩና በማረጋጋቱ በኩልስ ሚናችሁ ምን ያህል ነው?**

**አቶ አበራ፡-** አዎ በከተማችን ከተለያዩ የአማራና የኦሮሚያ አካባቢዎች ተፈናቅለው የመጡ ስደተኞች አሉ ፤ ቁጥራቸውም ከ 25 ሺ በላይ ነው፤ እነዚህ ሁሉ ሰዎች ደግሞ ወደከተማዋ የመጡት የደብረ ብርሃን ተወላጅ ስለሆኑ ሳይሆን በከተማዋ ያለውን አንጻራዊ ሰላም ለመጠቀም በማሰብ ነው::

የገጠመንን ችግር መንግስት በዘለቄታዊ ሁኔታ እስከሚፈታው ድረስ ደግሞ እንደ ከተማ የተቻለንን እናደርጋለን:: ነገር ግን እነዚህ ከቤት ንብረታቸው አላግባብ የተፈናቀሉ ዜጎች ብዙ በውስጣቸው የሚመላለሱ ስሜቶች አሏቸው:: አሁን ያሉበት ሁኔታ እጅግ አሳዛኝ ነው፤ ይህ ሁሉ ነገር ተደማምሮ እነሱም የከተማዋን ሰላም አደፍራሽ እንዳይሆኑ የራሳችንን ክትትል ከማድረግ የተለያዩ ድጋፎችን የሚያገኙበትን ሁኔታ ከማመቻቸት ጀምሮ ከራሳቸው ውስጥ ሰዎችን በመምረጥና እዛው የጸጥታ አደረጃጀትን በመፍጠር ክትትል እያደረግን እንገኛለን:: እስከ አሁን ለከተማዋ ስጋት የሚሆን ችግርም አልፈጠሩም:: እነሱም ላይ የተፈጠረ ችግር የለም::

**አዲስ ዘመን ፡- እንግዲህ እንደ አማራ ክልል ክተት በታወጀበት ወቅት በርካታ ሰዎች የጦር መሳሪያን የማግኘት እድሉን ወይም አጋጣሚውን አግኝተዋል፤ እንደው እንደእናንተ ከተማ ይህንን የጦር መሳሪያ ሳልተገባ አላማ እንዳይውል በመከላከሉ፣ በመቆጣጠሩና ፍቃድ በመስጠቱ በኩል እያከናወናችሁ ያላችሁት ነገር ምን ይመስላል?**

**አቶ አበራ ፡-** አዎ ከተቃጣብን የጁንታው ወረራ ጋር ተያይዞ ለበርካታ ሰዎች ፍቃድ ተሰጥቶ የተያዙ የጦር መሳሪያዎች አሉ:: እነዚህ የጦር መሳሪያዎችን የሚያስተዳድርበት ደግሞ ክልሉ የራሱ መመሪያ አለው፤ በዚህ መመሪያ መሰረትም እየተዳደረ ነው:: በመሆኑም የግል፣ የመንግስት፣ በሚሊሻ እጅ ያለ፣ በተመላሽ ሰራዊት እጅ ያለ፣ ትጥቅ እየተባለም አደረጃጀት ተፈጥሮለታል:: ይህንን በአግባቡ የመምራትና የማስተዳደር ስራም ይሰራል::

በነገራችን ላይ አሁን ለየትኛውም አካል የጦር መሳሪያ ፍቃድ መስጠት ተከልክሏል:: ለማንም ፍቃድ አይሰጥም:: በህገ ወጥ መንገድ የሚንቀሳቀስ የሚገበያይ እንዲሁም ይዞ የሚገኝ ካለ ደግሞ በኬላ ፍተሻዎቻችን በደፈጣ ስራችን እንዲሁም በተለያዩ መንገዶች በሚደረጉ ክትትሎች የሚገኙት ላይ ጠበቅ ያለ እርምጃ እየተወሰደ ነው:: ምክንያቱም ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ በተበራከተ ቁጥር መጨረሻው ወይም ደግሞ ሄዶ ሄዶ የሚያርፍበት ሁኔታ ከባድ ስለሚሆን በዚህ በኩል የሚደረገው ክትትልና ቁጥጥር ጫን ያለ ነው:: ይህንንም ለህብረተሰቡ በሚገባ የማሳወቅ ስራ ተከናውኗል::

እዚህ ላይ ግን ልብ እንዲባል የምፈልገው ነገር አንድ ሰው የጦር መሳሪያውን ስላስመዘገበ ወይም ፍቃድ በእጁ ስለያዘ ብቻ ክትትል አይደረግበትም ማለት አይደለም:: በተለይም በዚህ ወቅት ፍቃድ ያለው የጦር መሳሪያም ቢሆን እንኳን ለምን አላማ እንደሚውል፣ ምን እንደሚሰራበት የመከታተሉ ስራ በከፍተኛ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል::

**አዲስ ዘመን ፡- እንደ ከተማ ስምታደርጉት የሰላምና የጸጥታ ስራ በተለይም አጎራባች ከሆነው የኦሮሚያ ክልል ጋር ያላችሁ ጥምረትና አብሮ የመስራት ሁኔታ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ አበራ ፡-** አዎ፤ ከኦሮሚያ ክልል በተለይም መንዲዳ ከሚባለው አካባቢ ጋር እንዋሰናለን፤ ከዚህ አንጻር ደግሞ የሁለቱንም አካባቢዎች ሰላም ለማስጠበቅ ብዙ ስራዎችን እንሰራለን፤ ጥሩ ግንኙነትም ነው ያለን፤ በቅርቡም የጋራ ውይይት ተደርጓል:: የጸጥታ ስራ ድንበር ተሻጋሪ እንደመሆኑም በውስጣችን ያሉ ችግሮችን ለማረም ለመፍታትና ቀጣይ አቅጣጫችንም ለማሳመር ትብብር አይነተኛ ሚና ያለው ከመሆኑም አንጻር ብዙ ስራዎችን እንሰራበታለን:: ይህ ስራ ደግሞ በውጤትም መታጀብ ያለበት በመሆኑ በርካታ ውጤቶች መጥተዋል:: በዚህም ሰርጎ ገቦችን የመያዝ አንዳንድ ተላላኪዎች የሚሰሩትን እኩይ ተግባር የማክሸፍ ስራዎችም ተሰርተዋል::

**አዲስ ዘመን ፡-እንደ አገር ሰላማችንን የማይፈልጉ አፍራሽ ሀይሎች በተለያዩ ክልልች ላይ የፈጸሙት እኩይ ተግባር ብዙ ነገሮችን እያሳጣን ነው፤ ከዚህ አንጻር ደብረ ብርሃን እስከ አሁን ሰላም ናትና እንደው ይህንን ሰላም ወደፊትም አጠናክሮ ለመቀጠል ከማን ምን ይጠበቃል ይላሉ?**

**አቶ አበራ ፡-** አሁን ያለንበት ሁኔታ እንደ አገር እየፈተነን ነው ያለው:: የአገራችንን ሰላም የማይፈልጉ አካላትን ለተላላኪዎቻቸው ብዙ አጀንዳዎችን ነው የሚሰጡት ፤ይህንን እኩይ ተግባራቸውን ለማስፈጸምም የተጠናከረና የተጠና እቅድ ይዘው አማራጭ አስቀምጠው ነው የሚንቀሳቀሱት፤ በመሆኑም ይህንን ህልማቸውን ለማክሸፍ እኛም በበኩላችን አጀንዳ ሰጪ እንጂ ተቀባይ ሆነን መቀጠል የሌለብን ከመሆኑም በላይ አመራሩና ህዝቡ እንደከዚህ ቀደሙ በበለጠ ሁኔታ መቀናጀትና መናበብ ይኖርበታል::

የሰላም ጉዳይ የማይመለከታቸው የለም:: ሁሉም ይመለከተዋል:: ሰላም ከሌለ ማንም ወጥቶ መግባት ልጆቹን ማሳደግ ራሱን ማስተዳደር እንደማይችል ግልጽ ነው:: በመሆኑም የሰላምን ዋጋ ካጣነው በኋላ ሳይሆን መረዳት ያለብን አሁን በእጃችን እንዳለ መሆኑን ማወቅ መገንዘብ ያስፈልጋል:: ከተማችንም እስከ አሁን በመጣችበት አግባብ ሰላሟ ተጠብቆ እንድትቀጥልና የሰላም አምባሳደር እንድትሆን መላው የከተማው ነዋሪ የበኩሉን ሊወጣ ይገባል::

የሰላምና ጸጥታ ቢሮውም የተለያዩ እቅዶች አቅዶ እየሰራ በመሆኑም ይህንንም ሀይል ማገዝ ያስፈልጋል፤ ያለ ህዝብ የሚሰራ የጸጥታ ስራ ዋጋ የለውም ምክንያቱም የቱንም ያህል ብርጌድ ቢቆም የጸጥታ መዋቅሩም በከፍተኛ ሁኔታ ቢደራጅ ያለህዝብ ተሳትፎ የትም መድረስ ስለማይቻል ከወጣቱ፣ ከአገር ሽማግሌ፣ ከሀይማኖት አባቶች ጋር የጀመርናቸውን ውይይቶች አጠናክረን እንሰራለን::

በሌላ በኩል ደግሞ ህዝቡ በተለይም የትንሳኤ በዓል በሚከበርበት ወቅት ያሳየውን አንድነት፣ ትብብርና ሰላም ወዳድነት በማስቀጠል የከተማችንን ስም በሰላም ማስጠራቱን አጠናክሮ መቀጠል አለበት::

**አዲስ ዘመን ፡- ስነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ::**

**አቶ አበራ ፡-** እኔም አመሰግናለሁ

# ዓለም አቀፍ

## የብራዚሉ ፕሬዚዳንትና የሆሊውዱ ሊዮናርዶ ዲካፕሪዮ በአማዞን ደን ምክንያት እየተናቆሩ ነው

የብራዚሉ ፕሬዚዳንት ጃይር ቦልሶናሮ እና የሆሊውዱ ተዋናይ ሊዮናርዶ ዲካፕሪዮ የአማዞን ጫካን አስመልክተው አንድ ሁለት እየተባባሉ ነው። የአካባቢ ጥበቃ ተሟጋቹ ዲካፕሪዮ፣ የብራዚል ሕዝብ ለአማዞን ደን ደኅንነት ሲል በቀጣዩ አገር አቀፍ ምርጫ ድምጽ እንዲሰጥ ጥሪ አቅርቧል። ቦልሶናሮ ግን የዲካፕሪዮ አስተያየት አልጣማቸውም።

ዲካፕሪዮ «ብራዚል ለብዝሀ ሕይወት ቀጣይነት መሠረት የሆነው የአማዞን ደን ባለቤት ናት። ጤናማ ምድር እንዲኖረን የብራዚል ወጣቶች በቀጣዩ ምርጫ ድምጻቸውን ማሰማት አለባቸው» ብሏል። የአካባቢ ጥበቃ ሕግጋትን የቀነሱት ቦልሶናሮ ግን በዲካፕሪዮ ንግግር ተሳልቀዋል። «ሊዮ፣ ስለ ድጋፍህ እናመሰግናለን። በመጪው ምርጫ ሁሉም ብራዚላዊ ድምጽ መስጠት አለበት» ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

አክራሪ ቀኝ ዘመሙ ቦልሶናሮ፣ የብራዚል ሕዝብ አማዞን ደንን በተመለከተ «የውጭ ኃይሎችን ጣልቃ ገብነት» አልያም «አገር በቀል ውሳኔ» እንደሚያሳልፍ የሚታይበት ምርጫ እንደሆነም ጠቆም አድርገዋል። ዲካፕሪዮ እአአ በ2019 ለአማዞን ደን ጥበቃ 5 ሚሊዮን ዶላር ለግሷል። ቦልሶናሮ ደግሞ ደኑ እንዲጨፈጨፍ በመፍቀድ ይተቻሉ። አማዞን የዓለማችን ትልቁ ባለ ብዝሀ ሕይወት ደን ነው። የምድራችን 'ሳምባ' እየተባለም ይሞካሻል።

ቦልሶናሮ ይህ የተፈጥሮ ሀብት እንዲበዘበዝ ፈቅደዋል ተብለው ይታማሉ። አስተዳደራቸው በበኩሉ ድህነትን እየተዋጋ እንደሆነ ይከራከራል። የሳተላይት መረጃ እንደሚያሳየው፣ ዘንድሮ ጥር ላይ የተጨፈጨፈው ደን ከአምናው አምስት እጥፍ ይልቃል።

የአማዞን ደን ከከባቢ አየር ካርበንን ጨምቆ ይወስዳል። ዛፍ ሲቆረጥ ግን የካበን ልቀት ወደ አየር ይዋሀዳል። ይህም የአየር ንብረት ለውጥን ያፋጥናል። ዲካፕሪዮ እና ቦልሶናሮ ሲወዛገቡ ይህ የመጀመሪያቸው አይደለም። በ2019 ቦልሶናሮ ዲካፕሪዮን «አማዞን እንዲቃጠል ገንዘብ ሰጥቷል» ብለው ከሰዋል። ቦልሶናሮ ለክሳቸው ማስረጃ አላቀረቡም።

ፕሬዚዳንቱ ፖሊሲያቸውን የሚነቅፍ ማንኛውም የተፈጥሮ ጥበቃ ድርጅት ወይም ተሟጋችን ከማጠልሸት ወደኋላ አይሉም። ብራዚል አማዞንን መጠበቅ ካልቻለች፣ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ማንኛውንም ዓይነት የአካባቢ ጥበቃ ስምምነት ከብራዚል ጋር እንዳይፈርሙ የሚጠይቀው የዝነኞች ቡድን ውስጥ ዲካፕሪዮም እንደሚገኝበት ቢቢሲ ዘግቧል።




## የጊኒ ወታደራዊ አስተዳደር ሥልጣን ለሲቪል አስተዳደር እንደሚያስረክብ አስታወቀ

የጊኒ ወታደራዊ መንግሥት ከ39 ወራት የሽግግር ጊዜ በኋላ ሥልጣን ለሲቪል አስተዳደር አስረክባለሁ አለ።

የጁንታው አለቃ ኮሎኔል ማማዲ ዱምቦያ በቴሌቪዥን ቀርቦ ይህ ጊኒን በ3 ዓመታት ወደ ሲቪል አስተዳደር የማሸጋገሩ ምክረ ሐሳብ ለጊኒ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ይጸድቃል።

ወታደራዊው ኃይል ባለፈው ዓመት የአገሪቱን ተመራጭ ፕሬዚዳንት በመፈንቅለ መንግሥት ካስወገደ በኋላ አገሪቱን በመምራት ላይ ይገኛል። በርካታ ጊኒያውያን ይህን መፈንቅለ መንግሥት ደግፈውት ነበር። ሆኖም ግን እየቆየ ሲሄድ ወታደሮቹ ሥልጣን ለሲቪል አስተዳደር እንዲያስረክቡ ከሕዝብ ጫና በርትቶባቸዋል።

ይህ የወታደራዊው አገዛዝ መግለጫ የመጣው የምዕራብ አፍሪካ አገራት ኅብረት የሆነው ኢኮዋስ ወታደራዊው መንግሥት እስከ ሰኞ ዕለት ወደ ሲቪል አስተዳደር የሚመለስበትን ዕቅድ ካላቀረበ ማዕቀብ እንደሚጥሉ ከዛቱ በኋላ ነው። መፈንቅለ መንግሥቱን ተከትሎ 80 አባላት ያሉት የጊኒ የሽግግር ምክር ቤት ተመሥርቷል። ይህ ካውንስል ነው አሁን የጊዜ የተወካዮች ምክር ቤት ሥራን የሚሠራው።

የሦስት ዓመት ከሦስት ወራት የሽግግር ጊዜ እንዲኖር ምክረ ሐሳብ የቀረበው ለዚህ ካውንስል ነው። ኮሎኔል ዳምቦያ እንዳለው እሱን ጨምሮ ማንም ቢሆን በዚህ የሽግግር መንግሥት ጣልቃ መግባት አይችልም። ባለፈው የፈረንጆች ዓመት መስከረም ላይ ነበር ይህ ወታደራዊ ጁንታ የ84 ዓመቱን ፕሬዚዳንት አልፋ ኮንዴን በንቅዘት እና ሙስና በመክሰስ ከመንበራቸው ያስወገዳቸው።

ፕሬዚዳንቱ በተለይም ለሦስተኛ ዘመን በሥልጣን ለመቆየት ሲሉ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ካደረጉ ወዲህ በሕዝብ ዘንድ የነበራቸው ተቀባይነት ወድቋል። በርካታ ጊኒያውያን መፈንቅለ መንግሥቱን አዲስ ተስፋ አድርገው ተመልክተውት የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ለውጡ አዝጋሚ ሆኖባቸዋል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በምዕራብ አፍሪካ መፈንቅለ መንግሥት ተበራክቶ ታይቷል። ከእነዚህ ውስጥ የማሊና የኒጀር እንደሚገኙበት የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# በክልሎች እያደገ የመጣው የተማሪዎች ምገባ መርሃ ግብር

እየሩስ ተስፋዬ

በትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ምገባ መርሃ ግብር መጀመር ጥቅሙ ለተማሪዎች ብቻ ሳይሆን በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ወላጆች ለጭንቀታቸው በተወሰነ መልኩ እፎይታን የሰጠ መሆኑ ይነገራል፡፡ በተጨማሪም መርሃ ግብሩ በዘላቂነት መሰጠቱ የበለጸገ የሠው ኃይል ከማስገኘት አኳያ ሚናው ከፍተኛ ሲሆን ፤ከዚህ መርሃ ግብር መጀመር ጋር በተያያዘም ከ15 እስከ 25 በመቶ የተማሪዎች ተሳትፎና አቴንዳስ መሻሻሉንም ጥናቶች አመላክተዋል፡፡

ከአራት ዓመታት ወዲህ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በስፋት ይሰጥ የነበረውን የምገባ ፕሮግራም በቅድመ አንደኛና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ እንዲሰጥ ለማድረግ ትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር የፖሊሲ ማዕቀፍና ስትራቴጂ ሰነድ ማዘጋጀቱ ይታወቃል። ይህ ሰነድ በቀጣይ በየደረጃው ባለው የትምህርት መዋቅር በጀትን ጨምሮ በማስፋት እና የተጠቃሚ ተማሪዎችን ቁጥር ለመጨመር እቅድ ይዟል።

ከዚህ አኳያ መርሃ ግብሩን ለማስፋት ክልሎችም የራሳቸውን በጀት በመመደብ አበረታች እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛል፡፡የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የኦሮሚያ ክልል እያደረጉት ያለው ጥረት የሚደነቅ ሲሆን፤የትምህርት ሚኒስቴር በቀጣይ ዓመታት ሁሉም ሕፃናት የምገባ መርሃ ግብር ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ፖሊሲና ስትራቴጂ አዘጋጅቶ በቅርቡ ወደ ትግበራ እንደሚገባ ማሳወቁ የሚታወስ ነው።

የምገባ መርሃ ግብሩ ከተጀመረ ወዲህ በአዲስ አበባ ከተማ የትምህርት መጠነ ማቋረጥና መጠነ መድገም በከፍተኛ ሁኔታ ከመቀነስ ባሻገርም በከተማዋ



ፎቶ ኤፍ.ቢ.ሲ

ተማሪዎች በምገባ ላይ

ከስድስት መቶ ሺህ በላይ ተማሪዎችን ማሳተፍ ችሏል፡፡ በተጨማሪም ከአሥር ሺ በላይ ለሆኑ እናቶችና ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠሩን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

በያዝነው ሚያዚያ ወር የሐረሪ ክልል ትምህርት ቢሮ የተማሪዎች የምገባ ፕሮግራም ማስጀመሩን ያስታወቀ ሲሆን የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብሩ በዘጠኝ ወረዳዎች፤ በ67 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ 35 ሺ ሦስት መቶ 50 ተማሪዎችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ተገልጿል፡፡

የክልሉ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሙክታር ሳሊ እንዳሉት፤ የምገባ የመርሃ ግብሩ መጀመር በምግብ እጥረት ምክንያት የሚታየውን የተማሪዎች ማቋረጥ እንዲሁም የመድገም ምጣኔን ለመቀነስ እና ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት ለመሳብ ይጠቅማል፡፡ የመርሃ ግብሩ መጀመር ስድስት ለሚሆኑ ወገኖች የሥራ ዕድልን እንደሚፈጥር መግለጻቸውን ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

በአማራ ክልልም ከግንቦት ወር 2014 ዓ.ም ጀምሮ በ20 ሚሊዮን ብር በጀት በዋግ ኽምራ ብሔረሰብ ዞን በሚገኙ 76 ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የምገባ መርሃ ግብር ተግባራዊ እንደሚደረግ የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ አስታውቋል።በክልሉ ከየካቲት 2014 ዓ.ም ጀምሮ በሁለት መቶ 48 ትምህርት ቤቶች ከ98 ሺ በላይ ተማሪዎችን የምገባ ፕሮግራም ተጠቃሚ ማድረግ እንደተቻለ የተገለጸ ሲሆን፤የቢሮው የስርዓተ ምግብ ባለሙያ አቶ ተዋበ ዓለሙ ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት እንደገለጹት የምገባ መርሃ ግብሩ የሚካሄደው አሸባሪው ሕወሓት ዘረፋና ውድመት በፈፀመባቸው እና የምግብ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች ነው። የምገባ መርሃ ግብሩ መጀመር ተማሪዎች ትምህርታቸውን በንቃት እንዲከታተሉና የተማሪዎችን መጠነ ማቋረጥ ለመቀነስ የሚያስችል መሆኑም ተጠቁሟል።

የክልሉ መንግሥት በመደበው 20 ሚሊዮን ብር በጀት ከመጪው ግንቦት ወር 2014 ዓ.ም ጀምሮ በዋግኽምራ ብሔረሰብ ዞን በድሃናና ጋዝጊብላ ወረዳዎች በሚገኙ 76 ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የምገባ ፕሮግራም የሚጀመር ሲሆን እስከ ሐምሌ 2014 ዓ.ም በሚቆየው የምገባ ፕሮግራም ከአፀደ ህፃናት ወይም ከቅድመ አንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚገኙ ከ27 ሺ በላይ ተማሪዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል።

እንደ አቶ ተዋበ ገለጻ፤ በአሁኑ ወቅት ለመርሃ ግብሩ የሚውል ከሦስት ሺ ኩንታል በላይ አልሚ ምግብ ለማቅረብ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል። ከየካቲት 2014 ዓ.ም ጀምሮ በክልሉ ሰሜንና ደቡብ ወሎ ፣በዋግኽምራና ኦሮሞ ብሔረሰብ ዞኖች ውስጥ በሚገኙ ሁለት መቶ48 ትምህርት ቤቶች እየተካሄደ በሚገኘው የምገባ መርሃ ግብር ከቅድመ አንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚማሩ 98 ሺ አንድ መቶ ተማሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

የምገባ መርሃ ግብሩን ግሎባል ፓርትነርሽፕ ፎር ኢዱኬሽን፣ በኢትዮጵያ ስኩል ሚል ኢንሼቲብ ፣ ሴቭ ዘ ችልድረንና የዓለም ምግብ ድርጅቶች በተባሉ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን፤ግብረ ሰናይ ድርጅቶቹ በየወሩ ሁለትሺ አንድ መቶ45 ኩንታል አልሚ ምግብ፣ ዘጠኝ ሺ ሰባት መቶ 11 ካርቶን ብስኩት፣ 46 ሺ ሁለት መቶ ሊትር የምግብ ዘይትና ጨው እያቀረቡ መሆኑን አቶ ተዋበ ገልጸዋል።

በዋግኽምራ ዞን ሰቆጣ ዙሪያ ወረዳ የወለህ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምክትል ርዕሰ መምህርት ብርቅ ወርቁ በበኩላቸው በትምህርት ቤቱ ምገባ መጀመሩ ተማሪዎች ስለ ምግብ ሳያስቡ ትምህርታቸውን ብቻ እንዲከታተሉ አግዟል ያሉ ሲሆን አክለውም፤ የምገባ መርሃ ግብሩ ተማሪዎች በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ ከደረሰባቸው የስነ ልቦና ችግር በመውጣት ተሳትፏቸው እንዲጨምር አቅም ፈጥሯል ብለዋል፡፡

# ስፖርት





## ታዳጊዎቹ ሉሲዎች ወደ ዓለም ዋንጫ ለማቅናት ናይጄሪያን ይገጥማሉ

**ቦጋለ አበበ**

በአሰልጣኝ እንዳልካቸው ጫካ እየተመሩ ከሁለተኛው ዙር ማጣሪያ በኋላ ፉክክሩን የተቀላቀሉት ታዳጊዎቹ ሉሲዎች በመጀመሪያ የማጣሪያ ጨዋታቸው ዩጋንዳን በሜዳዋ ገጥመው ሁለት ለሁለት በሆነ አቻ ውጤት ማጠናቀቃቸው ይታወሳል። በመልሱ ጨዋታም በአዲስ አበባ አበበ ቢቂላ ስቴድየም አንድ ለአንድ በሆነ አቻ ውጤት አጠናቀዋል። ታዳጊዎቹ የዩጋንዳውን የደርሶ መልስ ማጣሪያ ሦስት ለሦስት በሆነ አቻ ውጤት ቢያጠናቅቁም ከሜዳቸው ውጪ ብዙ ግብ በማስቆጠራቸው ወደ ቀጣዩ ማጣሪያ ሊያልፉ ችለዋል። አራተኛውን የማጣሪያ ውድድር በ2010 እና 2018 የዓለም ዋንጫ ተሳታፊ ከነበረችው ደቡብ አፍሪካ ጋር የተደለደሉት ታዳጊዎቹ ሉሲዎች ከተጋጣሚያቸው አንጻር ልምድ የሌላቸው መሆኑ ብዙ ርቀት ላይጓዙ እንደሚችሉ ስጋት ነበር። ይሁን እንጂ የነበረው ስጋት ከንቱ እንደነበር ደቡብ አፍሪካን በሜዳዋ ጆሃንስበርግ ላይ ገጥመው ባስመዘገቡት አስደናቂ ውጤት ማረጋገጥ ችለዋል። እነዚህ ታዳጊ ሴቶች ከሁለት ሳምንት በፊት ወደ ደቡብ አፍሪካ አቅንተው የተሻለ ልምድ ያላትን ደቡብ አፍሪካን ባልተጠበቀ የሦስት ለዜሮ ውጤት በማሸነፍ ከሜዳቸው ውጪ ጣፍጭ ድል ይዘው ተመልሰዋል። ይህም የትናንቱን የአበበ ቢቂላ ስቴድየም የመልስ ጨዋታ ቀላል አድርጎላቸዋል።

እንደተጠበቀውም ታዳጊዎቹ ሉሲዎች የትናንቱ የመልስ ጨዋታ ላይ ግብ ማስቆጠር ወይም ማሸነፍ ሳይጠበቅባቸው ቀጣዩን ማጣሪያ በቀላሉ ሊቀላቀሉ ችለዋል። በትናንቱ የመልስ ጨዋታ ውጤት ለመቀልበስ አስበው ወደ ሜዳ የገቡት ደቡብ አፍሪካዎች ሰላሳ ሰባተኛ ደቂቃ ላይ ግብ ማስቆጠር ቢችሉም ደግመው የኢትዮጵያን የግብ ክልል መድፈር አልተቻላቸውም። በመጀመሪያው ጨዋታ የቤት ሥራቸውን ጨርሰው የመጡት ታዳጊዎቹ ሉሲዎችም በጨዋታው ተጨማሪ ግብ ተቆጥሮባቸው ጫና ውስጥ እንዳይገቡ ጥንቃቄ ከማድረግ የዘለለ ሥራ ሳይበዛባቸው የሚፈልጉትን ውጤት ይዘው ለመውጣት አልከበዳቸውም። በዚህም በአጠቃላይ ውጤት 3ለ1 በማሸነፍ በቀጣዩና በመጨረሻው ማጣሪያ የናይጄሪያ አቻቸውን እንደሚገጥሙ አረጋግጠዋል።



ታዳጊዎቹ ሉሲዎች ወደ ሕንዱ የዓለም ዋንጫ ለማቅናት ከናይጄሪያ አቻቸው ጋር የሚያደርጉት ማጣሪያ ብቻ ይቀራል፣

ወደ መጨረሻው የማጣሪያ ጨዋታ ለማቅናት ሦስተኛውን የማጣሪያ ጨዋታ ትናንትና ከትናንት በስቲያ ካደረጉ የአፍሪካ አገራት መካከል ሞሮኮ ተጋጣሚዋ ኒጀርን በደርሶ መልስ አጠቃላይ ውጤት 18ለ0 በመርታት ለመጨረሻው ማጣሪያ ቀርባለች። በተመሳሳይ ጋና ጊኒን 10ለ1 በሆነ የደርሶመልስ አጠቃላይ ውጤት በማሸነፍ የመጨረሻውን ማጣሪያ ተቀላቅላለች። ሞሮኮና ጋና በመጨረሻው ማጣሪያ እርስበርስ የሚፋለሙም ይሆናል። ካሜሩን ዛምቢያን በድምር ውጤት 5ለ0 አሸንፋ የመጨረሻውን ማጣሪያ የምትፋለም ሌላኛዋ አገር ነች። ካሜሩን የመጨረሻውን ማጣሪያ ከታንዛኒያና ቡሩንዲ አሸናፊ ጋር የምታደርግ ይሆናል። ታንዛኒያ በሦስተኛው ዙር ማጣሪያ የመጀመሪያ ጨዋታዋን ከሜዳዋ ውጪ አድርጋ ተጋጣሚዋ ቡሩንዲን አራት ለዜሮ የረታች አገር እንደመሆኗ የመጨረሻውን ጨዋታ በሜዳዋ አሸንፋ የካሜሩን ተጋጣሚ የምትሆንበት ዕድል ሰፊ ነው።

የዓለም እግር ኳስ መሪ የሆነው ፊፋ የሴቶችን እግር ኳስ ለማሳደግ በተለያዩ የዕድሜ እርከኖች ከሚያከናውናቸው ውድድሮች መካከል ከ17 ዓመት በታች የሴቶች የዓለም ዋንጫ አንዱ ነው። በዚህ የዓለም ዋንጫ እአአ ከ2005 ወዲህ የተወለዱ ሴት እግር ኳስ ተጫዋቾች ተሳታፊ ናቸው። በፈረንጆቹ 2022 ዓመት መጨረሻ በሕንድ አዘጋጅነት ለ7ኛ ጊዜ በሚካሄደው የሴቶች ከ17 አመት በታች የዓለም ዋንጫም ከተለያዩ አህጉራት አዘጋጇ ሕንድን ጨምሮ አስራ ስድስት አገራት ተሳታፊ ይሆናሉ። በዓለም ዋንጫው ተሳታፊ መሆናቸውን የተለያዩ አገራት ከወዲሁ እያረጋገጡም ይገኛሉ። ሦስት አገራት ወደ ዓለም ዋንጫው በሚያልፉበት የኤሽያ አህጉር አዘጋጇ ሕንድ በቀጥታ ተሳታፊ ስትሆን ቻይናና ጃፓንም በ2019 ውጤታቸው መሠረት ተሳታፊ መሆናቸው ቀደም ብሎ የታወቀ ነው። ከመካከለኛውና ሰሜን አሜሪካ እንዲሁም ካሪቢያን አገራትም ሦስት አገራት ተሳታፊ ይሆናሉ። ከደቡብ አሜሪካ አገራት ሦስቱ ተሳታፊዎች ብራዚል፣ ቺሊና ኮሎምቢያ የሕንድ ትኬታቸውን ቀድመው ቆርጠዋል። ከኦሽኒያ ብቸኛዋ ተሳታፊ ኒውዚላንድ ስትሆን ሦስት ሦስት አገራትን የሚያሳትፉት አፍሪካና አውሮፓ በማጣሪያ ሂደት ላይ ይገኛሉ።

---


## ኦሮሚያ ክልል

ንብረትነቱ በመሳይ ቶለሳ አዱኛ የተመዘገበ መኪና ፤ የሠሌዳ ቁጥር 03-66973 -ኦሮ የሆነ መኪና የሻነሲቁጥር JT121JK2100034479 የሞተር ቁጥር 2KD-1545259 ከላይ የተጠቀሰው መኪና ታርጋ ጠፋብን ብለው በ11/08/2014 አመልክቷል፡፡ ታርጋውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ታርጋ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የምዕራብ ሐረርጌ ዞን ትራንስፖርት ባለስልጣን ጽ/ቤት**

## ሲዳማ ክልል

አመልካች(ቾች) እነ ፋሲል በለጠ የውርስ ሀብት ስምምነት እንዲፀድቅ አቤቱታ መነሻነት በቀን 06/08/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ በሟች አቶ /ወ/ሮ ዘለቃ አለሙ ስም ባለው ንብረት ላይ ጥቅሜ ይነካል የሚል ወገን ካለ የጋዜጣ ማሳወጃ ፎርማሊቲ ወጪ በአመልካች( ቾች) ተሸፍኖ ተቃዋሚ ካለ 01/09/2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:30 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ ሀ/ከ/መ/ደ/ፍ/ቤት እንዲቀርቡ በጋዜጣ ታትሞ እንደወጣ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በሲዳማ ብ/ክ/መንግስትየሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ፍ/ቤት**

## አዲስ አበባ አስተዳር

የባለንብረት ስም ጃጋር ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-44889 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር WJME3G-PT004102723 ሞዴል 330-36H የሞተር ቁጥር 8210.42R*269-250222* የሊብሬ ቁጥር 0039507/0233103 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 11/8/2014 አመልክተዋል" የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብEC የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የኮልፌ ቀራንዮ ቅ/ጽ/ቤት**

ከሳሽ - አቶ በሰላም አንዳርጌ ተከሳሽ፣- ወ/ሪት ትዕግስት አንዳርጌ መካከል 3ኛ ውርስ ስላለው ክስ ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በ4/09/2014 ዓ/ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ ከ4:00 ሰዓት ለመ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ 3ኛ ውርስ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

ከሳሽ/አመልካች- አቶ ኃ/ሚካኤል ልኬ ሎሶ በተከሳሽ/ተጠሪ- አቶ ተስፋዬ ተክለዓብ መካከል የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 8ኛ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ02/09/2014 ዓ.ም ከቀኑ 8:00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ጂጋር ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-44880 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር *WJME3GPT004126099* ሞዴል 330-36H የሞተር ቁጥር FIAT8210.42R*271-270614* የሊብሬ ቁጥር 0233197 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 11/8/2014 አመልክተዋል የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የኮልፌ ቀራንዮ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ጂጋር ኮንስትራክሽን/ኃ/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-45133 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር WJM3GPT004103061 ሞዴል 330-36H የሞተር ቁጥር FIAT8210.42K*269-250577 የሊብሬ ቁጥር 003089/0233196 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 11/8/2014 አመልክተዋል የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ኮልፌ ቀራንዮ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ጂጋር ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A30249 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር MROBZ8CD100101819 ሞዴል KUN126L-DTAHY የሞተር ቁጥር 1KD-U823016 የሊብሬ ቁጥር 418625 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 11/8/2014 አመልክተዋል የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የፍ/ባለመብት ህብረት ኢንሹራንስ አማ እና የፍ/ባለዕዳ ጥበብ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማኀበር መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ መከሰስዎን አውቀው ግንቦት 1 ቀን 2014 ዓ.ም. በ3፡30 ሰዓት የተቀጠረ መሆኑን አውቀው ፌ/ከ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 3ተኛ ንግድና ኢንቨስትመንት ፍ/ብሄር 01 ፎቅ ቢሮ ቁጥር 101 ቀጥታ ክስ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል: የማይቀርቡ ከሆነ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ሚኪያስ ንጉሴ ጭቀ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-37436 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JALK6A13567100535 ሞዴል FSR 33L የሞተር ቁጥር 6HH1-414619 የሊብሬ ቁጥር 147646/165541 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 13/8/2014 አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ብሉመቴክ ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A67513 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር LJ12FKR10C4202246 ሞዴል HFC7130A1F የሞተር ቁጥር C3411075 የሊብሬ ቁጥር 044716 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 13/8/2014 አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የልደታ ቅ/ጽ/ቤት**

ህይወት ብርሀኑ በ20/08/2014 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የሊብሬ ደብተር ቁጥር 16002 የሰሌዳ ቁጥር ሥከ-EX-1900 የሆነ ኤክስካቫተር ማሽን ሊብሬ የጠፋባቸው መሆኑን ገልፀው ተለዋጭ ሊብሬ ጠይቀዋል፡፡ በዚሁ መሠረት የኮንስትራክሽን መሣሪያ ሊብሬውን ወድቆ ወይም ተሰርቆ ያገኘ ወይም በሌላ ሁኔታ ይዤዋለሁ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን እንዲያመለክቱ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን**

## ከመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር
### ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ስጡረታ አበል ውሳኔ የሚያዝ የልደት ዘመን

**ሶሎሞን በየነ**

የጡረታ መውጫ እድሜ የመንግስት ሠራተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር በቅድሚያ የመዘገበውን የልደት ዘመን መሰረት በማድረግ እድሜው 60 ዓመት ሲሞላው ይሆናል። ከዚህ አንጻር ለጡረታ አበል ውሳኔ ስለሚያዝ የልደት ዘመን በተመለከተ በመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር የአዲስ አበባ ሪጅን ጽህፈት ቤት የምዝገባና መዋጮ ገቢ መከታተያ ቡድን መሪ አቶ እንቁሥላሴ አጥላው እንደሚከተለው አቅርበውልናል።

ለጡረታ አበል አወሳሰን የሚያዘው የልደት ዘመን የመንግስት ሠራተኛው በጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ የመንግስት ወይም አገልግሎቱ እንዲያዝ በተደረገ የግል ድርጅት ለመጀመሪያ ጊዜ (በቅድሚያ) ለሥራ ሲቀጠር በሞላው መጠየቂያ ወይም በሕይወት ታሪክ ቅጽ ላይ የመዘገበው የልደት ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት ወይም ዕድሜ ነው።

ሁለተኛው ለጡረታ ተግባር የሚያዘው እድሜ ቅድሚያ በተሞላው የሥራ መጠየቂያ ወይም የሕይወት ታሪክ መግለጫ ቅጽ ላይ ወይም ከ1968 ዓ.ም በፊት የተሞላ የተያዥ መስጫ ቅጽ ወይም የምዝገባ ቅጽ ላይ (ቅጽ ጡ -1) ላይ የተመዘገበውን የልደት ዘመን ይሆናል። ቅድሚያ የሚያዘው የትኛው ነው ለሚለው እንደ አቀማመጣቸው ውይም አጠቃቀሳቸው ይሆናል።

ከላይ የተዘረዘሩት አራቱ (የሥራ መጠየቂያ፣ የሕይወት ታሪክ መግለጫ፣ ከ1968 ዓ.ም በፊት የተሞላ የተያዥ መስጫ ቅጽ ወይም ቅጽ ጡ -1) በማይኖሩበት ጊዜ በመስሪያቤቱ በመረጃነት የተያዘ እና የልደት ዘመን የተገለጸበት ማስረጃ ለጡረታ አበል ውሳኔ ተይዞ ይሠራል።

ነገር ግን በማስረጃው ላይ የተወለደበት ቀንና ወር ሳይጠቀስ የተወለደበት ዓመተ ምህረት ብቻ ተመዝግቦ ከተገኘ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከሆነ የዓመቱን መጨረሻ ወርና ቀን ማለትም ነሐሴ 30 ቀን ወይም እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር መዝገቦ ከተገኘ ደግሞ ዲሴምበር 31 ወደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ሲቀየር ታህሳስ 23 ቀን የልደት ቀኑ ተደርጎ ይወሰዳል።

ሌላው ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን መወለዱ የተመዘገበ ሲቪል የመንግስት ሠራተኛ ዕድሜው ለጡረታ የሚደርሰው ከተወለደበት ቀን በፊት ባለው ወር መጨረሻ ቀን ነው። ይህም ማለት ሠራተኛው የልደት ቀኑን ጥቅምት 1/1956 ዓ.ም ብሎ ከመዘገበ ዕድሜው 60 ዓመት የሚሞላው መስከረም 30/2016 ዓ.ም ስለሚሆን ጥቅምት 1 አንስቶ በጡረታ ይሰናበታል። በአንጻሩ ወር በገባ ከ2 እስከ30 ባሉት ቀናት መወለዱን ወይም ወርና ዓመተ ምህረት ብቻ የመዘገበ ከሆነ በጡረታ የሚገለለው ከተወለደበት ወር ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ይሆናል።

የልደት ዘመን ያልመዘገበ ሠራተኛ በሌላ ጊዜ በተከታታይ ከተሞሉ ቅጾች ቅድሚያ ያለው ወይም በአሠሪው መስሪያ ቤት በተያዘ የልደት ዘመን የተገለጸው ቅድሚያ ባለው ማስረጃ የሚያዝ ይሆናል። ነገር ግን የተለያዩ ፎርሞች ላይ የተለያየ የልደት ዘመን መዝግበው የሚገኙ ሠራተኞች ይኖራሉ። በዚህ ጊዜ በተከታታይ በተሞሉ ቅጾች ላይ ዓመተ ምህረቱን፣ ወሩን ወይም ቀኑን በመድገም ከመዘገበ የደገመውን የልደት ዘመን የሚያዝ ይሆናል። በተከታታይ በተሞሉ ቅጾች ላይ ተደግሞ የተመዘገበ የልደት ዘመን ከሌለ በተከታታይ ከተሞሉ ቅጾች ቅድሚያ ያለው የልደት ዘመን እንዲያዝ በሚጋብዘው ቅጽ ላይ የተመዘገበው የልደት ዘመን የሚያዝ ይሆናል።

ሆኖም በተከታታይ ከተሞሉ ቅጾች ቅድሚያ ባለው የልደት ዘመን እንዲያዝ በሚጋብዘው ቅጽ ላይ የተሟላ የልደት ዘመን መረጃ ከሌለ ደግሞ በተከታታይ ካሉ ሌሎች ቅጾች የሚወሰድ ይሆናል። ለአብነት ቅድሚያ ያለው የልደት ዘመን ቅጽ ላይ አመተ ምህረቱ ተጠቅሶ ወርና ቀኑ ከሌለ በተከታታይ ካሉ ሌሎች ቅጾች ላይ ወርና ቀን ከተጠቀሰ ከዛኛው ቅጽ ላይ ወርና ቀኑ ተወስዶ የሚያዝ ይሆናል። እንዲሁም ቅድሚያ ባለው የልደት ዘመን እንዲያዝ በሚጋብዘው ቅጽ ላይ እድሜውን ብቻ የመዘገበ ሠራተኛ ሲያጋጥም ቅጹ ከተሞላበት ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት ላይ ዕድሜው ተቀንሶ የልደት ዘመኑ ይያዛል።

ከዚህ ባሻገር ሠራተኛው በሞላቸው ተከታታይ ቅጾች ውይም በአሠሪው መስሪያቤቱ የሠራተኛው ማህደር ውስጥ ምንም አይነት የልደት ዘመን የሚገልጽ መረጃ በማይኖርበት ጊዜ የጡረታ አበል መጠየቂያ ቅጽ ጡ -2 ላይ የተገለጸው የልደት ዘመን የመጨረሻ አማራጭ ተደርጎ ይያዛል። ይህም ሠራተኛው አምኖበት ያስቀመጠውን የልደት ዘመን ለመያዝ እንገደዳለን ማለት ነው።

በሌላ በኩል የጡረታ ባለመብቱ ከዚህ አለም በሞት ቢለይ እና ለተተኪዎች የጡረታ አበል ለመወሰን ቢፈለግ የልጆች የልደት ዘመን የሚያዘው የጡረታ ባለመብቱ በሕይወት እያለ በአስተዳደር መስሪያቤቱ ያስመዘገበው የልደት ዘመን ነው። የጡረታ ባለመብቱ ካለፈ በኋላ የልደት ዘመን ለመስጠት ፈቃድ ወይም ስልጣን ካለው አካል የሚመጣው የልጆች የልደት ዘመን ከአስተዳደር መስሪያቤቱ ካለው መረጃ ጋር ልዩነት ያለው ከሆነ ሙሉ ለሙሉ ውድቅ ተደርጎ የጡረታ ባለመብቱ በሕይወት እያለ በተቋሙ ስለልጆቹ ያስመዘገበው መረጃ የሚያዝ ይሆናል።

ከዚህ ባለፈ መንግስት ሠራተኛው ወይም የጡረታ ባለመብቱ በሕይወት እያለ የልጆቹን የልደት ዘመን በአስተዳደር መስሪያቤቱ ያላስመዘገበ ከሆነ በአሠሪው የመንግስት መስሪያቤት ወይም አግልግሎቱ በተያዘለት የግል ድርጅት ስለልጆቹ የሞላው የልደት ዘመን የሚያዝ ይሆናል። እንዲሁም ልጁ የተወለደው የጡረታ ባለመብቱ ከሞተ በኋላ ከሆነ ደግሞ ፍርድ ቤት በወሰነው የወራሽነት ውሳኔ ላይ የተገለጸው የልጁ የልደት ዘመን ለጡረታ አበል ውሳኔ ይያዝለታል።

እንዲሁም የልደት ዘመን ማስረጃው ላይ የልጁ እድሜ ብቻ ከተገለጸ መረጃው ከተዘጋጀበት ወይም ፍርድ ቤት የወራሽነት መብቱን እንዲያረጋግጥለት ካመለከተበት ወርና ዓ.ም ላይ በማቀናነስ የልደት ዘመኑ ይያዛል። ነገር ግን ምንም አይነት የልጁን የልደት ዘመን የሚገልጽ መረጃ በማይኖርበት ጊዜ የጡረታ አበል መጠየቂያ ቅጽ ጡ -2 ላይ የተገለጸው የልደት ዘመን የመጨረሻ አማራጭ ተደርጎ ይያዛል።

በአጠቃላይ አንድ የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ እንዲወጣ በሚደረግበት ጊዜ አስቀድሞ ተመዝግቦ የተያዘውን የልደት ዘመን ለመቀየር ወይም ለማስተባበል ሲባል የሚቀርብ ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ ተቀባይነት እንደማይኖረው ቡድን መሪው አቶ እንቁሥላሴ ተናግረዋል።

**አድራሻ:-**

- **ነፃ ስልክ መስመር** ................. 888 /1-2-4/
- **በስልክ** .......... 011-122 97 13/ 011-123 27 24/25/19/30
- **በፋክስ** ......... 011- 123 27 08/09/20
- **ፖ.ሣ.ቁ** ............... 1030
- **ዌብ ሳይት (ፖርታል)**....... www.psssa.gov.et
- **ፌስ ቡክ**... https://www.facebook.com/EthiopiaPSSSA
- **ቴሌግራም** .... https://t.me/PublicPsssa
- **ትዊተር** .... https://twitter.com/PublicEthiopia
- **የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት**.... http://www.eservices.gov.et
- **በኢሜል**............... gmssa@ethionet.et

## ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር
### ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# በኢትዮጵያ ሜጋ ፕሮጀክቶች ላይ ያነጣጠሩ ፖለቲካዊ የሳይበር ጥቃቶች

**ይበል ካሳ**

በአሁኑ ዘመን መረጃን፣ ኮምፒውተር፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ የበይነ መረብ ቴክኖሎጂወችንና ሰው ሰራሽ ክህሎቶችን አጣምሮ ጥቅም ላይ እየዋለ ያለው አዲሱ የዓለማችን የሳይበር ምህዳር፤ ለዓለማችን ካበረከታቸው በጎ ትሩፋቶች መካከል ሰው ራሱን፣ አካባቢውንና ዓለሙን ሊለውጥበት የሚችልበትን የመረጃ ኃይል እንደልብ ማግኘትና መለዋወጥ የሚችልበትን ዕድል መፍጠሩ በትልቁ የሚጠቀስለት ነው።ይህም የሰዉ ልጆችን የዕለት ተዕለት ህይወት በማቅለል ረገድና ዓለም አቀፋዊ ትስስርና ቅርርብ በመፍጠር ዓለማችን ወደተሻለ የዕድገት ጎዳና እንድታመራ አዎንታዊ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።ይሁን እንጂ የምህዳሩን አጠቃቀም ተከትለው የመጡ የጎንዮሽ ችግሮችም በሰው ልጆችና በዓለማችን ደሕንነት ላይ የዚያኑ ያህል አሳሳቢ ስጋቶችን ደቅነዋል፡፡

በዚህም ጥናቶች እንደሚያሳዩት በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን በጦር መሣሪያ ከሚደረገው ጦርነት ይልቅ የሳይበር ጥቃቶች እና ዲጂታል ወንጀሎች በሀገራት ብሔራዊ ደህንነት ላይ ትልቅ ስጋት እየሆኑ መጥተዋል።የሳይበር ጥቃት ፈጻሚዎች ዓላማ እንደጥቃት አድራሾቹ ፍላጎት የተለያየ ሲሆን ዛሬ በዚህ ጽሑፋችን የምንዳስሰው የራሳቸውን ፖለቲካዊ ፍላጎትና ግብ ለማሳካት ልዩ ልዩ መንገዶችን በመጠቀም በሃገራትና በመንግሥታት ላይ በተለይም በእኛ ሃገር ላይ እየተፈጸሙ የሚገኙ የሳይበር ጥቃቶችን ነው፡፡

በኢትዮጵያ ቴክኖሎጅውና የበይነ መረብ ተጠቃሚዎች ቁጥር እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነትና የጥቃት ሙከራ እየጨመረ መምጣቱ የሚጠበቅ ቢሆንም በተለይም ባለፉት አራት ዓመታት ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ በሀገሪቱ ውስጥ ከተፈጠሩ ሀገራዊ ሁኔታዎች ጋር ተያይዞ ግን ፖለቲካዊ ፍላጎት ያላቸው የሳይበር ጥቃቶች በከፍተኛ ደረጃ ቁጥራቸው ጨምሮ ተስተውሏል።በዚህም በ2012 ዓ.ም 1087፣ በ2013 ዓመተ ምህረት ደግሞ ጥቃቱ በ150 በመቶ ጨምሮ 2 ሺ 800 ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት ብቻ በድምሩ 3 ሺ 887 አደገኛ የሳይበር ጥቃቶች መድረሳቸውን የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በያዝነው ዓመት መጀመሪያ አስታውቋል።

ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ጋር ተያይዞ የራሷን ጥቅም ብቻ ለማስጠበቅ የምትፈልገውና ከኢትዮጵያ ጋር አላስፈላጊ ግጭት ውስጥ የገባችው ግብጽና በግድቡ ላይ ፖለቲካዊ ፍላጎት ያላቸው ሌሎች አገራት ቢትዮጵያ ላይ ፖለቲካዊ ጫና ለመፍጠር ያለመ የሳይበር ጥቃት እንደሚያካሂዱም ይታወቃል።በዚህም የግድቡ የመጀመሪያ ዙር ውሃ ሙሌት ከመከናወኑ ጥቂት ጊዜያት ቀደም ብሎ መቀመጫቸውን ግብፅ ያደረጉ የሳይበር ወንጀለኞች ከሰኔ 10 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ለአራት ተከታታይ ቀናት በኢትዮጵያ ላይ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጫና ለመፍጠር ያለመ የሳይበር ጥቃት ለማድረስ ሞክረው በኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አማካኝነት ሙከራው መክሸፉ ይታወሳል።

የሳይበር ጥቃት ሙከራው በሀገሪቱ የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ፣ የደህንነትና የግል ድርጅቶች ላይ ያነጣጠረና በዚህም የ13 የመንግሥት፣ 4 መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ድረ ገጾችን የማስተጓጎል ዓላማ እንደነበረውም ታውቋል።ሳይበር ሆረስ ግሩፕ የተባለው መቀመጫውን በግብጽ ያደረገው የሳይበር ወንጀለኛ ቡድን በግድቡ ሁለተኛ ዙር የውሃ ሙሌት ወቅት በ2013 ዓመተ ምሕረትም ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን ጨምሮ በሌሎች ሜጋ ፕሮጀክቶች ላይ ያነጣጠረና በኢትዮጵያ ላይ ሁለንተናዊ አገራዊ ቀውስን ለመፍጠር ያለመ ፖለቲካዊ የሳይበር ጥቃት በድጋሜ ተሞክሮ በአስተዳደሩ መክሸፉንም ከአስተዳደሩና ከተለያዩ ሚዲያዎች የተገኙ መረጃዎች ያመላክታሉ።

በጥቃት ሙከራው በኢትዮጵያ የበይነ መረብ ሲስተም ውስጥ የነበሩ ከ37 ሺ በላይ ኮምፒውተሮችን ለማጥቃት ታስቦ እንደነበረና በኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የኢንተለጀንስ ቡድን ጥቃቱን ቀድሞ አውቆ ደርሶበት የነበረ በመሆኑ እንዲከሸፍ ማድረጉን መግለጹ ይታወሳል።በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታና ውኃ ሙሌት፣ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ከተካሄደው ህግ የማስከበር እርምጃና ከ2013 አገራዊ ምርጫ ጋር ተያይዞ ፖለቲካዊ ፍላጎት ያላቸው የሳይበር ጥቃቶች በከፍተኛ ደረጃ እየጨመሩ መጥተዋል፡፡

የሳይበር ጥቃቶቹ የስነ ልቦና ጦርነትን አጣምረው የሚፈጸሙ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ ሃገራችን ባለፈው አንድ ዓመት ስታካሂደው በቆየችው ህልውናንና ሉዓላዊነትን የማስጠበቅ ጦርነት የሳይበር ጦርነት አካል በሆነው የሃሰተኛ መረጃ ስርጭትና የሃገሪቱን ስም የማጥፋትና መልካም ገጽታን የማጠልሸት ፕሮፓጋንዳ ምዕራባውያንና ሌሎች የኢትዮጵያ ጠላቶች በህልውና ዘመቻው ሂደት ሲያደርሱት የነበረው ጫና ምን ያህል እንደነበረ የሚታወስ ነው።የዓለም ሃገራትን ሁሉ በእኩልነት ያገለግላል ተብሎ የሚታሰበው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሳይቀር ግብጽና የምዕራባውያን በኢትዮጵያ ላይ የሚያካሂዱትን ሃሰተኛ የሳይበር ፕሮፓጋንዳ እንደትክክለኛ አጀንዳ ቆጥሮ ከታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ጋር ተያይዞ በማይመለከተው የልማት ጉዳይ ላይ የዓለምን ሪከርድ የሰበረ ጉባኤ ጠርቶ መቀመጡ ለዚህ ትልቅ ማሳያ ነው።

የእነዚህ ሁሉ የፖለቲካዊና ሥነ ልቦናዊ የሳይበር ጥቃቶች ዋነኛ ዓላማም የግድቡን ግንባታ ማስተጓጎል፣ የኢትዮጵያን መፍረስ የሚፈልገውን አሸባሪውን የሕወሓት ቡድን ወደስልጣን መመለስና እንደ ግብጽና ምዕራባውያን የመሳሰሉ የኢትዮጵያን መዳከም የሚፈልጉ ኃይሎችን የግል ፍላጎት ማስጠበቅና በአጠቃላይ በሃገራዊ ቀውስ ውስጥ የምትኖርና ሉዓላዊነቷን ማስጠበቅ የማትችል ደካማ ኢትዮጵያን መፍጠር ስለመሆኑ ስለእውነት የሚኖሩ፣ የሚናገሩና የሚጽፉ ሁሉ የሚያውቁት ሐቅ ነው፡፡

በመሆኑም መንግሥትና ሕዝብ ከሁሉም በላይ ለሳይበር ደህንነት ቅድሚያ ሰጥተው ሊሠሩ ይገባል።የሳይበር ደህንነት መረጃን፣ የመረጃ መሰረተ ልማትን እንዲሁም ሰዎችን አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚፈጥሩ ጥቃቶች መጠበቅን ያለመ ሲሆን በዋናነትም የመረጃ እና መሰረተ ልማትን ምስጢራዊነት፣ ተአማኒነትን እና ተደራሽነትን ማረጋገጥ ላይ የሚያተኩር የሳይበር ደህንነት አሠራርን መዘርጋትና በጥብቅ ዲሲፒሊን መተግበር ያስፈልጋል።ለዚህም የመንግስት ተቋማት፣ የግል ድርጅቶችና ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉም በንቃት የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ከተወጣ በኢትዮጵያ የልማት ጉዞ ላይ የተደቀነውን የተሰወረ ግን የተገለጠ የሳይበር ጥቃትና የኢትዮጵያን ጠላቶች ዓላማ በማክሸፍ ሁለንተናዊ ደህንነቷና ሉዓላዊነቷ የተረጋገጠ በሁሉም ዘርፍ አሸናፊ የሆነች ጠንካራ ኢትዮጵያን መገንባት ይቻላል።